fetena.net : Ethiopian online exams and books


አካባቢ ሳይንስ

ሁለተኛ ክፍል

የተማሪ መጽሐፍ








አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

አካባቢ ሳይንስ

የተማሪ መጽሐፍ

2ኛ ክፍል

አዘጋጅ፡- መኮንን ታፈሰ

አርታኢ፡- ብርሃኑ ሀብተማሪያም
መድሃኔ እቁባሚካኤል

ገምጋሚዎች፡- መኮንን ሰገሠ ታችበሌ
ብርሃኑ ፍቅሩ ፍሬሰንበት
ሰሎሞን ወንድሙ መታፈሪያ
ደስታ መርሻ ኦዳ
ግርማ መንግሥቱ ጥሩነህ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
2006 ዓ.ም

© 2006 የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

ይህንን መጽሐፍ ከተዘጋጀበት ዓላማ ውጭ በከፊልም ይሁን በሙሉ በኅትመት ወይንም በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች ወይንም በየትኛውም መንገድ ያለ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ፈቃድ ማባዛትና አስመስሎ ማራባት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር ፬፻፲/፲፱፻፺፮ ዓ.ም. በጸደቀው የቅጅና የተዛማጅ መብቶች ጥበቃ ሕግ አዋጅ መሠረት ያስቀጣል::

የመጽሐፉ አዘጋጅ፡- ኩራዝ ኢንተርናሽናል አሳታሚ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

☎ +251 111 224 504
+251 111 224 505

E-mail: kurazpublisher@gmail.com
kurazpublisher@yahoo.com

✉ 100767
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ማውጫ

ምዕራፍ 1 እኛ

1.1 የምንመገበው ምግብ 2
1.2 ጤነኞች ነን 13
1.3 የግል ንጽሕናችንን እንጠብቃለን 20
ማጠቃለያ 29
የማጠቃለያ ጥያቄዎች 30
ፍተሻ 32

ምዕራፍ 2 ማኅበረሰባችን

2.1. የማኅበረሰብ አባላት 34
2.2 በማኅበረሰብ ውስጥ መኖር 50
2.3 የጉልበት አስፈላጊነት 59
2.4. ከሸክላ አፈር ከጄሶና ከወረቀት የተለያዩ ነገሮችን መሥራት 65
ማጠቃለያ 78
የማጠቃለያ ጥያቄዎች 79
ፍተሻ 81

ምዕራፍ 3 የተፈጥሮ አካባቢያችን

3.1 የተፈጥሮ ክስተቶች 83
3.2 የተፈጥሮ ሀብቶች 92
3.3 በዙሪያችን የሚገኙ ተክሎች..... 104
3.4 በዙሪያችን የሚገኙ እንስሳት..... 113
ማጠቃለያ 121
የማጠቃለያ ጥያቄዎች 122
ፍተሻ 124

ምዕራፍ 4 ክፍለ ከተማችን

4.1. የክፍለ ከተማችን መገኛ 126
4.2 የክፍለ ከተማችን የመሬት ገጽታ 131
4.3 በክፍለ ከተማችን ውስጥ የሚገኙ ተቋማት..... 136
4.4 የክፍለ ከተማችን የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች 140
ማጠቃለያ 152
የማጠቃለያ ጥያቄዎች 153
ፍተሻ 154

ምዕራፍ አንድ

እኛ

ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ይህንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፦

- የምግብን ጠቀሜታ ትናገራላችሁ፡፡
- በአካባቢያችሁ የተለመዱ የምግብ ዓይነቶችን ስሞች ትጠቅሳላችሁ፡፡
- ከእንስሳትና ከተክሎች የሚገኙ የምግብ ዓይነቶችን ትለያላችሁ፡፡
- ተገቢ የአመጋገብ ሥርዓትን በተግባር ታሳያላችሁ፡፡
- የጤናን ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- በጤነኛና በህመምተኛ ሰው መካከል ያለውን ልዩነት በማነጻጸር የጤናን አስፈላጊነት ታብራራላችሁ፡፡
- አንዳንድ የሕመም ምልክቶችን ትገልፃላችሁ፡፡
- የሕመም ስሜቶች ሲሰሟችሁ እንዴት ለሌሎች መናገር እንዳለባቸሁ ትለማመዳላችሁ፡፡
- ስለ ግል ንጽሕና ጠቀሜታ ታስረዳላችሁ፡፡
- የግል ንጽሕናን አለመጠበቅ የሚያስከትላቸውን ችግሮች ትገልጻላችሁ፡፡
- ተገቢ የግል ንጽሕና አጠባበቅን ትለማመዳላችሁ፡፡
- የሳይንሳዊ ምርምር ክህሎቶችን ማለትም፡- መመልከትን፣ መጠየቅን፣ መመደብን፣ መግባባትንና ተባብሮ መሥራትን በተግባር ታሳያላችሁ፡፡

1.1 የምንመገበው ምግብ

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦

- ስለምግብ ጠቀሜታ ታብራራላችሁ።
- በአካባቢያችሁ የተለመዱ የምግብ ዓይነቶችን ስሞች ትጠራላችሁ።
- ምግቦችን ከእንስሳትና ከተክሎች የሚገኙ በማለት ትመድባላችሁ።
- ከእንስሳትና ከተክሎች የሚገኙ ምግቦችን ምሳሌዎች ትሰጣላችሁ።
- ተገቢ የገበታ ሥርዓትን በተግባር ታሳያላችሁ።
- ርህራሄን በተግባር ታሳያላችሁ።

ቁልፍ ቃላት

- ገንቢ ምግብ
- ጉልበት ሰጪ ምግብ
- በሽታ ተከላካይ ምግብ
- የገበታ ሥርዓት

ሀ. ለ. ሐ. መ.






ሠ. ረ. ሰ. ሸ.






ቀ. በ. ተ. ቸ.






ሥዕል 1.1 የምግብ ዓይነቶች

ተግባር 1.1.1 ☛ የቡድን ሥራ

ዓላማ- ስለ ምግብ መገንዘብና የምግብ ዓይነቶችን መለየት

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን መሥርታችሁ ከታች በተሰጡት ጥያቄዎች መሠረት በመወያየት ለመምህራችሁና ለተማሪዎች ዘገባ አቅርቡ፡፡

ጥያቄዎች

- የሰው ልጅ በሕይወት ለመኖር ምን ያስፈልገዋል?
- ከላይ በስዕሉ የቀረቡትን የምግብ ዓይነቶች ለመምህራችሁ በዝርዝር ተናገሩ፡፡
- ሥዕል 1.1 የሚታዩት የምግብ ዓይነቶች ምን ምን ጥቅሞችን ይሠጣሉ?

ምግብ ለሰውነታችን አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች አንዱ ነው፡፡ ምግብ ጤናማና ጠንካራ ለመሆን ይረዳል፡፡ በሥዕል 1.1 የቀረቡት የምግብ ዓይነቶች ከሚሰጡት ጥቅም አንጻር በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይመደባሉ፡፡ እነዚህም ለእድገት የሚጠቅሙ፣ በሽታን የሚከላከሉና ጉልበት ሰጪ በመባል ይታወቃሉ፡፡

ተማሪዎች ከዚህ በመቀጠል

ሀ. ስለምግብ ጠቀሜታ

ለ. ስለምግብ ምንጮች

ሐ. ስለተለመዱ የምግብ ዓይነቶችና

መ. ስለገበታ ሥርዓት ትማራላችሁ፡፡

ሀ. የምግብ ጠቀሜታ



ሀ. በጥሩ አመጋገብ የተያዘ ሕጻን



ለ. በቂና የተመጣጠነ ምግብ ያላገኘ ሕጻን

ሥዕል 1.2 የተመጣጠነ ምግብ ያገኘና ያላገኘ ህፃን

- በሥዕሉ ከምታዩአቸው ሕጻናት ጤነኛው የትኛው ነው? ለምን?

ተግባር 1.1.2 ☛ **የቡድን ሥራ**

ዓላማ- ስለ ምግብ ጥቅም መግለጽ

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች መሠረት ከወላጆቻችሁና ከሌሎች ሰዎች መረጃ ሰብስባችሁ በክፍል ውስጥ ዘገባ አቅርቡ፡፡

ጥያቄዎች

- በቂ ምግብ የማይመገብ ተማሪ ምን ዓይነት የጤና ችግር ያጋጥመዋል?
- ምግብ ምን ዓይነት ጥቅሞችን ያስገኛል?

ምግብ ለሰውነታችን የሚከተሉትን ጥቅሞች ይሰጣል፡፡

- ሰውነታችንን ለመገንባትና ለመጠገን ይረዳል፡፡
- ሰውነታችንን ከበሽታ ለመከላከል ይጠቅማል፡፡
- ኃይልንና ጉልበትን ለማግኘት ይጠቅማል፡፡

1. ሰውነትን ለመጠገንና ለመገንባት

ሰውነትን ለመጠገንና ለመገንባት የሚጠቅሙ ምግቦች ገንቢ ምግብ ይባላሉ፡፡
የሚከተሉትን ሥዕሎች በትኩረት ተመልከቱ፡፡

ሀ.



ለ.



ሐ.



መ.



ሠ.



ረ.



ሥዕል 1.3 የገንቢ ምግብ ዓይነቶች

ተግባር 1.1.3 ☛ **በግል የሚከናወን ተግባር**

ዓላማ- ገንቢ ምግቦችን በስም መለየት

መመሪያ- በየግላችሁ በሥዕል 1.3 ላይ የምትመለከቷቸውን ገንቢ ምግቦች ስም በደብተራችሁ ላይ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ሥጋ፣ ወተት፣ አይብ፣ እንቁላል፣ ባቄላ፣ አተር፣ ሽምብራ፣ ምስርና የመሳሰሉት ገንቢ ምግቦች ናቸው፡፡

2.በሽታን ለመከላከል

ተግባር 1.1.4 ☛ የቡድን ሥራ

ዓላማ- በሽታ ተከላካይ ምግቦችን መለየት

መመሪያ- በቡድን በመወያየት ከዚህ በታች በተሰጡት የቡድን ሥራ ነጥቦች መሠረት ካከናወናችሁ በኋላ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

የቡድን ሥራ ነጥቦች

- በሥዕል 1.4 ከሀ-ቀ በቀረቡት የምግብ ሥዕሎች ስር ስሞቻቸውን ጻፉ።
- በሽታ ተከላካይ ምግቦችን ከምን ከምን እንደምናገኝ ግለጹ?
- ምግቦቹን ለሁለት በመክፈል አትክልትና ፍራፍሬ በማለት መድቡ።

	አትክልት	ፍራፍሬ
1		
2		
3		
4		
5		
6		



ሀ.



ለ.



ሐ.



መ.



ሠ.



ረ.



ሰ.



ሸ.



ቀ.

ሥዕል 1.4 በሽታ ተከላካይ ምግቦች

በሽታ ተከላካይ ምግቦች ሰውነትን ከልዩ ልዩ በሽታዎች ይከላከላሉ። በሽታ ተከላካይ ምግቦች ከአትክልትና ፍራፍሬዎች እንዲሁም ጨውን ከመሳሰሉ ማዕድናት ማግኘት ይቻላል።

ብርቱካን፣ ሎሚ፣ ፓፓያ፣ ሙዝና አናናስ ከፍራፍሬ የምግብ ዓይነቶች የሚመደቡ ሲሆን ጥቅል ጐመን፣ ካሮት፣ ቲማቲምና ቃሪያ ደግሞ ከአትክልት የምግብ ዓይነቶች ይመደባሉ።

አትክልትና ፍራፍሬ የተመገበ ልጅ እድገቱ ፈጣንና ሰውነቱም ጤናማ ይሆናል።

3. ጉልበት ስመስጠት

ተግባር 1.1.5 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- ጉልበት ሰጪ ምግቦችን መለየት

መመሪያ- በውይይት ጥያቄዎቹ መሠረት በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ በደብተራችሁ ላይ በመጻፍ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

የውይይት ጥያቄዎች

- ማንኛውንም ሥራ ለመሥራት ምን ያስፈልጋል?
- ጉልበት የሚሰጡ ምግቦች የትኞቹ ናቸው? ዘርዝሯቸው።

ሥራ ለመሥራት ጉልበት ያስፈልጋል። ሰውነታችን ጉልበትን ከምግብ ያገኛል።

- ከታች በሥዕሉ ላይ የምታዩአቸውን ምግቦች ስም በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ ጻፉ።



ሀ.



ለ



ሐ.



መ.



ሠ.



ረ.

ሥዕል 1.5 ጉልበት ሰጪ የምግብ ዓይነቶች

ጉልበትና ኃይል የሚሰጡ ምግቦች እንደ ድንች፣ ሽንኮራ አገዳ፣ በቆሎ፣ ስንዴ፣ ጤፍ፣ ስኳር ድንች፣ ፓስታ፣ ቅቤ፣ ዘይት፣ መኮሮኒና የመሳሰሉት ናቸው።

ተማሪዎች! ምግብ ብዙ ጥቅሞች እንዳለው ተረዳችሁ። ይኸውም፡-

- ✓ ጤናማ ዕድገት እንዲኖረንና በአደጋ ወቅት የተጐዳ የሰውነት ክፍልን ለመጠገን
- ✓ በበሽታ እንዳንጠቃና፤
- ✓ ማንኛውንም ሥራ መሥራት የሚያስችለንን ጉልበት እንድናገኝ ይረዳናል።

ሰ. የተለመዱ የምግብ ዓይነቶች

ተግባር 1.1.6 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- በአካባቢያችን የተለመዱ ምግቦችን መለየት

መመሪያ- በመወያያ ጥያቄዎቹ መሠረት በቡድን ተወያይታችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ።


የመወያያ ጥያቄ

- በአካባቢያችሁ የተለመዱና የምታውቋቸው የምግብ ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?

በተለያየ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች የተለያዩ የምግብ ዓይነቶችን ይመገባሉ። አንዳንድ ሰዎች እንጀራ፣ የሽሮ ወጥ፣ የምስር ወጥ የመሳሰሉትን ያዘወትራሉ። ሌሎች ሰዎች ደግሞ የሥጋ ወጥና የአትክልት ምግቦችን ይመገባሉ።

የምግብ ምንጮች

የምንመገባቸውን ምግቦች የምናገኛቸው ከእንስሳት ወይም ከእፅዋት ነው።



ሥዕል 1.6 ከተለያዩ የምግብ ምንጮች የሚገኙ የምግብ አይነቶች

ተግባር 1.1.7 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- የምግብ ምንጮችን መለየት

መመሪያ- በቡድን በመሆን በመወያያ ጥያቄዎቹ መሠረት ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

የመወያያ ጥያቄዎች

- የምንመገባቸው ምግቦች ከምን ዓይነት ምንጮች ይገኛሉ?
- ሥዕል 1.6ን በመመልከት ከእንስሳት የምናገኛቸውንና ከእፅዋት የምናገኘውን የምግብ ዓይነቶች በመለየት ከታች በሰንጠረዡ ውስጥ ጻፉ።
- ሥዕል 1.6ን በመመልከት የፍራፍሬ ዓይነቶችን ዘርዝሩ።

የምግብ ዓይነት	ምንጭ	
	እንስሳት	እፅዋት

የምግብ ምንጮች ሁለት ናቸው። እነርሱም እንስሳትና ተክሎች ናቸው። ከእንስሳት የምናገኛቸው የምግብ ዓይነቶች ሥጋ፣ እንቁላል፣ ወተትና የወተት ውጤቶች ናቸው። የወተት ውጤት የምንላቸው እርጎ፣ ቅቤና አይብ ናቸው።

ተግባር 1.1.8 ☛ **የቡድን ሥራ**

ዓላማ- ከተክሎች የሚገኙ የምግብ ዓይነቶችን መለየት

መመሪያ- ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ከተክሎች የሚገኙ የምግብ ዓይነቶች በተሰጠው ሰንጠረዥ ውስጥ በየምድባቸው ጻፉ።

ብርቱካን፣ ገብስ፣ ጐመን፣ ጤፍ፣ በቆሎ፣ ጥቅል ጐመን፣ ድንች፣ ሙዝ፣ ፓፓያ፣ ባቄላ፣ አተር፣ ማንጐ፣ ወይን፣ ቀይሥር፣ ካሮት፣ አናናስ፣ ሽምብራ፣ ቃሪያ፣ ምስር፣ አቮካዶ፣ ቲማቲም

ከተክሎች የሚገኙ የምግብ ዓይነቶች		
ፍራፍሬዎች	ጥራጥሬዎች	አትክልቶች

ተግባር 1.1.9 ☛ **በግል የሚከናወን ተግባር**

ዓላማ- የምግብ ዓይነቶችን አዘገጃጀት ማጥናትና ምግቦችን በስዕል ማሳየት

መመሪያ- ከዚህ በታች በተሰጡት ትዕዛዞች መሠረት በየግላችሁ ሠርታችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ::

ጥያቄዎች

- እርጎ፣ ቅቤና አይብ እንዴት እንደሚዘጋጁ ወላጆቻችሁን በመጠየቅ በዝርዝር ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ::
- ሁለት የፍራፍሬ አይነቶችን ምረጡና በወረቀት ላይ ሳሉ:: ከዚያም በቀለም (ክለር) ካቀለማችኋቸው በኋላ በቅርጻቸው ትክክል ቀርጻችሁ በማውጣት ለመምህራችሁ አሳዩ::

መ. የገበታ ሥርዓት

የገበታ ሥርዓት ማለት ምግብን በምንመገብበት ወቅት መከተል የሚገባን ሥነ ሥርዓት ማለት ነው::

የገበታ ሥርዓት ከቦታ ቦታ እንደየባህሉ ይለያያል:: ይህ የገበታ ሥርዓት ለጤናችን ጠቃሚ ተግባር ነው::



ሥዕል 1.7 የመጀመሪያው የገበታ ሥርዓት



ሥዕል 1.8 በቤተሰብ ውስጥ የሚታይ የገበታ ሥርዓት

- በሥዕል 1.7 የምታዩት ተግባር ምንድን ነው?
- በሥዕል 1.8 በምታዩት የቤተሰብ የገበታ ሥርዓት ምን ታስታውሳላችሁ?

ተግባር 1.1.10 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- ስለገበታ ሥርዓት መግለጽ

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን መሥርታችሁ በመወያያ ጥያቄዎቹ መሠረት ተወያይታችሁ የውይይታችሁን ዋና ዋና ነጥቦች ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

የመወያያ ጥያቄዎች

- ምግብ ከመመገባችን በፊት ምን ማድረግ አለብን?
- ምግብ በምንመገብበት ጊዜ ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?
- ምግብ ከመዋጣችን በፊት ማኘክና ማላመጥ ለምን ይጠቅማል?
- በገበታ ሥርዓት ተገቢ የሆነውንና ተገቢ ያልሆነውን ተግባር በመለየት በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ጻፉ፡፡

ተ.ቁ	በገበታ ሥርዓት ተገቢ የሆነ ተግባር	በገበታ ሥርዓት ተገቢ ያልሆነ ተግባር
1		
2		
3		
4		
5		

- በቡድን በመሆን የገበታ ሥርዓት እንዴት እንደሚካሄድ ለመምህራችሁ ግለጹ፡፡

በገበታ ሥርዓት ሊደረጉ የሚገባቸው ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- እጅን በሳሙና መታጠብ
- ንጹሕ የመመገቢያ ዕቃዎችን ማዘጋጀት
- የመጠጥ ውሃ አስቀድሞ ማቅረብ
- ለሌሎች ሰዎች ቅድሚያ መስጠትና የሌሎችን ሰዎች ፍላጐት ተረድቶ ማስተናገድ
- በምንመገብበት ወቅት ትኩረታችንን ምግቡ ላይ ማድረግ
  - ➢ ምግቡን ለማድቀቅና በቀላሉ ለመዋጥ መጥኖ መጉረስ
  - ➢ ሲመገቡ አለማውራት ትንታን ይከላከላል፡፡
    - → ሌሎች ተመጋቢዎችን አያስቀይምም፡፡
  - ➢ አፋችንን ገጥመን መብላት
    - → የምንመገበው ምግብ ወደ ውጭ እንዳይንጠባጠብ ይጠቅማል፡፡
    - → ሌሎች ተመጋቢዎችን አያስቀይምም፡፡
  - ➢ የምንመገበውን ምግብ በምራቃችን በደንብ በማራስና በማኘክ መዋጥ፡፡

ምግብ ተመግበን ከጨረስን በኋላ

- አፋችንን በንፁህ ውሃ መጉመጥመጥ
- እጆቻችንን በውሃና በሳሙና መታጠብ
- የተመገብንባቸውን ዕቃዎች አጥቦና አድርቆ በንጹሕ ቦታ ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡

መልመጃ 1.1

ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

1. ቅቤና ወተት ከተክሎች የሚገኙ የምግብ ዓይነቶች ናቸው።
2. ምግብ ሰውነትን ለመገንባት ብቻ ይጠቅማል።
3. ምግብ በሚቀርብበት ጊዜ ለሌሎች ቅድሚያ መስጠት ያስፈልጋል።

ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ።

1. ከሚከተሉት ውስጥ ትክክለኛ የገበታ ሥርዓት ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. አፍን ገጥሞ መብላት　　ሐ. እጅን አስቀድሞ መታጠብ

ለ. ምግብን በችኮላ መዋጥ　　መ. እየተመገቡ አለማውራት

2. ከሚከተሉት ውስጥ ከአትክልት የሚመደበው የምግብ ዓይነት የትኛው ነው?

ሀ. ቲማቲም　　ለ. አናናስ　　ሐ. አተር　　መ. በቆሎ

ሐ. በ 'ሀ' ሥር የቀረቡትን የምግብ ጥቅምች በ'ለ' ሥር ካሉት የምግብ ዓይነቶች ጋር አዛምዱ


'ሀ'		'ለ'
____1. ሰውነትን ይገነባሉ	ሀ.	 ድንች  በቆሎ  ሸንኮራ አገዳ
____2. የወተት ውጤቶች	ለ.	 ሥጋ  ወተት  እንቁላል
____3. የፍራፍሬ ምግብ ዓይነቶች	ሐ.	 አይብ  ቅቤ  እርጎ
_____4. ጉልበት ይሰጣሉ	መ.	 አናናስ  ፓፓያ  ሙዝ

መ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::

1. ጠንካራና ጤነኛ ለመሆን ምን ምን የምግብ አይነቶችን መመገብ አለብን?

2.  ከዶሮ የምናገኛቸው የምግብ ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?

3. የሚከተሉትን ሳጥኖች በትክክለኛው መልስ ሙሉ።



1.2 ጤነኞች ነን

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠብቁ የመማር ብቃቶች
ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦ • ጤና አካላዊ፣ አዕምሯዊና ማህበራዊ ደህንነት መሆኑን ትገልፃላችሁ። • ስለ ጤና አስፈላጊነት ታስረዳላችሁ። • የሕመምተኛን ሰው ገጽታዎች ከጤነኛ ሰው ገጽታዎች ጋር ታነጻጽራላችሁ። • ሕመምተኞችን ስለመርዳት አስፈላጊነት ታስረዳላችሁ። • አንዳንድ የሕመም ምልክቶችን ትገልጻላችሁ። • የህመም ስሜት ሲሰማችሁ ለሌሎች የመናገርን አስፈላጊት ታስረዳላችሁ።

ቁልፍ ቃላት

- ጤና
- ሕመም

ሀ. ጤና ምንድን ነው?

ተግባር 1.2.1 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- ስለ ጤና ምንነት መግለጽ

መመሪያ- ከ4-6 ተማሪዎች ባልበለጠ ቁጥር ቡድን መሥርታችሁ በመወያያ ጥያቄዎች መሠረት በመወያየት የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለክፍላችሁ አቅርቡ።

የመወያያ ጥያቄዎች

- ጤና ማለት ምን ማለት ነው?
- አንድ ሰው ጤነኛ ነው ሲባል ምን ማለት ነው?
- ጤነኛ ሰዎች ምን ዓይነት ባህርይ (ፀባይ) ይታይባቸዋል?

ጤና ማለት አለመታመም፣ ደኅና መሆንና ደስተኛ መሆን ማለት ነው። ሰው በአካሉ ላይና በአዕምሮው ምንም ሕመም ከሌለው ጤነኛ ሰው ነው ይባላል።

ጤነኛ ሰው ደስተኛና በራሱ ጥሩ ስሜት የሚሰማው ነው።

ጤና በአካላችን፣ በአእምሮችንና በማኅበራዊ ሕይወታችን ያለ ደኅንነት ማለት ነው።

ለ. የመልካም ጤንነት አስፈላጊነት



ሥዕል 1.9 መልካም ጤንነት ያለው ሰው በግብርና ሥራ ላይ

ተግባር 1.2.2 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- ስለ ጤና አስፈላጊነት በመግለጽ

መመሪያ- በቡድን በመሆን በመወያያ ነጥቦቹ ላይ ተወያይታችሁ የቡድናችሁን ሐሳብ አቅርቡ፡፡

የመወያያ ነጥቦች

- ምን እንደሚያስደስታችሁና ምን እንደሚያስከፋችሁ በዝርዝር ግለጹ፡፡
- ጤነኛ መሆን ለምን ይጠቅማል?
- ለአካል ጉዳተኞች ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?
- በጓደኞቻችን ላይ ኃይልን መጠቀም ምን ዓይነት ችግር ያስከትላል?


ጤነኛ ሰው ደስተኛ ነው፡፡ ጤነኛ ስንሆን ከሰዎች ጋር መልካም ግንኙነት ይኖረናል፡፡ ትምህርታችንን በአግባቡ መከታተል እንችላለን፡፡ ጤነኛ ስንሆን ከጓደኞቻችን ጋር መጫወት እንችላለን፡፡ ጤነኛ ሰው የዕለት ተግባሩን ማከናወን ይችላል፡፡

አካል ጉዳተኞችን ማገዝ መልካም ተግባር ነው፡፡ አካል ጉዳተኝነት በሽታ ወይም ሕመም ሳይሆን በተፈጥሮና በአደጋ ሊከሰት የሚችል ጉዳት ነው፡፡ ለሕመምተኛ ሰዎች ፍቅር ማሳየት ተገቢ ሥነ ምግባር ነው፡፡ በጓደኞቻችንም ላይ ኃይል መጠቀም የለብንም፡፡ በአጠቃላይ ጤናማ መሆን

- ትምህርታችንን እንድንከታተል ይረዳናል፡፡
- ሥራችንን እንድናከናውን ይጠቅመናል፡፡
- በራሳችን ደስታ እንዲሰማን ያደርጋል፡፡

አካል ጉዳት ማለት አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የአካል ክፍላችን ተግባሩን (ሥራውን) ማከናወን ሳይችል ሲቀር ነው፡፡

ሐ. ጤነኛና ሕመምተኛ ሰዎችን ማነጻጸር



ሀ. ሕመምተኛ ሰው



ለ. ጤነኛ ሰው

ሥዕል 1.10 ሕመምተኛ ሰውና ጤነኛ ሰው

ተግባር 1.2.3 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- ስለ ሕመም ምልክቶች ማወቅና ለሕመምተኛ ሰው መደረግ ያለበትን እንክብካቤ ማድረግ

መመሪያ- ከ5-6 ተማሪዎች ባልበለጠ ቁጥር ቡድን መስርታችሁ በመወያያ ጥያቄዎች መሠረት በመወያየት የተስማማችሁበትን ሀሳብ ለክፍላችሁ ተማሪዎች አቅርቡ።

የመወያያ ጥያቄዎች

- በሽተኛ ሰው ከጤነኛ ሰው በምን ይለያል? ስዕል 1.10ን በማየት የሁለቱን ሰዎች ልዩነት ዘርዝሩ።
- ለታመመ ሰው ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?

ጤነኛ ሰው	ሕመምተኛ ሰው
• ጠንካራና ንቁ ነው። • ደስተኛ ነው። • መጫወትና መሥራት ይወዳል • ትምህርቱን በሚገባ ይከታተላል።	• ደካማና ፈዛዛ ነው። • የመከፋትና ደስታ የማጣት ስሜት ይታይበታል። • መኝታን ያበዛል። • ትምህርቱን መከታተል ይሳነዋል።

ሕመምተኛ ሰዎችን መርዳት አስፈላጊ ተግባር ነው። ሕመምተኞች የሚመገቡትን ምግብና የሚገለገሉበትን ቁሳቁስ በማቅረብ ልንረዳቸውና ልንንከባከባቸው ይገባል።

መ. የህመም ምልክቶች



ሀ. ሳል ለ. ትኩሣት ሐ. ማንቀጥቀጥ

ሥዕል 1.11 የሕመም ምልክቶች

ተግባር 1.2.4 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- ስለ ሕመም ምንነትና ምልክቶች መግለጽ

መመሪያ- በቡድን ተወያይታችሁ የውይይቱን ነጥቦች በደብተራችሁ ላይ ጻፉ።

የመወያያ ጥያቄዎች

- ሕመም ምንድን ነው?
- የሕመም ምልክቶች የምንላቸው ምን ምን ናቸው?

ሕመም ማለት የሰውነታችን ጤንነት መጓደል ማለት ነው። ጤንነታችን ሲጓደል አካላችንና አእምሯችን መሥራት ይሳነዋል። ማኅበራዊ ሕይወታችንም ይናጋል።

የተለያዩ በሽታዎች የተለያዩ የሕመም ምልክቶችን ያሳያሉ። ሆኖም በብዙ በሽታዎች የሚታዩ የጋራ ምልክቶች አሉ። ለምሳሌ ትኩሳት፣ ማንቀጥቀጥ፣ ራስ ምታት፣ ውጋት፣ ቁርጠት፣ የምግብ ፍላጎት መቀነስ፣ ማስታወክ (ማስመለስ) እና ተቅማጥ ዋና ዋና የሕመም ምልክቶች ናቸው።

ተግባር 1.2.5 ☛ **የሚና ጫወታ**

ዓላማ- በሕመም ወቅት የበሽታ ምልክቶችን መናገር።

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን መሥርቱ። አንድ ተማሪ እንደ ታማሚ፣ አንድ ተማሪ እንደ ሐኪም፣ ሁለት ተማሪዎች እንደ እናትና አባት (ቤተሰብ) በመሆን ቤተሰብና ሐኪም ለሚጠይቁት ጥያቄዎች ታማሚ ትክክለኛ የበሽታውን ምልክት እንዲገልጽ ወይንም እንድትገልጽ አድርጉ። ሐኪምም በተገለጸው ምልክት መሠረት በሽታውን ለማወቅ ወይም ለመገመት ሲሞክር በተግባር በሚያሳይ መልኩ የሚና ጨዋታውን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ።

ሠ. የሕመም ስሜት (ምልክት) ሲሰማን ምን ማድረግ ይኖርብናል?

ተግባር 1.2.6 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- ሕመም ሲያጋጥም መደረግ የሚገባውን ነገር መግለጽ

መመሪያ- ቡድን መሥርታችሁ ከታች በተሰጡት መወያያ ጥያቄዎች መሠረት ተወያይታችሁ ለክፍላችሁ ተማሪዎች ሪፖርት አቅርቡ።

የውይይት ጥያቄዎች

- የሕመም ስሜት ሲሰማን ለማን መንገር አለብን?
- የታመሙ ሰዎች ምን ምን ዓይነት ምልክቶች ይታዩባቸዋል?
- በምንታመምበት ወቅት ለማንም ሰው አለመናገር ምን ጉዳት ያስከትላል?



ሥዕል 1.12 ሕመምተኛ ልጅ በሀኪም ሲመረመር

ሕመም ሲሰማን በፍጥነት ለወላጆቻችን፣ ለመምህሮቻችን፣ ለአሳዳጊዎቻችን ወይም በአቅራቢያችን ለሚገኝ ሰው መንገር አለብን። የሕመም ስሜትን አለመናገር በወቅቱ ተገቢ የሕክምና እርዳታ እንዳናገኝ በማድረግ ችግሩን የከፋ ያደርገዋል። በታመምንበት ጊዜ ተገቢ የሕክምና እርዳታ ካገኘን በፍጥነት ከበሽታው እንድናለን።

መልመጃ 1.2

ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆኑ ደግሞ «ሐሰት» በማለት መልሱ።

1. የሕመም ስሜት ከተሰማን ለሰዎች መንገር የለብንም።
2. ሕመምተኛ ሰውና ጤነኛ ሰው አንድ ዓይነት ገጽታ አላቸው።
3. አካል ጉዳተኞችን መርዳት ጥሩ ሥነ ምግባር ነው።
4. በወባ በሽታ የተያዘ ሰው ምንም ዓይነት የበሽታ ምልክት አይታይበትም።
5. በሽተኛ ሰው ከሁሉም ሰው የተሻለ ማኅበራዊ ሕይወት አለው።
6. ማንኛውንም እንቅስቃሴ ለማከናወን ጤነኛ መሆን ያስፈልጋል።

ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ።

1. የጤነኛ ሰው ባህርይ ያልሆነው የትኛው ነው?

   ሀ. ጠንካራና ንቁ መሆን　　ሐ. ደስተኛ መሆን

   ለ. ደካማና ፈዛዛ መሆን　　መ. ትምህርትን በአግባቡ መከታተል

2. ከሚከተሉት አንዱ የበሽታ ምልክት ነው።

   ሀ. ሽንት መሽናት　　ሐ. ሣል

   ለ. አብዝቶ መናገር　　መ. ማፋሸግ

3. ለዓይነ ሥውራን ማድረግ ያለብን እገዛ ምንድን ነው?

   ሀ. የመኪና መንገድ እንዲያቋርጡ መርዳት

   ለ. ከማኅበራዊ ሕይወት ማግለል።

   ሐ. ፈጽሞ እንዳይንቀሳቀሱ መከላከል።

   መ. ምንም እገዛ አያስፈልጋቸውም።

4. የሕመምተኛ ሰው ባህሪ ያልሆነው የትኛው ነው?

   ሀ. ደካማና ፈዛዛ መሆን　　ሐ. መኝታ ማብዛት

   ለ. ደስታ ማጣት　　መ. ትምህርትን በንቃት መከታተል

1.3 የግል ንጽሕናችንን እንጠብቃለን

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦

- ስለ ግል ንጽሕና አጠባበቅ ጠቀሜታ ትገልጻላችሁ።
- በንፅሕና ጉድለት ምክንያት የሚመጡ የአንዳንድ በሽታዎችን ስሞች ትጠቅሳላችሁ።
- ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ በደም ንክኪ የሚተላለፍ በሽታ መሆኑን ትገልጻላችሁ።
- ተገቢ የግል ንጽሕና አጠባበቅን በተግባር ታሳያላችሁ።

ቁልፍ ቃላት

- የጤና አጠባበቅ
- የግል ንጽሕና
- የአካባቢ ንጽሕና

ሀ. የግል ንጽሕናችንን ለምን እንጠብቃለን?



ሥዕል 1.13 እጅንና ፊትን የመታጠብ ሥርዓት

ተግባር 1.3.1 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- ስለ ግል ንጽሕና ጥቅም መግለጽ

መመሪያ- በቡድን በመሆን ከታች በተሰጡት የመወያያ ጥያቄዎች መሠረት ተወያይታችሁ መልሳችሁን በጽሑፍ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

የመወያያ ጥያቄዎች

- የግል ንጽሕና ማለት ምን ማለት ነው?
- የግል ንጽሕናችንን መጠበቅ ለምን ይጠቅማል?
- ምግብ በሚዘጋጅበት ሥፍራ ምን ዓይነት ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል?
- የግል ንጽሕናችንን ባንጠብቅ ምን ጉዳት ይደርስብናል? በሌሎች ሰዎች ላይስ ምን ዓይነት ጉዳት ያስከትላል?

የጤና አጠባበቅ ማለት የግልና የአካባቢያችንን ንጽሕና በመጠበቅ ራስን ከበሽታ መከላከል ማለት ነው። የግል ንጽሕና ሲባል ዘወትር የሰውነታችንን፣ የፀጉራችንና የምንለብሳቸውን ልብሶች ንጽሕና መጠበቅ ማለት ነው። የተሟላ ጤንነት እንዲኖረን ንጽሕናችንን መጠበቅ ይኖርብናል።

የግል ንጽሕና መጠበቅ

- ራሳችንን ከበሽታ ለመከላከል ይጠቅማል።
- ንቁ ደስተኛና ጤነኛ ሆኖ ለመገኘት ያስችላል።
- ሥራችንን ከሌሎች ሰዎች ጋር በትጋት ለማከናወን ያስችለናል።

የግል ንጽሕናን አለመጠበቅ

- ሰውነት መጥፎ ጠረን እንዲኖረው ያደርጋል።
- ከሌሎች ሰዎች ጋር ተግባብቶ የመሥራት ሁኔታን ይቀንሳል።
- ለተለያዩ በሽታዎች ያጋልጣል።
- የተለያዩ ተባዮች በፀጉራችንና በልብሳችን ውስጥ እንዲፈጠሩ መንስኤ ይሆናል።

ለ. በግል ንጽሕና ጉድለት ምክንያት የሚመጡ በሽታዎች

ተግባር 1.3.2 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- ስለ ግል ንጽሕና ጠቀሜታ መግለጽ

መመሪያ- ከ3-5 ተማሪዎች በመሆን ቡድን መሥርታችሁ በመወያየት የውይይታችሁን ነጥቦች ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

የመወያያ ነጥቦች

- በግል ንጽሕና ጉድለት ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ለመምህራችሁ ዘርዝሩ።
- የግል ንጽሕናውን የማይጠብቅ ሰው የሚታይበትን ሁኔታ ግለጹ።



ሀ. የግል ንጽሕናውን የሚጠብቅ ወጣት



ለ. የግል ንጽሕናውን የማይጠብቅ ወጣት

ሥዕል 1.14 የግል ንጽሕና አያያዝ

በስዕል 1.14 ንጽሕናውን የማይጠብቀው ወጣት ንጽሕናውን ከሚጠብቀው በምን ይለያል?

የግል ንጽሕናን አለመጠበቅ ለተለያዩ በሽታዎች ይዳርጋል። በንጽሕና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎች እንደ እከክ፣ የዓይን ማዝ፣ ወስፋት፣ ኮሌራ የመሳሰሉት ናቸው። ዓይንን በቆሻሻ እጅ መንካት ለዓይን ማዝ በሽታ ይዳርጋል።

ሐ. ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ

ተግባር 1.3.3 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምንነት መግለጽ

መመሪያ- በተሰጡት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያይታችሁ የውይይታችሁን ሐሳቦች ለመምህራችሁ አቅርቡ።

የቡድን ውይይት

- ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ምንድን ነው?
- የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ መተላለፊያ መንገዶች ምን ምን ናቸው?
- አደጋ የደረሰበትና ሰውነቱ የደማ ሰው ቢያጋጥማችሁ ምን ታደርጋላችሁ?

ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ከእንግሊዝኛ (HIV/AIDS) የተወሰደ ምኅጻረ ቃል ነው። ኤድስ ኤች.አይ.ቪ በተባሉ በዓይን የማይታዩ ጥቃቅን ሕዋሳት አማካኝነት የሚመጣ በሽታ ነው። ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሰውነታችንን በተፈጥሮ በሽታን የመከላከል አቅም የሚያዳክም በሽታ ነው።

ኤች.አይ.ቪ /ኤድስ በደም ንክኪ አማካኝነት ይተላለፋል። ለምሳሌ በሽታው ያለበት ሰው ደም ወደ ጤነኛ ሰው ደም ውስጥ ሲገባ ሊተላለፍ ይችላል።

የደም ንክኪ ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ከሚተላለፍባቸው መንገዶች አንዱ ነው።

ስለዚህ

- በመጫወቻ ሥፍራ ድንገተኛ አደጋ በሚከሰትበት ጊዜ የደም ንክኪ እንዳይኖር መጠንቀቅ ያስፈልጋል።
- መርፌ፣ ምላጭና ስለታማ ነገሮችን በጋራ ከመጠቀም መቆጠብ ያስፈልጋል።

በመጫወቻ ሥፍራዎች ድንገተኛ አደጋ ሲከሰት መወሰድ ያለባቸው ጥንቃቄዎች
እጁ ወይም የሰውነቱ ክፍል የተቆረጠና የሚደማ ከሆነ የደም ፍሰቱ እንዲቀንስ የተጎዳውን አካሉን አንጋሎ እንዲይዝ መምከር፤ በባዶ እጅ ለመንካት አለመሞከር።
በአደጋ ወይም በአጋጣሚ (ህመም) የሚነስረው ሰው ሲያጋጥመን በት/ቤት ቅጥር ግቢ ከሆነ መጀመሪያ ዕርዳታ ወደሚሰጥበት ማዕከል (ወደ ቀይ መስቀል ክበብ) መውሰድ፣ በመኖሪያ አካባቢ ከሆነ ደግሞ ለትልልቅ ሰዎች በፍጥነት መንገር - የደም ንክኪ እንዳይኖር መጠንቀቅ አለብን።
- አደጋ የደረሰበት ሰው ሲያጋጥመን በፍጥነት እርዳታ እንዲያገኝ በአጠገባችን ለሚገኝ ሰው መንገር። - የደም ንክኪ እንዳይኖር መጠንቀቅ ያስፈልጋል።
- ስለታም ነገሮችን በመጫወቻ ሥፍራ ስናገኝ ፈጽሞ አለመንካትና ለመጠቀምም አለመሞከር - እንደ ምላጭ የመሳሰሉትን ስለታም ነገሮች በጋራ አለመጠቀም

የግል ንጽሕና አጠባበቅን መተግበር

ተግባር 1.3.4 ☛ **የቡድን ውይይት**


ዓላማ- ስለ ግል ንጽሕና እና አካባቢ ንጽሕና አጠባበቅ መግለጽ

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን መሥርታችሁ ከታች በተሰጡት የመወያያ ነጥቦች መሠረት ተወያዩ። ቡድኑ የተስማማባቸውን ሐሳቦችም በመጻፍ ለመምህራችሁ አቅርቡ። በመቀጠልም የግል ንጽሕና አጠባበቅን የሚያሳዩ ሁለት ሥዕሎችን በመሣል በቀለም አስውባችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

የመወያያ ጥያቄዎች

- የግል ንጽሕናችንን እንዴት እንጠብቃለን?
- የአካባቢ ንጽሕናን መጠበቅ ለምን ይጠቅማል?

በስዕል 1.15 የምታዩአቸው ሰዎች ምን እንደሚሠሩ በመመልከት ከሥዕሎቹ ሥር በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ላይ ጻፉ።



ሀ. _____ ለ. _____ ሐ. _____

ሥዕል 1.15 የግል ንጽሕና አጠባበቅ

ፊታችንንና እጆቻችንን መቼ መታጠብ እንዳለብን ለመምህራችሁ ግለጹ።

ዘወትር ጠዋት ከመኝታችን ስንነሣ ፊታችንንና እጆቻችንን በውሃና በሳሙና በሚገባ መታጠብ አለብን።

እጆቻችንን መቼ እንታጠብ?

- ከመጸዳጃ ቤት ስንመለስ
- ሕጻናትን ከመመገባችን በፊት
- ምግብ ከመመገባችን በፊትና ከተመገብን በኋላ
- ከጨዋታ ስንመለስ
- ማንኛውንም ሥራ ካጠናቀቅን በኋላና
- እንስሳትን ከነካን (ካሻሸን) በኋላ።

ዘወትር ማታ ወደ መኝታ ከመሄዳችን በፊት እግሮቻችንን መታጠብ አለብን።

ገላንና ፀጉርን መታጠብ

ስንጫወት ወይም የተለያዩ ከባድ ሥራዎችን ስንሠራ ሰውነታችንን ያልበናል። ሰውነታችንን ሲያልበን መታጠብ አለብን። ሰውነታችንን የማንታጠብ ከሆነ መጥፎ ጠረን ይፈጥራል። ገላችንን የማንታጠብ ከሆነ ሌሎች ሰዎችን ደስ የማያሰኝ ጠረን ሊፈጥርብን ይችላል። ፀጉራችንንም መታጠብና ማበጠር ያስፈልጋል። ፀጉራችን የማይበጠር ከሆነ ደግሞ ተባይ ሊፈጥር ይችላል።

የአፍን ንጽሕና መጠበቅ

- በስዕል 1.16 የምታዩት ልጅ ምን እያደረገ ነው?
- የአፍን ንጽሕና እንዴት መጠበቅ ይቻላል?



ሥዕል 1.16 የአፍ ንጽህና አጠባበቅ

ተግባር 1.3.5 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- ስለ ጥርስ ንጽሕና አስፈላጊነት መግለጽ

መመሪያ- በቡድን በመሆን በመወያያ ጥያቄዎቹ መሠረት ተወያይታችሁ የቡድናችሁን ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ።

የመወያያ ጥያቄዎች

- ጥርሳችንን ማጽዳት ያለብን መቼ ነው?
- ጥርስን አለማጽዳት ምን ችግር ያስከትላል?

ምግብ ከተመገብን በኋላ አፍን በውሃ መጉመጥመጥ ያስፈልጋል። እንዲሁም ጥርሳችንን ዘወትር ጠዋት ከመኝታ እንደተነሳን በጥርስ ቡርሽ መፋቅ ወይም በእንጨት መፋቂያ መፋቅ ያስፈልጋል።

አፋችን የማይጸዳ ከሆነ

- የአፍ ጠረን መጥፎ ይሆናል።
- ጥርሳችን ለመቦርቦር ይጋለጣል። ይህም ለከፍተኛ የጥርስ ህመም ያጋልጠናል።
- የጥርሳችን ቀለም ይቀየርና የጥርሳችንን ውበት ይቀንሳል።

የልብስ ንጽሕናን መጠበቅ

በሥዕሉ ላይ ምን ተረዳችሁ?

በሥዕል 1.17 የምታዩአቸውን ተግባራት ዘርዝሩ።



ሀ. _____ ለ. _____ ሐ. _____

ሥዕል 1.17 የልብስ ንጽህና አጠባበቅ

- ለልብሳችን ንጽሕና ምን ዓይነት ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብን ለመምህራችሁ በዝርዝር ተናገሩ።

ልብሳችንን

- በአግባቡ መልበስና በንጽሕና መያዝ፤
- በሚቆሽሽበት ጊዜ ማጠብ፤
- ተኩሰንና አጥፈን በንጹሕ ቦታ ማስቀመጥ ያስፈልጋል።

የአካባቢ ንጽሕናን መጠበቅ

ተግባር 1.3.6 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- ስለ አካባቢ ንጽሕና አጠባበቅ መግለጽ

መመሪያ- በቡድን በመሆን በመወያያ ጥያቄዎች መሠረት ተወያይታችሁ የተስማማችሁባቸውን ሐሳቦች ለመምህራችሁ አቅርቡ።

የመወያያ ጥያቄ

- የመማሪያ ክፍላችሁን ንጽሕና እንዴት መጠበቅ እንደምትችሉ ግለጹ።
- መጸዳዳት ስንፈልግ የት መፈጸም አለብን?
- አካባቢያችን እንዳይቆሽሽ ከኛ ምን ይጠበቃል? በዝርዝር ተናገሩ።



ሥዕል 1.18 አካባቢን ማጽዳት

ንጹሕ አካባቢ ለጤናችን በጣም ጠቃሚ ነው። አካባቢያችን ንጹሕ ሲሆን ደስተኞች እንሆናለን። እንዲሁም ለተለያዩ በሽታዎች አንጋለጥም።

ንጹሕ አካባቢ ለጤናችን ለኑሮአችንና ለትምህርታችን በጣም ተስማሚ ነው።

አካባቢያችን ንጹሕ እንዲሆን

- መማሪያ ክፍላችንን ማጽዳት
- ቆሻሻዎችን በቆሻሻ መጣያ ሥፍራ (በቅርጫት ውስጥ) መጣል።
- በመጸዳጃ ቤት በአግባቡ መጸዳዳት።
- የቤት እንስሳት ከሰው መኖሪያ ቤት አካባቢ ራቅ ባለ ሥፍራ እንዲኖሩ ማድረግ።

- የትምህርት ቤታችንንና የመኖሪያ አካባቢያችንን ጽዳት በጋራ መጠበቅ።
- የአካባቢያችንን አትክልቶች መንከባከብ ያስፈልጋል።

ተግባር 1.3.7 ☛ **የቡድን ሥራ**

ዓላማ- የጤና አጠባበቅ መንገዶችን በሥዕል ማሳየት

መመሪያ- በቡድን በመሆን የጤና አጠባበቅ መንገዶችን የሚያሳዩ ሥዕሎችን በመሣል በቀለም (ክለር) ካቀለማችሁ በኋላ ለመምህራችሁ አሳዩ።

መልመጃ 1.3

ሀ. የሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆኑ ደግሞ «ሐሰት» በማለት መልሱ።

1. ምግብ ተመግበን ስንጨርስ አፋችንን መጉመጥመጥ መጥፎ የአፍ ጠረን እንዳይኖረን ይረዳል።
2. ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ በመሳሳም የሚተላለፍ በሽታ ነው።
3. የግል ንጽሕናን መጠበቅ ራስን ከበሽታ ለመከላከል ይጠቅማል።
4. ድንገተኛ አደጋ የደረሰበት ሰው ሲያጋጥመን ደሙን በውሃ ማጠብ ያስፈልጋል።
5. አካባቢያችንን በጋራ ማጽዳት ስለሌሎች ሰዎች ጤንነት ኃላፊነት እንዲሰማን ያደርጋል።

ለ. በ'ሀ' ሥር የቀረቡት በ«ለ» ሥር ከቀረቡት ጋር አዛምዱ።

ሀ	ለ
_____ 1. በንጽሕና ጉድለት የሚመጣ በሽታ	ሀ. እጅን መታጠብ
_____ 2. በደም ንክኪ የሚመጣ በሽታ	ለ. እከክ፣ ዓይን ማዝ
_____ 3. ከመጸዳጃ ቤት መልስ ማድረግ ያለብን	ሐ. የግል ንጽሕና መጠበቅ
_____ 4. የሰውነት ጠረን እንዲኖር ያደርጋል።	መ. ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ
_____ 5. ለበሽታ የመጋለጥ ዕድልን ይቀንሳል።	ሠ. ገላችንን አለመታጠብ

ሐ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. የጤና አጠባበቅ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ምንድን ነው?
3. ተገቢ የግል ንጽሕና ሲባል ምን ማለት ነው?

ማጠቃለያ

በዚህ ርዕስ የሚከተሉትን ቁም ነገሮች ተምራችኋል፡፡

- ምግብ በሕይወት ለመኖር ከሚያስፈልጉ ነገሮች አንዱ ነው፡፡
- ምግብን ከእንስሳትና ከተክሎች እናገኛለን፡፡
- የገበታ ሥርዓት ምግብ በምንመገብበት ወቅት ማድረግ ያለብን ሥነ ሥርዓት ነው፡፡
- ጤና ማለት አካላዊ፣ አእምሮአዊና ማኅበራዊ ደኅንነት ማለት ነው፡፡
- የተሟላ ጤንነት ያለው ሰው ጠንካራና ጤነኛ ነው፡፡ ሕመምተኛ ሰው ግን ደካማና ፈዛዛ ነው፡፡
- ማንቀጥቀጥ፣ ራስ ምታት፣ ውጋትና ቁርጠት፣ ትኩሳት፣ ማስታወክ፣ ተቅማጥ፣ የምግብ ፍላጎት መቀነስ ዋና ዋና የሕመም ምልክቶች ናቸው፡፡
- በማንኛውም ጊዜ የሕመም ስሜት ሲሰማን ለመምህራችን፣ ለወላጆቻችን ወይም በአቅራቢያችን ለሚገኝ ሰው መንገር ይገባናል፡፡
- የግል ንጽሕናን መጠበቅ ለበሽታ የመጋለጥ ዕድልን ይቀንሳል፡፡
- እከክ፣ ወስፋት፣ ዓይን ማዝ፣ ኮሌራ ወዘተ በንጽሕና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎች ናቸው፡፡
- ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ በደም ንክኪ ይተላለፋል፡፡

ማጠቃለያ ጥያቄዎች

ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆኑ ደግሞ «ሐሰት» በማለት መልሱ።

1. የምንመገበው ምግብ ከእንስሳትና ከተክሎች ይገኛል።
2. ሕመምተኛ ሰው ንቁና ቀልጣፋ ነው።
3. ጤና አካላዊና አእምሮአዊ ደኅንነት ማለት ነው።
4. እርጎና አይብ ከአትክልት የሚመደቡ የምግብ ክፍሎች ናቸው።
5. ማንኛውም በሽታ በደም ንክኪ ይተላለፋል።

ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ።

1. ከሚከተሉት በሽታዎች ዋነኛ መንሥኤው የንጽሕና ጉድለት ያልሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. ኤች አይ ቪ/ ኤድስ — ሐ. ወስፋት
   ለ. እከክ — መ. ዓይነማዝ
2. የጤና አጠባበቅ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?
   ሀ. ጤነኛ ሆኖ ለመገኘት
   ለ. ተላላፊ በሽታን ለመከላከል
   ሐ. ትምህርታችንን በአግባቡ ለመከታተል
   መ. ሁሉም መልስ ይሆናል።
3. የኤች. አይ. ቪ/ ኤድስ መተላለፊያ መንገድ የሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. አብሮ መመገብ — ሐ. ቆሻሻ ልብስ መልበስ
   ለ. ደም ንክኪ — መ. መሳሳም
4. ከሚከተሉት ውስጥ የበሽታ ምልክት ያልሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. ሰውነትን ማሳከክ — ሐ. ትኩሳት
   ለ. ማስቀመጥ — መ. ትንታ
5. ከጥራጥሬ የምግብ ዓይነቶች የማይመደበው የቱ ነው?
   ሀ. ጥቅል ጐመን — ሐ. አተር
   ለ. ሽምብራ — መ. አደንጓሬ

ሐ. ከዚህ በታች በሚገኘው ሠንጠረዥ ውስጥ በሚገኘው ባዶ ቦታ የሚስማማውን ሥዕል ሥላችሁ ከሥሩ ስሙን ጻፉ።

ከእንስሳት የሚገኙ ምግቦች	 ሥጋ	1.	 ቅቤ	2.
ከፍራፍሬዎች የሚመደቡ የምግብ ዓይነቶች	3.	 ወይን	4.	 ፓፓያ

መ. የሚከተሉት ጥያቄ መልሱ።

1. የበሽታ ስሜት (ምልክት) ሲሰማን ምን ማድረግ አለብን?
2. በአካባቢያችሁ ከተለመዱ የምግብ ዓይነቶች ውስጥ ሦስቱን ዘርዝሩ።

ፍተሻ

የምታውቋቸውን ክንውኖች በመለየት በእያንዳንዱ ሳጥን ውስጥ ይህንን (✓) ምልክት አኑሩ።

1. የምግብን ጠቀሜታ እናገራለሁ።
2. በአካባቢያችን የተለመዱ የምግብ ዓይነቶችን ስሞች እጠራለሁ።
3. ከእንስሳትና ከተክሎች የሚገኙ የምግብ ዓይነቶችን እለያለሁ።
4. ተገቢ የአመጋገብ ሥርዓቶችን በተግባር አሳያለሁ።
5. የጤንነትን ፍቺ እሰጣለሁ።
6. በጤነኛና በህመምተኛ ሰው መካከል ያለውን ልዩነት በማነጻጸር የጤናን አስፈላጊነት አብራራለሁ።
7. አንዳንድ የሕመም ምልክቶችን እገልጻለሁ።
8. የሕመም ስሜት ሲሰማን ለሌሎች እንዴት መናገር እንዳለብን አስረዳለሁ።
9. ስለ ግል ንጽሕና ጠቀሜታ አስረዳለሁ።
10. የግል ንጽሕናን አለመጠበቅ የሚያስከትላቸውን ችግሮች እገልጻለሁ።
11. ተገቢ የግል ንጽሕና አጠባበቅን አሳያለሁ።

ምዕራፍ ሁለት

ማኅበረሰባችን

ከምዕራፉ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ይህን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የማኅበረሰባችሁን አባላት በዕድሜያቸው መሠረት ትመድባላችሁ፡፡
- በማኅበረሰባችሁ የዕድሜ ምድብ መሠረት የራሳችሁንም የዕድሜ ምድብ ትለያላችሁ፡፡
- አንዳንድ የሕጻናት መብቶችንና የመብት ጥሰት የሚገልጹ ምሳሌዎችን ትሰጣላችሁ፡፡
- የሕጻናት መብቶች እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው ሐሳብ ታቀርባላችሁ፡፡
- የየዕለት እንቅስቃሴያችሁን ማቀድን ትለማመዳላችሁ፡፡
- ራስን በራስ የመምራት ተግባርን ታሳያላችሁ፡፡
- ዕድሜያችሁ በሚፈቅደው መሠረት በአንዳንድ የማኅበረሰብ እንቅስቃሴ ውስጥ ለመሳተፍ ያላችሁን ፍላጎት በተግባር ታሳያላችሁ፡፡
- ጉልበት ለማኅበረሰባችሁ ያለውን ጠቀሜታ ትገልጻላችሁ፡፡
- የጉልበት ምንጮችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- ንድፎችን መሥራትና ቁሳቁሶችን ማያያዝ (ማገናኘት) ትለማመዳላችሁ፡፡
- ጌጣጌጦችንና ቅርጻቅርጾችን ከወረቀትና ከሸክላ ትሠራላችሁ፡፡
- ሳይንሳዊ የምርምር ክህሎቶችን ማለትም፡- መመልከትን፣ መጠየቅን፣ መመደብን፣ መለካትን፣ መግባባትን፣ መሳይ ቅርጾችን መሥራትንና ተባብሮ መሥራትን በተግባር ታሳያላችሁ፡፡

2.1. የማኅበረሰብ አባላት

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ትምህርት ከተማራችሁ በኋላ፦

- የማኅበረሰባችሁን አባላት ዕድሜያቸውን መሠረት በማድረግ ትመድባላችሁ።
- በማኅበረሰባችሁ የዕድሜ ምድብ መሠረት የራሳችሁንም የዕድሜ ምድብ ትለያላችሁ።
- አንዳንድ የሕጻናት መብቶችንና የመብቶችን ጥሰት የሚገልጹ ምሳሌዎችን ትሰጣላችሁ።
- የሕጻናት መብቶች እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው ሐሳብ ታቀርባላችሁ።
- የየእለት እንቅስቃሴያችሁን በማቀድ ትተገብራላችሁ።
- በራሳችሁ ደረጃ ራስን የመምራት ክህሎትን በተግባር ታሳያላችሁ።

ቁልፍ ቃላት

- ማኅበረሰብ
- ሕጻናት
- መብት
- የመብት ጥበቃ
- የመብት ጥሰት

ሀ. የማኅበረሰብ አባላት



ሥዕል 2.1 የማኅበረሰብ አባላት

ተግባር 2.1.1 ☛ የቡድን ሥራ

ዓላማ- የማኅበረሰብ አባላት ምንነት መለየት

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለመምህራችሁ በጽሑፍ አቅርቡ።

- ሥዕል 2.1ን በማስተዋል ተመልከቱ። ምን ተገነዘባችሁ?
- የማኅበረሰብ አባላት ማለት ምን ማለት ነው?

በሥዕል 2.1 እንደተመለከታችሁት በተለያዩ የዕድሜ ክልልና የተለያዩ ጾታ ያላቸው ሰዎች ተሰብስበዋል። እነዚህ ሰዎች በአንድ አካባቢ የሚኖሩና የተለያዩ ተግባራት የሚያከናውኑ ናቸው። በአንድ አካባቢ የሚኖሩ በተለያዩ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሰዎች የማኅበረሰብ አባላት ይባላሉ።

በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ የተሰባሰቡ አባላት ዕድሜያቸው የተለያየ ነው። ዕድሜን መሠረት በማድረግ የማኅበረሰቡን አባላት፡-

- ሕጻናት
- ጕልማሳ
- ጕረምሳ
- አዛውንት
- ኮረዳ በማለት መመደብ ይቻላል።

የማኅበረሰብ አባላት የዕድሜ ክልልን መሠረት በማድረግ በአምስት ቡድን መክፈል ይቻላል።

ሠንጠረዥ 2.1 የማኅበረሰብ አባላት

ተ.ቁ	ስያሜ	የዕድሜ ክልል
1	ሕጻን	18 ና 18 ዓመት በታች
2	ጕረምሳ/ወጣት /ለወንድ	19 - 35
3	ኮረዳ/ወጣት /ለሴት	19 - 35
4	ጕልማሳ	36 - 60
5	አዛውንት	ከ60 ዓመት በላይ

ተማሪዎች! በጕረምሳና በኮረዳ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? መልሱን ለመምህራችሁ ንገሩ።

ጐረምሳ የሚለው ስያሜ የሚያገለግለው ለወንድ ጾታ ሲሆን ኮረዳ የሚለው ደግሞ ለሴት ጾታ የሚያገለግል ስያሜ ነው።

ለ. የምንገኝበት የማኅበረሰብ ክፍል

ተግባር 2.1.2 ☛ **የቡድን ሥራ**

ዓላማ- ሰዎችን በዕድሜያቸው መሠረት በማኅበረሰብ ውስጥ መመደብ

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለመምህራችሁ በጽሑፍ አቅርቡ።

- በሥዕል 2.1 የቀረበውን በማየት የማኅበረሰብ አባላትን በዕድሜያቸው መሠረት ምን ምን ተብለው ሊመደቡ እንደሚችሉ ለመምህራችሁ በዝርዝር ተናገሩ።
- በዕድሜያችሁ መሠረት እናንተ በየትኛው የማኅበረሰብ ክፍል ውስጥ ትመደባላችሁ?
- የቤተሰባችሁን አባላት በዕድሜያቸው መሠረት በመመደብ ስንት ሰዎች በምድቡ ውስጥ እንዳሉ ተናገሩ።

የማኅበረሰብ አባላት ዕድሜን መሠረት በማድረግ ሕጻናት፣ ጎረምሶች፣ ኮረዶች፣ ጎልማሶችና አዛውንቶች ተብለው ይመደባሉ። በዚህም መሠረት እናንተ የምትገኙበት የዕድሜ ክልል ከ18 ዓመት በታች በመሆኑ ሕጻናት በመባል ትጠራላችሁ።

በሠንጠረዥ 2.1 በተመለከተው መሠረት የማኅረሰባችን አባላት የዕድሜ ሽግግር ስንመለከት፦

- ከሕጻንነት ወደ ጎረምሳነት/ኮረዳነት፣
- ከጎረምሳነት/ኮረዳነት ወደ ጎልማሳነት፣
- ከጎልማሳነት ወደ አዛውንትነት ሊሆን ይችላል።

ተግባር 2.1.3 ☛ **የግል ተግባር**

ዓላማ- ሕጻናት በቤታቸውና በማኅበረሰብ ውስጥ ሊኖራችሁ የሚችለውን ሚና መለየት

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

- በቤታችሁ ውስጥ ምን ምን ተግባራትን እንደምታከናውኑ ግለጹ።
- በምትኖሩበት ማኅበረሰብ ውስጥ ያላችሁን ሚና በዝርዝር ተናገሩ።



ሥዕል 2.2 በተለያዩ ተግባራት የተሰማሩ ሕጻናት

ሕጻናት በቤተሰባቸውና በሚኖሩበት ማኅበረሰብ ውስጥ ሊያከናውኗቸው ከሚገቡ ተግባራት መካከል ቤተሰብን ማክበር፣ ታላላቆችን ማክበር፣ ሕጻናትን በሚመለከቱ ተግባራት ላይ መሳተፍ ጠንክረው ትምህርትን መማር፣ ለማኅበረሰቡና ለሀገር ጠቃሚ ዜጋ መሆን የሚሉትን መጥቀስ ይቻላል።

ሐ. የሕጻናት መብትና ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ አደጋዎች

ተግባር 2.1.4 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- የሕጻናት መብትና የመብት ጥሰቶችን ምንነት መግለጽ

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻች አቅርቡ።

- የሕጻናት መብቶች ምንድን ናቸው?
- በሕጻናት ላይ የሚደርሱ አደጋዎችን በዝርዝር ተናገሩ።



ሥዕል 2.3 የሕጻናት መብቶች

ሕጻናት የተለያዩ መብቶች አሏቸው። ለምሳሌም፡- የቤተሰብንና የሌሎችን ፍቅርና እንክብካቤ የማግኘት፣ የመኖር፣ የማደግና ከአደጋ የመጠበቅ፣ ለዕድገታቸውና ለትምህርታቸው የሚያስፈልጋቸውን ከቤተሰባቸው የመጠየቅና የማግኘት መብቶች አሏቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ሕጻናትን የሚከተሉት አደጋዎች ሊያጋጥማቸው ይችላል።

- በቀላሉ ለተለያዩ አደጋዎች መጋለጥ ለምሳሌ፡- ሕጻናት ለመኪና አደጋ፣ ለጎርፍ፣ ለእሳት፣ ለኤሌትሪክ አደጋ ሊጋለጡ ይችላሉ።
- ለጉልበት ብዝበዛ መዳረግ
- ራሳቸውን ከጥቃት መከላከል ስለማይችሉ በአካላቸው ላይ ድብደባና ጉዳት ሊደርስባቸው ይችላል።
- በሌሎች በመታለል ከቤተሰቦቻቸውና ከአካባቢያቸው ተሰርቀው ሊወሰዱ ይችላሉ፡
- በቀላሉ ለበሽታ ሊጋለጡ ይችላሉ።

ተግባር 2.1.5 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- በሕጻናት ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችና ራስን እንዴት ከጉዳት መከላከል እንደሚቻል መግለጽ

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለመምህራችሁ በጽሑፍ አቅርቡ።

- ሕጻናት በቀላሉ ለአደጋ እንዲጋለጡ የሚያደርጋቸው ምክንያት ምንድንነው?
- ሕጻናት ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ አደጋዎች ምን ምን ናቸው?
- ሕጻናት ራሳቸውን ከአደጋ ለመከላከል ምን ማድረግ አለባቸው?

ሕጻናትን የተለያዩ አደጋዎች ሊያጋጥሟቸው ይችላሉ። ለምሳሌም፡-

- የመኪና አደጋ
- የእሳት ቃጠሎ
- በጎርፍ የመወሰድ
- መውደቅ
- በሹል ነገር መወጋት
- በስለታም ነገር መቆረጥ የመሳሰሉት በሕጻናት ላይ የሚደርሱ አደጋዎች ናቸው።

ስለዚህ ሕጻናት በመኪና መንገድ ላይ መጫወት፣ በመኪና መንገድ ላይ ሲሄዱ የግራ መስመርን ይዞ አለመሄድ፣ ለማቋረጫ ባልተፈቀደ ቦታ ማቋረጥ በአካል ላይ ጉዳት በሚያደርሱ ስለታም ነገሮች መጫወት፣ እንስሳትን መተናኮል ተገቢ ያለመሆኑን በመገንዘብ ራሳቸውን ከአደጋ መጠበቅ አለባቸው።

ሕጻናት በአዕምሮና በአካል ያልዳበሩ ስለሆኑ ራሳቸውን መከላከል አይችሉም። ስለዚህ በሌሎች ሰዎች ይታለላሉ፣ ለጉልበት ብዝበዛ ይዳረጋሉ። በተጨማሪም የበሽታ መንሥኤ (ለበሽታ የሚዳርጉ ተግባሮችን) ለይቶ ባለማወቅ ምክንያት በቀላሉ ለበሽታ ይጋለጣሉ።

መ. የሕጻናት መብቶች


ተግባር 2.1.6 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- የሕጻናትን መብትና ግዴታ መግለጽ

መመሪያ- ከ4-6 ተማሪዎች በመሆን ቡድን መሥርታችሁ በቀረቡት ጥያቄዎች ተወያይታችሁ ዋና ዋና ሐሳቦችን ለመምህራችሁ አቅርቡ።

- መብት ማለት ምን ማለት ነው?
- ሕጻናት ምን ምን መብት አላቸው?
- የሕጻናት ግዴታ ምንድን ነው?





ሥዕል 2.4 የሕጻናት መብቶች

ከሥዕል 2.4 ስለ ሕጻናት መብቶች ምንነት ምን ትረዳላችሁ?

መብት ሌሎች ሰዎች ምንም ዓይነት ተጽእኖ ሳያደርሱብን ልናከናውናቸው የሚገቡ ተግባራት ወይንም ልናገኛቸው የሚገቡ ጥቅሞች መገለጫ ነው። አንዳንድ የማኅበረሰብ አባላት የተለያዩ መብቶች አሏቸው።

ለምሳሌ፡- የሕጻናት መብቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ. የመማር መብት

ለ. ከአቅም በላይ የሆነ ሥራ ያለመሥራት

ሐ. ምግብ፣ አልባሳት የመኖሪያ ቤት የማግኘት

መ. ፍቅርና እንክብካቤ የማግኘት

ሠ. ወላጆቻቸውን የማወቅ መብት

ረ. ስምና ዜግነት/ሀገር የማግኘት መብት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የመማር መብት

ተግባር 2.1.7 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- ዋና ዋና የሕጻናት መብትን መለየት

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በዝርዝር አቅርቡ፡፡

- የሕጻናት መሠረታዊ መብቶች ምን ምን ናቸው?
- የሕጻናት መብትን ማክበር ለምን ያስፈልጋል?



ሥዕል 2.5 የሕጻናት የመማር መብት

ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ሕጻናት ትምህርት ቤት ገብተው የመማር መብት አላቸው፡፡ በሀገራችን ሕጻናት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት በነጻ የመማር መብት አላቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሕጻናት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የመማር ግዴታ አለባቸው፡፡ ሕጻናት እንክብካቤ የማግኘት መብት ጭምር አላቸው፡፡

ሕጻናት በአካልና በአዕምሮ እንዲያድጉና እንዲበስሉ እንክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባል። ለምሳሌ ወላጆች ወይንም አሳዳጊዎች ሕጻናትን ንጽሕናቸውን በመጠበቅ፣ በመመገብ፣ በጤናቸው ላይ ጉዳት እንዳይደርስባቸው በመጠበቅ የመንከባከብ ግዴታ አለባቸው።

ከአቅም በላይ ከሆነ ሥራ የመጠበቅ መብት



ሥዕል 2.6 የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ

ተግባር 2.1.8 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- ከአቅም በላይ የሆነ ሥራን ምንነትን መዘርዘር

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለመምህራችሁ በጽሑፍ አቅርቡ።

- ከሥዕል 2.6 ምን ተገነዘባችሁ?
- ለሕጻናት ከአቅም በላይ የሆኑ ሥራዎችን ዘርዝሩ።
- ሕጻናት ከአቅም በላይ የሚሠሩት ሥራ ምን ዓይነት ጉዳት ያስከትልባቸዋል?

ሕጻናት ከአቅማቸው በላይ የሆኑ ሥራዎች የለመሥራት መብት አላቸው። ከአቅም በላይ የሆኑ ሥራዎች ጉልበትን ያደክማል፣ ጤንነትን ይጎዳል፣ አካላዊና አእምሮአዊ ዕድገትን ያቀጭጫል። በትምህርት አቀባበል ላይም ተጽእኖ ያሳድራል። ስለዚህ ሕጻናት ከአቅም በላይ የሆነ ሥራ እንዲሠሩ መገደድ የለባቸውም። ሕጻናት ለረኅም ጊዜ ያለምንም ክፍያ የሚሠሩት አድካሚ ሥራ የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ይባላል።

ምግብ፣ አልባሳትና የመኖሪያ ቤት የማግኘት መብት

ተግባር 2.1.9 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- የሕጻናት መብት ምንነትን መግለፅ።

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለመምህራችሁ በጽሑፍ አቅርቡ።

- ለሕጻናት የሚደረጉ እንክብካቤዎችን ዘርዝሩ።
- ሕጻናት መሠረታዊ ፍላጎታቸውን የሚያሟሉት እንዴት ነው?



ሀ. መጠለያ ያላቸው ሕጻናት



ለ. መጠለያ የሌላት ሕጻን

ሥዕል 2.7 መጠለያ የላቸውና የሌላቸው ሕጻናት

ሰዎች ለመኖር መሠረታዊ ፍላጐቶች አሏቸው። ሕጻናት ለዕድገታቸው አስፈላጊና ወሳኝ መሠረታዊ ፍላጎታቸውን የማግኘት መብት አላቸው። ስለዚህ ወላጆቻቸው ወይንም አሳዳጊዎቻቸው ምግብ፣ አልባሳትና መጠለያ እንዲያገኙ በማድረግ ይንከባከቧቸዋል። ሕጻናትም ለመኖርና ለዕድገት እነዚህን መሠረታዊ ፍላጐቶች የማግኘት መብት አላቸው።

በተጨማሪም ሕጻናት ፍቅርንና እንክብካቤ ይፈልጋሉ። መሠረታዊ ፍላጎታቸው የተሟላላቸው፣ፍቅርና እንክብካቤ የተሰጣቸው ሕጻናት ጠንካራና ውጤታማ ይሆናሉ። ለቤተሰባቸውና ለሀገራቸው ጠቃሚ ዜጎች ይሆናሉ። ስለዚህም የሕጻናትን መሠረታዊ ፍላጎት ማሟላት የወላጆች ወይንም የአሳዳጊዎች ግዴታ ነው።

ስም የማግኘትና የመማር መብት

ተግባር 2.1.10 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- የትምህርትን ጥቅም መግለጽ

መመሪያ- ከ4-6 ተማሪዎች በመሆን ቡድን መሥርታችሁ በቀረቡት ጥያቄዎች መሠረት ተወያይታችሁ መልሳችሁን ለክፍላችሁ ተማሪዎች አቅርቡ።

- የትምህርት ጥቅም ምንድን ነው?
- የትምህርት ዕድል ማግኘት የምትችሉት እንዴት ነው?

ሕጻናት ከተወለዱበት ጊዜ ጀምሮ መጠሪያ ስም የማግኘት መብት አላቸው። ስለዚህ በትምህርት ቤትና በሕክምና ተቋማት ስማቸው ይመዘገባል፣ በስማቸው ይታወቃሉ፣ በስማቸው ይጠራሉ።

ሁሉም ሕጻናት ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ወደ ትምህርት ቤት ገብተው የመማር መብት አላቸው። ወላጆች ወይንም አሳዳጊዎች ልጆቻቸውን የማስተማር ግዴታ አለባቸው። የሀገራቸው መንግሥት ደግሞ ትምህርት ቤቶችን በመክፈትና አስፈላጊውን ቁሳቁስ በማሟላትና መምህራንን በመመደብ ለሕጻናት ነጻ የትምህርት ዕድል የመስጠት ግዴታ አለበት። ሕጻናት በአካባቢያቸው በሚገኙ የትምህርት ተቋማት በነጻ የመማር መብት አላቸው። ትምህርት ሕይወትን ለመለወጥ፣ ሀገርን ለማሳደግና ችግርን ለመፍታት ይጠቅማል። ስለዚህም ሕጻናት ነገ የተሻለ ሕይወት እንዲኖራቸውና ለሀገራቸው አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ የመማር ግዴታም አለባቸው።

ሕጻናት ከመብቶቻቸው አንጻር ሊያከናውኗቸው የሚገቡ የተለያዩ ግዴታዎችም አሉባቸው። ለምሳሌ ያህል ሁላችሁም፦

- ወላጆቻችሁን፣ ታላላቆቻችሁንና ጓደኞቻችሁን ማክበር አለባችሁ።
- የትምህርት ቤታችሁን ደንብ ማክበር ይጠበቅባችኋል።
- በትምህርት ቤታችሁና በቤታችሁ የተሰጣችሁን የሥራ ድርሻ በወቅቱ የማከናወን ኃላፊነት አለባችሁ።
- የመማሪያ መጽሐፎቻችሁን፣ ደብተሮቻችሁን፣ እስክሪብቶና እርሳሳችሁን በጥንቃቄና በንጽሕና መያዝ አለባችሁ።
- በአካባቢያችሁ የሚገኙ እጽዋትንና እንስሳትን የመንከባከብ ግዴታ አለባችሁ።
- በመኪና መንገድ ላይና በሌሎች አካባቢዎችም አደጋ እንዳይደርስባችሁ በጥንቃቄ የመንቀሳቀስና የመጫወት ግዴታ አለባችሁ።

የሕጻናት መብት ጥሰት

ተግባር 2.1.11 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- የሕጻናት መብት ጥሰት ምንነትን መግለጽ

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለመምህራችሁ በጽሑፍ አቅርቡ፡፡

- የሕጻናት መብት ጥሰት ምንድን ነው?
- የሕጻናት መብት ጥሰት መገለጫዎች ምንድን ናቸው?

የሕጻናት መብት ጥሰት ለሕጻናት የተሰጡ መብቶችን በማወቅ ወይንም ባለማወቅ ወይንም በቸልተኝነት አለማክበር ነው፡፡ በሕጻናት ላይ የሚደርስ የመብት ጥሰት በሕጻናት አእምሮአዊ፣ አካላዊና ሥነ ልቡናዊ ዕድገት ላይ ተጽእኖ ያደርሳል፡፡ የሕጻናት መብት ጥሰት በሕጻናት ሕይወት ላይ የአጭር ወይንም የረዥም ጊዜ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፡፡ ስለዚህም ሕጻናት በአካባቢያቸው በሚገኙ ሰዎች የመብት ጥሰት እንዳይደርስባቸው መብታቸውንና ግዴታቸውን ለይተው ማወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ቀጥሎ የቀረቡትን ሥዕሎች በመመልከትና አጫጭር ታሪኮችን በማንበብ በሕጻናቱ ላይ የደረሰውን የመብት ጥሰት ዓይነት ለመናገር ሞክሩ፡፡

ለምሳሌ፡- ሕጻናትን ከአቅም በላይ የሆነ ሥራ በማሠራት የጉልበት ብዝበዛ መፈጸም፣ ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ሕጻናትን ወደ ትምህርት ቤት አለመላክ የሕጻናት መብት ጥሰት ናቸው፡፡

ሕጻናት በቤተሰብ ወይንም በአሳዳጊዎቻቸው እንዲሁም በአካባቢው በሚገኙ ሰዎች በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ወይንም በቸልተኝነት አካላዊ፣ ስሜታዊና ማኅበራዊ ተጽእኖ የሚያደርስ የመብት ጥሰት ሊገጥማቸው ይችላል፡፡ በሕጻናት ላይ አካላዊ፣ ስሜታዊና ማኅበራዊ ተጽእኖ የሚያደርስ ጉዳት ሲደርስ ሕጻናት መብታቸው ተጣሰ ይባላል፡፡

በሕጻናት ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችና የመብት ጥሰቶች መገለጫዎች

- ሕጻናት ምግብ እንዳይበሉ መከልከል ወይንም ማስራብ፣
- ድካምና ሕመም የሚያስከትሉ ሥራዎችን ማሠራት፣
- ተገቢ ባልሆነ ንግግር እንዲጨነቁ፣ እንዲረበሹና በፍርሃት እንዲዋጡ ማድረግ፣
- ሕጻናትን ማንገላጠጥና ማዋረድ፣
- መደብደብ፣

- ልብሳቸውን አስወልቆ ጓደኞቻቸው እንዲስቁባቸው ማድረግና ሌሎችም ጭካኔና ሰብአዊነት የማይታይባቸው ቅጣቶች በሕጻናት ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችንና የመብት ጥሰቶችን ያሳያሉ፡፡

ተማሪዎች! ቀጥሎ የቀረቡትን ሥዕሎች በመመልከት በሕጻናቱ ላይ ምን ምን ዓይነት የመብት ጥሰት እንደደረሰ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡



በሥዕሉ የሚታየው ምንድን ነው? በሕጻናቱ ላይ ምን ዓይነት የመብት ጥሰት እየደረሰ ነው?



ሥዕሉ ምንን ያሳያል? በሕጻናቱ ላይ ምን ዓይነት የመብት ጥሰት እየደረሰ ነው?



ከሥዕሉ ምን ተመለከታችሁ? በሕጻናቱ ላይ እየደረሰ ያለው ምን ዓይነት የመብት ጥሰት ነው?

ሥዕል 2.8 የሕጻናት መብት ጥሰት መገለጫዎች

ተግባር 2.1.12 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ፡- የሕጻናት መብት ጥሰት መገለጫዎችን መለየት

መመሪያ፡- አምስት በሚደርሱ አባላት ቡድን መሥርታችሁ ቀጥሎ በሚቀርቡት ገጠመኞችና ተያይዘው በቀረቡ ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።

- በውይይታችሁ የተነሡ ፍሬ ሐሳቦችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በጽሑፍ አቅርቡ።

የማሙሽ ገጠመኝ

ማሙሽ የሁለተኛ ክፍል ተማሪ ነው። አንድ ቀን ወደ ትምህርት ቤት ሲሄድ መንገድ ላይ ያገኙት የሠፈር ልጆች የያዘውን የምሳ ዕቃ ቀምተው ይበሉበታል። ማሙሽም እያለቀሰ ምሳውን እንዳይበሉበት ለመናቸው ልጆቹ ግን "ከዚህ ጥፋ።" በማለት ደበደቡት። የምሳ መያዣውን እንዲሰጡት ሲለምናቸው ሱሪውን አስወልቀው የአካባቢው ሕጻናትና ጓደኞቹ እንዲስቁበት አደረጉ። ማሙሽም እያለቀሰ ወደ ቤቱ ተመለሰ።

የመወያያ ጥያቄዎች

ተማሪዎች! ከማሙሽ ታሪክ ምን ተማራችሁ? በማሙሽ ላይ ምን ዓይነት የመብት ጥሰት የተፈጸመ ይመስላችኋል? ማሙሽ መብቱን ለማስከበር ምን ምን ማድረግ አለበት?

የማሚት ገጠመኝ

ማሚት የሁለተኛ ክፍል ተማሪ ናት። አንድ ቀን እናቷ ከትምህርት ቤት ቀርታ በቤት ውስጥ ሥራ አንድትሠራ አደረጉ። ከዚያ በኋላም ማሚት ትምህርቷን አቋርጣ ጉልት እንድትሸጥ አደረጉ። ማሚት ትምህርቷን ለመቀጠል ብትፈልግም እናቷ ፈቃደኛ አልሆኑም። በመጨረሻም እናቷ ከጎረቤታቸው የተበደሩትን ገንዘብ መመለስ ስላልቻሉ ማሚት ወደ ጎረቤታቸው ቤት ሄዳ ያለምንም ክፍያ ሥራ እንድትሠራና የተበደሩት ገንዘብ እንዲቀርላቸው አደረጉ። ማሚትም ተገዳ ወደ ጎረቤታቸው ቤት ሄደች።

የመወያያ ጥያቄዎች

ተማሪዎች! ከማሚት ታሪክ ምን ተማራችሁ? በማሚት ላይ ምን ዓይነት የመብት ጥሰት የተፈጸመ ይመስላችኋል? ማሚት መብቷን ለማስከበር ምን ማድረግ ነበረባት?

ተማሪዎች! በሕጻናት ላይ የሚደርሱ የመብት ጥሰቶች በሕጻናት አካላዊ፣ አእምሮአዊና ማኅበራዊ እድገት ላይ ተጽእኖ ያስከትላሉ።

- ሕጻናትን ልብስ አስወልቆ መደብደብ፣ ጓደኞቻቸው እንዲስቁባቸው ማድረግ ሰብአዊ ክብርን ይቀንሳል።
- ድብደባ አካላዊ ጉዳት ያስከትላል።
- ለሕጻናት ፍላጎት ምላሽ መንፈግ፣ ጸያፍ ቃላትና ስድብ የሕጻናትን ሥነ ልቡና ይጎዳል።

በሕጻናት ላይ ከሚደርሱ የመብት ጥሰቶችና አደጋዎች ማምለጫ ዘዴዎች

- በትምህርት ቤት አካባቢና በመንገድ ላይ ስትጫወቱ ሰዎች የማትፈልጉትን ነገር እንድታደርጉ ሲጠይቋችሁ "እምቢ" በማለት ተቃውሟችሁን መግለጽ
- ሌሎች ሰዎች ሊነኩባችሁ የማይገቡ የሰውነት ክፍሎቻችሁን እንዳይነኩባችሁ መከላከል
- ሌሎች ሰዎች ሊነኩባችሁ የማይገቡ የሰውነት ክፍሎቻችሁን ሰዎች በኃይል ከነኩባችሁ ደግሞ የደረሰባችሁን ነገር በግልጽ ለቤተሰቦቻችሁ ወይንም ለመምህራን መንገር
- በመንገድ ላይ ችግር ሲያጋጥማችሁ በአካባቢያችሁ የሚገኙ የፖሊስ አባላት ወይንም ትላልቅ ሰዎች እንዲረዷችሁ መጮህ
- አስፈሪ በሆኑና ለአደጋ ሊያጋልጡ በሚችሉ ጭር ባሉና በቀላሉ በማይታዩ ሥፍራዎች አለመጫወት ወይንም አለመቀመጥ

- የተለያዩ ሰዎች የተለያዩ ማባበያዎችን በመስጠት ወይንም በመኪና ወደማታውቁት ሥፍራ ወይንም ወደማታውቁት ቤት ሊወስዷችሁ ሲጠይቋችሁ ፈቃደኛ ያለመሆን
- አደጋ ሲያጋጥማችሁ በቀላሉ እርዳታ ማግኘት እንድትችሉ የቤተሰቦቻችሁንና በአካባቢያችሁ የሚገኝ የፖሊስ ጣቢያን ስልክ ቁጥሮች በቃላችሁ ማጥናትና ችግር ሲገጥማችሁ ደውላችሁ ማሳወቅ

የሕጻናት መብቶች ጥበቃ

ተግባር 2.1.13 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- በሕጻናት ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን እንዴት መከላከል እንደሚቻል መግለጽ።

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ሐሳብ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

- ሕጻናት በቤታቸውና በማኅበረሰቡ ውስጥ ጥቃት እንዳይፈጸምባቸው ምን ምን መደረግ አለበት?
- ሕጻናት የመብት ጥሰት እንዳይደርስባቸው ምን ምን እርምጃዎች መውሰድ አለባቸው?

ሕጻናት በወላጆቻቸው ወይም በአሳዳጊዎቻቸው እንዲሁም በማኅበረሰቡ አባላት የተለያዩ የመብት ጥሰት ሊያጋጥማቸው ይችላል። ለምሳሌ ጭካኔ በተሞላበትና ርኅራኄ በጎደለው መንገድ የሚፈጸም አካላዊ ጥቃት፣ ስድብ፣ ከአቅም በላይ የጉልበት ሥራ መሥራት፣ ምግብ መከልከል፣ ያለእረፍት መሥራት፣ ልብስ አስወልቆ መግረፍ፣ በሰዎች ፊት ራቁት ማስቆም፣ መሳቂያ ማድረግና ለፍላጎታቸው ተገቢ ምላሽ አለመስጠት በሕጻናት ላይ የሚደርስ የመብት ጥሰት መገለጫዎች ናቸው።

መልመጃ 2.1

ሀ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

1. የማኅበረሰብ አባላትን በዕድሜያቸው መሠረት መመደብ አይቻልም።
2. መብት አንድ ሰው በነጻነት የሚያከናውናቸውን ተግባራት ይገልጻል።
3. ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሰ ሕጻናት ሁሉ የመማር መብት አላቸው።
4. ሕጻናትን ማንኛውንም ዓይነት ሥራ ማሠራት ተገቢ ነው።
5. ጥፋት የፈጸሙ ሕጻናትን ከባድ የጉልበት ሥራ በማሠራት መቅጣት ያስፈልጋል።

ሰ. በ"ሀ"ሥር የቀረቡትን በ"ለ" ሥር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምዱ።

'ሀ'	'ለ'
1. የማኅበረሰብ አባል	ሀ. የመማሪያ ቁሳቁሶችን በንጽሕና መጠበቅ
2. የሕጻናት ግዴታ	ለ. ጎልማሳ
3. የሕጻናት መብት	ሐ. የቤተሰብ ምክርን አለመቀበል
	መ. መጠሪያ ስም ማግኘት
	ሠ. አካላዊ ድብደባ

ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።

1. ዕድሜን መሠረት በማድረግ ትክክለኛ ያልሆነው አመዳደብ የትኛው ነው?

ሀ. ሕጻን ሐ. ጨቅላ

ለ. ጎረምሳ መ. አዛውንት

2. የሕጻናት ግዴታ ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ቤተሰቦቻቸውን ማክበር

ለ. ከአቅም በላይ የጉልበት ሥራ መሥራት

ሐ. በአካባቢያቸው የሚገኙ ዕጽዋትን መንከባከብ

መ. የትምህርት ቤት ደንብን ማክበር

3. የሕጻናት መብት ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ነጻ የትምህርት ዕድል ማግኘት ሐ. መሠረታዊ ፍላጎት ማግኘት

ለ. በመኪና መንገድ ላይ መጫወት መ. መጠሪያ ስም ማግኘት

4. የሕጻናት መብት ጥሰት መገለጫ ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ሕጻናትን ልብስ አስወልቆ ማሳፈር ሐ. ድብደባ

ለ. ለሕጻናት ፍላጎት ምላሽ መንፈግ መ. ፍቅርን መስጠት

መ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. ሕጻናት አደጋ እንዳይደርስባቸው ምን ምን ዓይነት ጥንቃቄ መወሰድ እንደሚገባቸው አብራሩ።
2. ሕጻናትን ሊጋጥሟቸው የሚችሉ የአደጋ ዓይነቶችን ዘርዝሩ።

2.2 በማኅበረሰብ ውስጥ መኖር

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦

- የየዕለት እንቅስቃሴያችሁን ማቀድ ትለማመዳላችሁ።
- ራስን በራስ የመምራት ተግባር ታሳያላችሁ።
- ዕድሜያችሁ በሚፈቅደው መሠረት በአንዳንድ የማኅበረሰብ እንቅስቃሴ ውስጥ ለመሳተፍ ያላችሁን ፍላጎት በተግባር ታሳያላችሁ።

ቁልፍ ቃላት

- ዕቅድ
- ራስን በራስ መምራት
- ተሳትፎ

1. የየዕለት እንቅስቃሴዎችን ማቀድ

ሀ. የቀን እቅድ ማዘጋጀት



ልጆቹ ምን እያደረጉ ነው?





በሥዕሉ የሚታየው ምንድን ነው?



ልጁ ምን እያደረገ ነው?

ሥዕል 2.9 በተለያዩ ተግባራት ላይ የተሰማሩ ሕጻናት

ተግባር 2.2.1. ☛ የቡድን ሥራ

ዓላማ- ስለዕለት እንቅስቃሴ ምንነት ማብራራት

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለመምህራችሁ በጽሑፍ አቅርቡ።

- የዕለት እንቅስቃሴ ምንድን ነው?
- በየዕለቱ ምን ምን ዓይነት እንቅስቃሴዎችን ታደርጋላችሁ?

አንድ ሰው በቀን ውስጥ ለማንኛውም ውጤት ላለው ተግባር የሚያደርገው እንቅስቃሴ የዕለት እንቅስቃሴ ይባላል። ተማሪዎች በየዕለቱ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ታደርጋላችሁ። **ለምሳሌ**፦ በዕለቱ ምግብ መመገብ፣ ጥናት ማጥናት፣ በግል ወይንም በቡድን መጫወት፣ የቤት ሥራ መሥራት፣ እንቅልፍ መተኛት የመሳሰሉትን ይጠቀሳሉ። የተለያዩ ተግባራትን በቅደም ተከተል ለማከናወን ደግሞ የዕለት ወይንም የቀን እቅድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። የዕለት እቅድን ለማዘጋጀት የምናከናውናቸውን ተግባራት በመዘርዘር ዕለቱን በሰዓት በመከፋፈል በወረቀት ላይ ማስፈር ተገቢ ነው።

የቀን እቅድን በተለያዩ መንገዶች ማዘጋጀት ይችላል። ለምሳሌ ያህልም የሁለተኛ ክፍል ተማሪ የሆነችው ማሚት የሠራችውን የዕለት እቅድ ትመለከታላችሁ።

ሠንጠረዥ 2.2 የእስት እቅድ

ተ.ቁ	በዕለቱ የሚከናወኑ ተግባራት	የጊዜ ሰሌዳ
1	ከመኝታ መነሣት	ከንጋቱ 12፡30
2	ወደ ትምህርት ቤት መሄድ	ከጥዋቱ 1፡45
3	የትምህርት ሰዓት	ከጥዋቱ 2፡00- እስከ ቀኑ 9፡30
4	መክሰስ መብላት	ከቀኑ 9፡35 እስከ ቀኑ 10፡00
5	ዕረፍት ማድረግና መጫወት	ከቀኑ 10፡05 እስከ ቀኑ 11፡00
6	ማጥናት	ከቀኑ 11፡05 እስከ ምሽቱ 2፡00
7	ቴሌቪዥን መመልከት	ከምሽቱ 2፡00 እስከ ምሽቱ 3፡00
8	የመኝታ ሰዓት	ከምሽቱ 3፡00 እስከ ንጋቱ 12፡30

ተግባር 2.2.2 ☛ **የግል ሥራ**

ዓላማ- የዕለት እቅድ ማዘጋጀት

መመሪያ-

- የዕለት እንቅስቃሴያችሁን የጊዜ ሰሌዳ በማዘጋጀት ለመምህራችሁ በጽሑፍ አቅርቡ።

ለ. የሳምንት እቅድ ማዘጋጀት

የሳምንት እቅድ ማለት በየዕለቱ የምናደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች ለማከናወን በሳምንቱ ውስጥ ባሉ ቀናት ተግባራቱን ከፋፍሎ ማስቀመጥና በዚሁ መሠረት ማከናወን ነው።



ሥዕል 2.10 ተማሪዎች የሳምንት እቅድ ሲያዘጋጁ

ተግባር 2.2.3 ☛ **የቡድን ሥራ**

ዓላማ- የእቅድን ምንነት መረዳት

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

- የሳምንት እቅድ ምንድን ነው?
- የእቅድ ጥቅም ምንድን ነው?

እቅድ ሥራችንን በተገቢው ጊዜና ሁኔታ እንድናከናውን ይረዳናል። የሳምንት እቅድ ደግሞ በሳምንት ውስጥ ልናከናውን የምናስባቸውን ተግባራት በአንድ ሳምንት ውስጥ ላሉ ቀናት በመከፋፈል ተግባራችንን እንድናከናውን ይረዳናል።

ለእያንዳንዱ ማከናወን ለሚገባን እንቅስቃሴ በቂ ጊዜ መስጠት እንድንችል ቀኑን ወይንም ሳምንቱን በመከፋፈል የጊዜ ሰሌዳ አዘጋጅተን መጠቀም ይኖርብናል።

ተግባር 2.2.4 ☛ **የቡድን ሥራ**

ዓላማ- ሳምንታዊ እቅድ የማዘጋጀት ክህሎትን ማዳበርና ማዘጋጀት

መመሪያ-

- አምስት አባላት ያሉትን ቡድን በመመሥረት ሳምንታዊ እቅድ አዘጋጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በጽሑፍ አቅርቡ።

ሠንጠረዥ 2.3 የየዕለቱ ተግባራዊ ክንዋኔዎች

ቀናት	ሰኞ	ማክሰኞ	ረቡዕ	ሐሙስ	ዓርብ	ቅዳሜ	እሑድ
ተግባራዊ ክንዋኔ							

ተግባር 2.2.5 ✒ የግል ሥራ

ዓላማ- ዕለታዊ እቅድ የማዘጋጀት ክህሎትን ማዳበር


መመሪያ-

- ቀጥሎ "የኔ ቀን" በሚለው ርዕስ ሥር ሰዓትና የሚከናወኑ ሥራዎች በሠንጠረዥ ቀርበዋል። ሰዓታቱን በየዕለቱ ከምታከናውኑት ተግባር ጋር አዛምዱ።
- የቀን እቅድ ማዘጋጃ የጊዜ ሰሌዳ በመሥራት የየራሳችሁን የቀን እቅድ አዘጋጁ።

"የኔ ቀን"

	ጠዋት 12 ሰዓት	ጠዋት 1 ሰዓት	ጠዋት 2 ሰዓት	3 ሰዓት	ጠዋት 4 ሰዓት	5 ሰዓት	እኩለ ቀን 6 ሰዓት	ቀን 7 ሰዓት	ቀን 8 ሰዓት	ከቀኑ 9 ሰዓት እስከ ቀኑ 12 ሰዓት	ምሽት
ከእንቅልፍ መነሳ											
ቁርስ መመገቢያ											
ወደ ትምህርት ቤት መሄድ											
ጨዋታ											
ፕናት											

2. ራስን የመምራት ክህሎት





ሥዕል 2.11 ራስን የመምራት ክህሎት

ተግባር 2.2.6 ☛ የቡድን ሥራ

ዓላማ- ራስን የመምራት ምንነትን በመገንዘብ በተግባር መለማመድ።

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለመምህራችሁ በጽሑፍ አቅርቡ።

- ራስን የመምራት ክህሎት በትምህርት ቤት እንዴት ይገለጻል?
- በቡድን ጨዋታ ወቅት ሊኖረን የሚገባው ራስን የመምራት ክህሎት መገለጫ ምንድን ነው?

ራስን የመምራት ክህሎት ጊዜያችንንና ተግባራችንን በእቅድና በሥርዓት ወስኖ የመኖር ክህሎት ነው። ራስን መምራት ማለት ማከናወን የሚገባንን ማንኛውንም ተግባር በተያዘው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ራስን ችሎ በአግባቡ ማከናወን ነው። ራስን መምራት ማለት ሥነ ሥርዓት ማክበር ማለት ነው። ተማሪዎች ሥነ ሥርዓት የማክበር ክህሎትን ከሚያዳብሩባቸው ቦታዎች መካከል

ሀ. ትምህርት ቤት

ለ. የመማሪያ ክፍል

ሐ. የቡድን ጨዋታ በዋናነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

ሀ. በትምህርት ቤት



ሥዕል 2.12

ሀ. በሥዕሉ የምታዩአቸው ተማሪዎች ምን እያደረጉ ነው?

ለ. ከዚህ ሥዕል በተማሪዎች የሚታየው የምን ክህሎት ነው?

በትምህርት ቤት አለማርፈድ፣ የደንብ ልብስ በአግባቡ መልበስ፣ ከሌሎች አለመጣላት ራስን የመምራት ክህሎቶች መገለጫ ናቸው።

ሰ. በክፍል ውስጥ



ሥዕል2.13 በክፍል ውስጥ ራስን የመምራት ክህሎት

የትምህርት መሣሪያ ይዞ መገኘት፣ የቤት ሥራ መሥራት፣ ጥያቄ መመለስ፣ አለመረበሽና የመሳሰሉት በክፍል ውስጥ የሚታዩ ራስን የመምራት ክህሎት መገለጫዎች ናቸው።

ሐ. በቡድን ጨዋታ



ሥዕል 2.14 የቡድን ጨዋታ

በቡድን ጨዋታ ወቅት አለመሳደብ፣ ተራን ጠብቆ መጫወት፣ ሽንፈትን መቀበል ራስን የመምራት ክህሎት መገለጫዎች ናቸው።

ራሱን የመምራት ክህሎት ያዳበረ ተማሪ ጊዜውን፣ ገንዘቡንና ጉልበቱን በአግባቡ ይጠቀማል።

ራሱን መምራት የሚችል ተማሪ፡-

- የትምህርት ሰዓቱን ያከብራል፤
- ለጥናት፣ ለጨዋታና ቤተሰቡን ለማገዝ ሰዓት ይመድባል፤
- የመኝታ ሰዓቱን ያከብራል፤
- ጎበዝ ተማሪም ይሆናል።

ተግባር 2.2.7 ☛ የግል ሥራ

ዓላማ- ራስን የመምራት ክህሎት መገለጫዎችን መለየት

መመሪያ- ቀጥሎ የተዘረዘሩትን የአራት ተማሪዎች ጠባይ በማጥናት ለጥያቄዎቹ ትክክለኛውን መልስ ስጡ።

	የተማሪው ስም	የተማሪው መገለጫ
1	ሕሊና	ብዙ ስለማትጫወት አይደክማትም። ስለዚህ ለማጥናት በቂ ጉልበት አላት። ነገር ግን እቅድ የላትም።
2	ወርቅነሽ	በየቀኑ የመጫወቻ፣ የጥናት፣ የዕረፍትና ቤተሰቧን የምትረዳበት እቅድ አላት። ስለዚህም ጎበዝና ደስተኛ ናት።
3	አድናን	በዕረፍት ሰዓቱ በሙሉ ኳስ ስለሚጫወትና ስለሚደክመው ማጥናት አይችልም። ስለዚህም ይተኛል።
4	ቢራቱ	ደብተሩን ይጥላል፣ እርሳሱንም በአግባቡ አይጠቀምም፣ የደንብ ልብሱንም አሟልቶ አይለብስም።

ተማሪዎች!

1. ራስን የመምራት ክህሎት በትክክል ያዳበረው የትኛው ተማሪ ነው?
2. ራስን የመምራት ክህሎት በትክክል ያላዳበረው ማነው?
3. ጊዜውን በአግባቡ የሚጠቀመው ማን ነው?
4. እናንተ ማንን መምሰል ትፈልጋላችሁ? ለምን?

3. በማኅበረሰብ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍ



ሥዕል 2.15 ተማሪዎች በማኅበረሰብ እንቅስቃሴ ውስጥ ሲሳተፉ

ተግባር 2.2.8 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- የማኅበረሰብን ትርጉም ማስረዳት

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለመምህራችሁ በጽሑፍ አቅርቡ፡፡

- የትምህርት ቤት ማኅበረሰብ አባላትን ዘርዝሩ፡፡
- በትምህርት ቤት በማኅበረሰብ ውስጥ የሚካሄዱ ተግባራትን በመዘርዘር ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

በትምህርት ቤት ውስጥ የትምህርት ቤት ማኅበረሰብ ይገኛል፡፡ የትምህርት ቤት ማኅበረሰብ አባላት የሚባሉት ተማሪዎች፣ መምህራን፣ የትምህርት ቤት ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች ናቸው፡፡ በከተማችንም የተለያዩ ማኅበረሰቦች ይገኛሉ፡፡ የአካባቢ ማኅበረሰብ፣ የወረዳው ማኅበረሰብ፣ የክፍለ ከተማው ማኅበረሰብ ተብለው ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

ማኅበረሰብ የግለሰቦች ስብስብ ነው፡፡ ግለሰቦች በየጊዜው የሚያደርጓቸው ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ወደ ቡድን ሥራ መሸጋገር አለባቸው፡፡ የቡድን ሥራዎች ደግሞ በተደራጀ መልኩ በየሳምንቱ ወይንም በየወሩ በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚካሄዱ ተግባራትን የሚያግዙ

ሊሆኑ ይገባል። በማኅበረሰብ ውስጥ ከሚካሄዱ ተግባራት መካከል የአካባቢ ጽዳት፣ የችግኝ ተከላ፣ አቅም የሌላቸውን የመደገፍና የመንከባከብ ተግባራት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

ሀ. በክበባት ውስጥ መሳተፍ

ተግባር 2.2.9 ☛ የቡድን ሥራ

ዓላማ- የክበባትን ጠቀሜታ መግለጽ

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለመምህራችሁ በጽሑፍ አቅርቡ።

- በትምህርት ቤት ውስጥ የሚቋቋሙ ክበቦች ጠቀሜታ ምንድን ነው?
- በትምህርት ቤታችሁ ተሳትፎ የምታደርጉባቸውን ክበባት ስም ግለጹ።
- ለክበባችሁ እንቅስቃሴዎች የሳምንት እቅድ አዘጋጁ።

በትምህርት ቤት ውስጥ ተማሪዎች የሚሳተፉባቸው በርካታ ክበባት ሊቋቋሙ ይችላሉ። ክበባት በተማሪዎች ተሳትፎና ፍላጎት የሚቋቋሙና ለትምህርታቸውም አጋዥ ናቸው። ለምሳሌ ፀረ ኤድስ ክበብ፣ የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ክበብ፣ የልጃገረዶች ክበብ የመሳሰሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ። ተማሪዎችም በሚፈልጉት ክበብ ውስጥ ገብተው መሳተፍ ይችላሉ።

መልመጃ 2.2

ሀ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

1. የዕለት ተግባራትን በቅደም ተከተል ለማከናወን የዕለት እቅድ ማዘጋጀት አያስፈልግም።
2. በእቅድ መጠቀም ለእያንዳንዱ ተግባር በቂ ጊዜ ለመስጠት ያስችላል።
3. ራሱን የመምራት ክህሎት ማዳበር ጊዜ፣ ገንዘብና፣ ጉልበት በአግባቡ ለመጠቀም ይረዳል።

ለ. በ"ሀ" ሥር የቀረቡትን በ"ለ" ሥር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምዱ።

ሀ	ለ
1. የዕለት እንቅስቃሴ	ሀ. አለማርፈድ
2. በእቅድ መመራት	ለ. ተማሪ
3. የትምህርት ቤት ማኅበረሰብ አባል	ሐ. በክፍል ውስጥ መረበሽ
	መ. ምግብ መመገብ

ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።

1. ራስን የመምራት ክህሎትን የማያሳየው የትኛው ተግባር ነው?
   ሀ. በእቅድና በሥርዓት የመኖር ክህሎትን ማዳበር
   ሐ. ሥነ ሥርዓት አለማክበር
   ለ. ተግባርን በጊዜ መሠረት ማከናወን
   መ. በክበባት ውስጥ መሳተፍ
2. በቡድን ጨዋታ ወቅት ተገቢ ያልሆነው ባሕርይ የትኛው ነው?
   ሀ. አለመሳደብ
   ሐ. ሽንፈትን መቀበል
   ለ. ተራን ጠብቆ አለመጫወት
   መ. መከባበር
3. ራሱን መምራት የሚችል ተማሪ ተግባር የትኛው ነው?
   ሀ. የትምህርት ሰዓትን ማክበር
   ለ. ለጥናት፣ ለጨዋታና ቤተሰቡን ለማገዝ ሰዓት መመደብ
   ሐ. የመኝታ ሰዓቱን ማክበር
   መ. ሁሉም ትክክል ናቸው
4. በማኅበረሰብ ውስጥ ከሚካሄዱ ተግባራት መካከል የማይካተተው የትኛው ነው?
   ሀ. የአካባቢ ጽዳት
   ሐ. የችግኝ ተከላ
   ለ. የቡድን ጸብ
   መ. አቅም የሌላቸውን መደገፍና መንከባከብ

መ. የሚከተሉት ጥያቄዎች መልሱ።

1. ራስን የመምራት ክህሎት የሚባሉትን ነገሮች ዘርዝሩ።
2. በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ የሚገኙ ክበባትን ዘርዝሩ።

2.3 የጉልበት አስፈላጊነት

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦

- ጉልበት ለማኅበረሰባችሁ ያለውን ጠቀሜታ ትገልጻላችሁ።
- የጉልበት ምንጮችን ትዘረዝራላችሁ።

ቁልፍ ቃላት

- ጉልበት
- የጉልበት ምንጮች



በሥዕሉ የሚታየው ምንድን ነው?
ልጁ ምን እያደረገ ነው?



ከሥዕሉ ምን አያችሁ?



በሥዕሉ የሚታየው ምንድን ነው?



ልጆቹ ምን ያደረጉ ነው?
የጉልበት ምንጫቸው ምንድን ነው?

ሥዕል 2.16 የጉልበት አስፈላጊነት

ሀ. የጉልበት አስፈላጊነት

ተግባር 2.3.1 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- የጉልበትን ምንነትና ለምን እንደሚያስፈልግ መግለጽ

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ዘገባ አቅርቡ።

- ጉልበት ምንድን ነው?
- የጉልበት ምንጮችን ዘርዝሩ።

ጉልበት አንድን ሥራ የመሥራት አቅም ወይም ችሎታ ነው። ማንኛውንም ሥራ ለመሥራት ጉልበት ያስፈልጋል። ለምሳሌ ምግብ ለማብሰል፣ ቤታችንን ለማሞቅ፣ የታጠበ ልብስ ለማድረቅና የመሳሰሉትን ለማከናወን ጉልበት አስፈላጊ ነው።



ጉልበት ሰጪ ምግብ

- ✓ በሥዕሉ የሚታየው ምንድን ነው?
- ✓ ምን ጥቅም ይሰጣል?



የፀሐይ ብርሃን

- ✓ በሥዕሉ ላይ የሚታየው ምንድን ነው?
- ✓ ለምን ይጠቅማል?



በንፋስ ኃይል የኤሌትሪክ ጉልበት ማመንጫ



ሥዕሉ ምንን ያሳያል?
ለምን ያስፈልጋል?

ሥዕል 2.17 የጉልበት ምንጮች

የጉልበት ምንጮች ማለት ጉልበትን በተለያየ መልክ በውስጣቸው ይዘው የሚገኙ አካላት ናቸው። ጉልበት በተለያየ መንገድ ይገኛል። የጉልበት ምንጮችን በተለያየ መልክ ልንመድባቸው እንችላለን። እነዚህም፦

ሀ. የቤት ውስጥ የጉልበት ምንጮች፦ ለምሳሌ የማገዶ እንጨት፣ ከሰል፣ ኩበት፣

ለ. ለመጓጓዣና ለተለያዩ ተግባራት የሚውሉ የጉልበት ምንጮች፦ ለምሳሌ ነዳጅ (ቤንዚን፣ ናፍጣ፣ ዘይት)፣

ሐ. የተፈጥሮ የጉልበት ምንጮች፦ ለምሳሌ የፀሐይ ብርሃን፣ ነፋስና ውሃን መጥቀስ ይቻላል። ነገር ግን ኤሌክትሪክ የጉልበት ዓይነት ሲሆን በራሱ ግን የጉልበት ምንጭ አይደለም።



- ✓ ሥዕሉ ላይ የሚታየው ምንድን ነው ? ለምን ይጠቅማል?
- ✓ ጉልበት ከየት ያገኛል?



- ✓ በሥዕሉ ላይ የሚታየው ምንድን ነው ለምን ይጠቅማል?
- ✓ ጉልበት ከየት ያገኛል?

ሥዕል 2.18 የጉልበት ጥቅም

የነዳጅ ዘይት የሚባሉት እንደነጭ ጋዝ፣ ናፍጣ፣ ኬሮሲን፣ ቤንዚን፣ ቡታጋዝና የመሳሰሉት ናቸው። የነዳጅ ዘይት በጉልበት ምንጭነት ያገለግላል። ለምሳሌ፦ኬሮሲን በቤት ውስጥ ምግብ ለማብሰል፣ ውሃ ለማፍላትና ለመሳሰሉት እንጠቀምበታለን። የቤት መኪናዎች አውቶብሶች፣ ከባድ የጭነት መኪናዎች፣ አውሮኘላንና መርከብ ጉልበት የሚያገኙት እንደቤንዚንና ናፍጣ ከመሳሰሉት ነዳጅ ዓይነቶች ነው።

የተፈጥሮ የጉልበት ምንጮች

ፀሐይ የተፈጥሮ የጉልበት ምንጭ ናት። ከፀሐይ በርካታ ጥቅሞችን ማግኘት እንችላለን። የታጠበ ልብስ በፀሐይ ጉልበት ቶሎ ይደርቃል። ተክሎች ምግባቸውን ለማዘጋጀት የፀሐይ ብርሃንን ጉልበት ይጠቀማሉ። ከፀሐይ የኤሌክትሪክ ጉልበት ማመንጨት ይቻላል። ይህም ጉልበት ለመብራት፣ ለመኪናዎችና ለውሃ ማሞቂያ ሊያገለግል ይችላል።

በተጨማሪም የፀሐይ ጉልበት፦

- ውሃ ከወንዝ፣ ከሐይቅ፣ ከባሕርና ከውቅያኖስ እንዲተንና ተመልሶ በዝናብ መልክ ወደ መሬት እንዲዘንብ ያደርጋል።
- ጥራጥሬዎችን፣ እንጨትን፣ ቅጠላ ቅጠሎችንና የመሳሰሉትን ለማድረቅ ይረዳል።
- የአካባቢያችንን አየር ለማሞቅ ይጠቅማል።

ነፋስ

ተግባር 2.3.2 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- የነፋስን ጠቀሜታ መግለጽ

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሱን ለመምህራችሁ ንገሩ።

- ነፋስ ምን ጥቅም ይሰጣል?
- የነፋስ ጉልበት የሚያንቀሳቅሳቸውን ነገሮች ዘርዝሩ።



በነፋስ ጉልበት ውሃን ከጉድጓድ ማውጣት



በነፋስ ጉልበት የሚሰሠራ የኤሌክትሪክ ማመንጫ

ሥዕል 2.19 የነፋስ ጥቅም

ነፋስ ብዙ ነገሮችን የማንቀሳቀስ ጉልበት አለው። ነፋስ የሚንቀሳቀስ አየር ነው። ነፋስ ከሰልን ለማቀጣጠል፣ እርጥብ ልብስን ለማድረቅ፣ እህልን ከገለባው ለመለየት (ለማዝራት)፣ የከባቢ አየር ሙቀትን ለማመጣጠንና ለመሳሰሉት ይጠቅማል።

ውሃ

ውሃ ለሕይወት እጅግ አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች አንዱ ነው። ውሃ ሳይጠጡ ብዙ ቀናት በሕይወት መቆየት አይቻልም።

ተግባር 2.3.3 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- ውሃ ለሰው ልጅ ያለውን ጥቅም መግለጽ

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት በቀረበው ጥያቄ ላይ ተወያይታችሁ መልሱን በጽሑፍ ለመምህራችሁ አቅርቡ።


- ውሃ ለሰው ልጆች ያለው ጠቀሜታ ምንድን ነው?



ሥዕል 2.20 የኤሌክትሪክ ጉልበት ማመንጫ

- ✓ ሥዕሉ ምንን ያሳያል?
- ✓ ለምን ይጠቅማል?
- ✓ ጉልበት የሚያገኘው ከምንድን ነው?

የኤሌክትሪክ ጉልበት



ሥዕሉ ምንን ያሳያል?
ለምን ይጠቅማል?



ይህ ሥዕል ምንድን ነው?
ለምን ይጠቅማል? ጉልበትስ ከምን ያገኛል?

ሥዕል 2.21 የኤሌክትሪክ ጉልበት

ኤሌክትሪክ በራሱ የጉልበት ምንጭ ባይሆንም ለተለያዩ አገልግሎቶች ይውላል። በቤታችን ውስጥ መብራት እንድናገኝ፣ ለፋብሪካዎች የምርት ሂደት፣ ለመንገድ ላይ መብራት፣ ለእህል ወፍጮና ለመሳሰሉት ጥቅም ላይ ይውላል።

መልመጃ 2.3

ሀ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

1. ጉልበት ማንኛውንም ሥራ ለመሥራት የሚያስችል አቅም ነው።
2. ነፋስ ለመጓጓዣ ተግባራት የሚያገለግል የጉልበት ምንጭ ነው።
3. ኤሌክትሪክ ተፈጥሯዊ የጉልበት ምንጭ ነው።

ለ. በ "ለ" ሥር የተዘረዘሩትን የጉልበት ዓይነቶች በ " ሀ" ስር ከተዘረዘሩት የጉልበት ምንጮች ጋር አዛምዱ።

"ሀ"	"ለ"
1. የተፈጥሮ የጉልበት ምንጭ	ሀ. ቤንዚን እና ናፍጣ
2. ለመጓጓዣ የሚውል የጉልበት ምንጭ	ለ. ነፋስና ውሃ
3. የቤት ውስጥ የጉልበት ምንጭ	ሐ. ኤሌክትሪክ
	መ. ከሰልና ማገዶ

ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ።

1. ከሚከተሉት ውስጥ የጉልበት ምንጭ የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ማገዶ ሐ. የፀሐይ ብርሃን
   ለ. ነዳጅ መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ
2. ከማገዶ ዓይነቶች ውስጥ የማይካተተው የትኛው ነው?
   ሀ. ከሰል ለ. ነፋስ ሐ. ኩበት መ. ገለባ
3. የነዳጅ ዘይት ከሚባሉት መካከል የማይመደበው የትኛው ነው?
   ሀ. የፀሐይ ብርሃን ሐ. ኬሮሲን
   ለ. ነጭ ጋዝ መ. ቤንዚን
4. ከሚከተሉት ውስጥ የፀሐይ ጉልበት ጥቅም የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ውሃ እንዲተንና ተመልሶ በዝናብ መልክ ወደ መሬት እንዲዘንብ ለማድረግ
   ለ. ጥራጥሬዎችን፣ እንጨትን፣ ቅጠላቅጠሎችን ለማድረቅ
   ሐ. የአካባቢ አየርን ለማሞቅ
   መ. ሁሉም መልስ ይሆናል።
5. ከሚከተሉት ውስጥ የውሃ ጥቅም ያልሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. ምግብ ለማብሰል
   ለ. ለመንገጥና ዓሳ ለማርባት
   ሐ. የኤሌክትሪክ ጉልበት ለማመንጨት
   መ. መልሱ አልተሰጠም

መ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

1. የነፋስ ጉልበት በአካባቢያችን ለምን ለምን ተግባራት እንደሚውል ግለጹ።
2. የጉልበት ምንጮችን ከነምሳሌያቸው ግለጹ።

2.4. ከሸክላ አፈር ከጄሶና ከወረቀት የተለያዩ ነገሮችን መሥራት

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦

- ንድፎችን መሥራትና ቁሳቁሶችን ማያያዝን ትለማመዳላችሁ።
- ጌጣጌጦችንና አምሳያዎችን ከወረቀትና ከሸክላ በመሥራት ታሳያላችሁ።

ቁልፍ ቃላት

- ንድፍ
- ጌጣጌጥ

1. የንድፍ ሥራ

ተማሪዎች! መስመሮችን በመሥራትና በመጠቀም የተለያዩ የእቃ ቅርጾችን መሥራት ይቻላል።

ንድፍ መሥራት፡-

- እጃችሁን በደንብ ያፍታታል፤
- የእጅ ጽሑፋችሁን ያሻሽላል፤
- ሥዕል ለመሣል ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፤
- የተለያዩ ነገሮችን በመለካት ለመሥራት ያግዛል፡

የንድፍ ሥራን ለማከናወን መከተል ያለባችሁን ሂደቶች እንመልከት።

1. ቀጥተኛ መስመሮች መሥራት።


ቀጥተኛ መስመሮችን በእጅና በእርሳስ ብቻ በመጠቀም በደብተራችሁ ላይ ሥሩ።



ሀ. ለ ሐ. መ

2. ቀጥተኛ መስመሮችን በእጅ ብቻ በመገጣጠም ሦስት ጎን መሥራት።


በእጅ ብቻ ቀጥተኛ መስመሮችን በመገጣጠም የሚከተሉትን ሦስት ጎኖች ሥሩ።



ሀ ለ ሐ መ

3. ቀጥተኛ መስመሮችን በተጓዳኝ መሥራት

ተጓዳኝ መስመሮች ማለት ትይዩ የሆኑ አቻ ወይም እኩል የሆኑ መስመሮች ማለት ነው።



ሀ ለ ሐ መ

4. ቀጥተኛ መስመሮችን በመገጣጠም አራት ጎን መሥራት


ማስመሪያ ሳትጠቀሙ ከዚህ በታች የተሠሩትን አራት ጎን መስመሮችን በመገጣጠም ሥሩ።



ሀ



ለ



ሐ

የወረቀት ሥራ

ተግባር 2.4.1 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- ጌጣጌጦችንና ቅርጻ ቅርጾችን ከወረቀትና ከሸክላ መሥራት እንደሚቻል መግለጽ

መመሪያ- ከ4-6 ተማሪዎች በቡድን በመሆን በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ ሐሳባችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

- ከወረቀት ምን ምን መጫወቻዎችን መሥራት እንደሚቻል ለመምህራችሁ በዝርዝር ግለጹ።
- እናንተ ከወረቀት ምን ምን መጫዎቻዎችን መሥራት ትችላላችሁ?
- ከወረቀት ምን ምን ዓይነት ጌጣ ጌጥ መሥራት እንደሚቻል ምሳሌ በማቅረብ ለጓደኞቻችሁ ግለጹ።

ወረቀትን በተለያየ መልኩ በማጠፍ የተለያዩ ነገሮችን መሥራት ይቻላል። ከወረቀት ተሠርተው አገልግሎት ላይ መዋል ከሚችሉ ነገሮች መካከል፦

- ወላንዶ
- ፖስታ
- የደስታ መግለጫ ካርድ
- የወረቀት ጌጣጌጦች ይገኙባቸዋል።

ሀ. ወላንዶ

ልጆች ወረቀትን በረጅም ክር አሥረው ነፋስ ባለበት ጊዜ አየር ላይ እንዲንሳፈፍ በማድረግ ይጫወታሉ። ይህ ከወረቀት የሚሠራ መጫወቻ ወላንዶ በመባል ይጠራል።

ተግባር 2.4.2 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- ወላንዶ ለመሥራት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን መለየት

መመሪያ- ወላንዶ ለመሥራት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችና የአሠራር ቅደም ተከተል ለመረዳት የሚከተሉትን ተግባራት ደረጃ በደረጃ አከናውኑ።

ወላንዶ ለመሥራት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፡-

- ሁለት ቀጫጭን እንጨቶች ወይንም ስንደዶዎች ወይንም ሰንበሌጥ
- አራት ጎን ቅርጽ ያለው ስስና ጠንካራ ወረቀት /ፕላስቲክ/
- ሁለት ረጅምና አጭር ክሮች
- አንድ ቀጭንና ረዥም ሆኖ የተቆረጡ ስስ ወረቀት

የአሠራር ቅደም ተከተል


1. ወረቀቱን ጠረጴዛ ላይ አስቀምጡ።
2. ወረቀቱን አራት እኩል ቦታ ላይ በማሥመሪያ በመለካት ሀ፣ ለ፣ ሐ፣ መ፣ሠ በማለት በሥዕሉ መሠረት ምልክት አድርጉ።
3. ወረቀቱን በቁመቱ እጠፉና ምልክት አድርጉ።
4. ከሥር በሥዕሉ ላይ እንደምትመለከቱት


   ቁጥር ሀን _____ከለ

   ለን_____ ከሐ

   ሐን_____ ከመ

   መን_____ ከሀ በማስመሪያ አገናኙ





ሥዕል 2.22 የወላንዶ አሠራር

5. አሁን የተገናኙት መስመሮች ላይ ቁረጡ።
6. ወረቀቱን በመብሳት ረዥሙን ሰንበሌጥ ወይንም ስንደዶ በመስመር"ሀ" "ሠ" "ሐ" አጋድማችሁ አጣብቁት።
7. አጭሩን ደግሞ በተመሳሳይ ሁኔታ በፊደል "መ "ሠ"ለ" ላይ አጋድማችሁ አጣብቁት።
8. ረዥሙን ክር ፊደል ሠ ላይ እሠሩት።
9. ትንንሽ ወረቀቶችን በመርፌ በመስፋት ከ "ሐ" ጋር አያይዙ።

በመጨረሻም በቡድን ያዘጋጃችሁትን ወላንዶ ከክፍል በመውጣት በአየር ላይ እንዲንሳፈፍ በማድረግ ለመጫወት ሞክሩ።

ሰ. የፖስታ አሠራር

ተግባር 2.4.3 ☛ **የቡድን ሥራ**

ዓላማ- የፖስታ አሠራርን መለማመድ

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት ቀጥሎ በቀረበው የፖስታ አሠራር ቅደም ተከተል መሠረት ፖስታ ሠርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

- ደብዳቤ የተላከበት አሮጌ ፖስታ ፈልጋችሁ ያዙ።
- ቀስ ብላችሁ አሮጌውን ፖስታ የተጣበቀበትን ቦታ አላቁ
- ፖስታውን ዘርግታችሁ አሠራሩን ተመልከቱ።
- የፖስታውን አሠራር ንድፍ በሌላ ንጹሕ ወረቀት ላይ ገልብጡ።
- ይህን ፖስታ የመሰለ ሌላ ፖስታ ለመሥራት ሞክሩ።
- የሠራችሁትን ፖስታ ለክፍል ጓደኞቻችሁና ለመምህራችሁ አሳዩ።

ተግባር 2.4.4 ☛ የቡድን ሥራ


ዓላማ- የፖስታ አሠራር ሂደትን መለየት


የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች

- የተለያየ ቀለም ያላቸው (ነጭ፣ ቀይ፣ ቢጫ) ወረቀቶች
- መቀስ
- ማጣበቂያ (ሉሀ)
- ማስመሪያ
- እርሳስ

መመሪያ- ከ4 - 6 ተማሪዎች በመሆን ቡድን መሥርታችሁ ቀጥሎ በቀረበው የፖስታ አሠራር ቅደም ተከተል መሠረት ፖስታ ሠርታችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

- ወረቀቱን እኩል ቦታ እጠፉት
- ወረቀቱን ሁለት ሳ.ሜ ገባ በማለት መስመር 1-3 እና 4-6 አስምሩ።
- የግማሽ ወረቀቱን አናት ወስዳችሁ ሦስት ሳ.ሜ ዝቅ ብላችሁ አስምሩ፤






ሥዕል 2.23 የፖስታ አሠራር

በሥዕል 2.23 የተመለከቱትን ቁጥሮች በመከተል መስመር 1-2፣ 4-5፣ 3-8 እና 6-7 በመቀስ ቁረጡና አውጧቸው።

- የቀረውን ወረቀት ገልብጣችሁ መስመር 2-3 እና 5-6 ያሉባቸውን ወረቀቶች በሉሀ ቀቧቸው፤ ከወረቀት 1-2 እና 4-5 ጋር አጣብቋቸው።
- መስመር 3-8 እና 6-7 የተጻፈበት የወረቀት ክፍል የፖስታው ክዳን ሆኖ እንዲያገለግል አጥፋችሁ ውስጡን በሉሀ ቀቡት፤
  በመጨረሻ የተፈለገው ፖስታ መሠራቱን ወረቀት (ደብዳቤ) አጣጥፋችሁ ውስጡ በመጨመር አረጋግጡ።

ሐ. የደስታ መግለጫ ካርድ አሠራር

የደስታ መግለጫ ካርድ ለመሥራት የሚያገለግል ጠንከር ያለ ወረቀት ያስፈልጋል። ስለዚህ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት የወረቀቱን መጠን ለኩ። ከዚህ በኋላ በሚከተለው መንገድ ወረቀቱን መሐል ለመሐል በማጠፍ የደስታ መግለጫ ካርድ ሥሩ።





ሥዕል 2.24 የደስታ መግለጫ ካርድ

ካርዱ ከተዘጋጀ በኋላ ልዩ ልዩ ሥዕሎችን በመሣል ወይንም ሥዕሎችን ቆርጦ በመለጠፍ ማስጌጥ ይቻላል።

2. ከወረቀት ጌጣጌጦች መሥራት

ወረቀትን በማጠፍ፣ በመቆራረጥና በማጣበቅ የተለያዩ ነገሮችን መሥራት እንደሚቻል ተምራችኋል።

ተግባር 2.4.5 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- ከወረቀት የተለያዩ ጌጣጌጦችን መሥራትና መጠቀም እንደሚቻል መግለጽ

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለመምህራችሁ በጽሑፍ አቅርቡ።

- ከወረቀት ምን ምን ዓይነት ጌጣ ጌጦች መሥራት ይቻላል?
- በወረቀት የሚሠሩ ጌጣጌጦች የሚሰጡት ጥቅም ምንድን ነው?

3. ከሸክላ አፈርና ከጂሶ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ወይንም /መሳይ ቅርጾችን/መሥራት

ጌጣጌጦችንና መሳይ ቅርጾችን ከሸክላ ወይንም ከጂሶ መሥራት ይቻላል።

ተግባር 2.4.6 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- ከሸክላ አፈር ወይንም ከጂሶ የሚሠሩ ቁሳቁሶችን መለየት።

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለመምህራችሁ በጽሑፍ አቅርቡ።

- ከሸክላ ወይም ከጂሶ ምን ምን ዓይነት ቁሳቁሶች መሥራት ይቻላል?
- ከሸክላ ወይም ከጂሶ የሚሠሩ ቁሳቁሶች ምን ዓይነት ጥቅም ይሰጡናል?



- ሥዕሉ ምንን ያሳያል?
- ለምን ይጠቅማል?



- ሰውዬው ምን እየሠራ ነው?



- ሥዕሉ ምንን ያሳያል?





- ሥዕሉ ምን ያሣያል?
- ለምን ይጠቅማሉ?

ሥዕል 2.25 ከጂሶና ከሸክላ የተሠሩ ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች

የሸክላ ሥራ

የተለያዩ ቁሳቁሶችንና መሣሪያዎችን በመጠቀም ከሸክላ ልዩ ልዩ የቤት ቁሳቁሶችን መሥራት ይቻላል። የሸክላ ሥራ በሀገራችን ራሱን የቻለና ጠቃሚ የሥራ መስክ ነው። በተጨማሪም በፋብሪካ በሚዘጋጅ ጂሶ የተለያዩ እቃዎችንና የቤት ማስጌጫዎችን መሥራት ይቻላል። ጂሶ በፋብሪካ ተዘጋጅቶ የሚቀርብ በመሆኑ እንደሸክላ አፈር ለዝግጅት ብዙ ጊዜ አይወስድም።

ከሸክላ አፈር ጌጣጌጦችን ለመሥራት የተለያዩ መሣሪያዎችን እንጠቀማለን። ለምሳሌ፦ ሙቀጫ፣ ወንፊት፣ የውሃ መያዣ ባልዲ፣ የመቁረጫ ሽቦ፣ የተለያዩ ቅርጽ ያላቸው ቢላዎች፣ ቅርጽ ማውጫ፣ ወስፌ፣ የመጠፍጠፊያ እንጨትና የመሳሰሉት መሣሪያዎች ለሸክላ ሥራ አስፈላጊ ናቸው።

የሸክላ ጭቃ አዘገጃጀት

የተለያዩ የሸክላ ቁሳቁሶችን ለመሥራት ቀይ የሸክላ አፈርና ጥቁር መረሬ አፈር አስፈላጊ ናቸው።

- አፈሩን ለማግኘት መጀመሪያ አካባቢውን ማጥናት ያስፈልጋል።
- አፈሩን ለማግኘት ከ40 እስከ 50 ሳንቲ ሜትር ጥልቀት ያለው መሬት መቆፈር ይገባል።
- የሸክላ አፈር የማጣበቅ ባሕርይ ስላለው በቁፋሮ ወቅት አፈሩ የማጣበቅ ባሕርይ እንዳለው ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

የአዘገጃጀት ሂደት

ሀ. አፈሩን ማድቀቅ፦ ከሸክላ አፈር የቤት ቁሳቁስ ለመሥራት በመጀመሪያ በቁፋሮ የተገኘውን አፈር ማድቀቅ ያስፈልጋል። ስለዚህም፦

- የሸክላ አፈር በደንብ መድቀቁን ማረጋገጥ።
- አፈሩን እየከለከሉ እስከሚደቅ ድረስ መውቀጥና መፍጨት።
- በጥቅጥቅ ወንፊት አፈሩን በመንፋት ጠጣሩን ከላመው የሸክላ አፈር መለየት።

ለ. ማቡካት፦ የደቀቀው አፈር ተቦክቶ የተለያዩ ቅርጽ ያላቸው ቁሳቁሶች ይሠራሉ። ስለሆነም የማቡካት ሂደቱ በሚከተለው ሁኔታ መከናወን አለበት።

- የተጣራውን የሸክላ አፈር ውሃ በመጨመር እየለወሱ ማቡካት
- የቦካውን አፈር ማሸትና በጠፍጣፋ ድንጋይ ላይ አድርጎ መለንቀጥ
- የተቦካው ጭቃ እንደላስቲክ እስከሚሳብ ድረስ በእጅ ማሸት
- የታሸውን የሸክላ ጭቃ በመጠፍጠፊያ እንጨት ወይም ጣውላ ላይ አድርጎ እየዳመጡ መለንቀጥ ያስፈልጋል።

ለሸክላ ሥራ የተዘጋጀውን ጭቃ ወይንም ጆሶ በመጠቀም የተለያየ ቅርጽ ያላቸው የሸክላ እቃዎችን በሁለት መልክ ማዘጋጀት ይቻላል። የሸክላ እቃዎችን ለመሥራት ሁለት ዓይነት የአሠራር ስልቶች አሉ።

እነርሱም፡-

1. የሸክላ ጭቃን በማድቦልቦል የሚሠሩ የሸክላ እቃዎች
2. የሸክላ ጭቃን በመጠፍጠፍ የሚሠሩ የሸክላ እቃዎች ተብለው ይከፈላሉ።

የሸክላ ጭቃን በማድቦልቦል የተለያዩ ቅርጽ ያላቸውን እቃዎች መሥራት ይቻላል። ለምሳሌ ጀበና፣ ድስት፣ እንስራ፣ ገንቦ፣ ጡብ የመሳሰሉት እቃዎች የሚሠሩት የሸክላ ጭቃን በማድቦልቦል ነው።

የሸክላ ጭቃን ዝርግ ነገር ላይ በመጠፍጠፍ የተለያዩ ቅርጽ ያላቸውን ነገሮች መሥራት ይቻላል። **ለምሳሌ፡-** ምጣድ፣ ምድጃ፣ ሣህንና የመሳሰሉት ነገሮች የሚሠሩት የሸክላ ጭቃን በዝርግ ነገር ላይ በመጠፍጠፍ ነው።

ሸቦ ለሸክላ ሥራ አስፈላጊ ነው። ሸቦው የተድቦለቦለውን ወይንም የተጠፈጠፈውን የሸክላ ጭቃ በምንፈልገው መጠን ለመቁረጥ ይጠቅማል።

ጐድጓዳ ሣህን ከሸክላ አፈር ለመሥራት ደግሞ፡- ከፕላስቲክ የተሠሩ ጐድጓዳ ሣህን፣ ጋዜጣ ወይንም ስስ ፌስታል፣ እስፖንጅ ወይም የተጠፈጠፈ የሸክላ ጭቃ ያስፈልጋል።

ተግባር 2.4.7 ☛ የቡድን ሥራ

ዓላማ- ከሸክላ አፈር እንዴት ጐድጓዳ ሳህን መሥራት እንደሚቻል መለማመድ

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት ቀጥሎ በቀረበው ጐድጓዳ ሳህን አሠራር ቅደም ተከተል መሠረት ጐድጓዳ ሳህን ሠርታችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

አሠራር

1. ጐድጓዳ ሣህኑን በጋዜጣ ወይንም በፌስታል በውስጥ በኩል መሸፈን
2. የተጠፈጠፈውን ጭቃ ሣህኑ ውስጥ መጨመር
3. ጭቃው የላስቲክ ሣህኑን ቅርጽ እስከሚይዝ ድረስ ከጠፈጠፉ በኋላ ማለስለስ
4. ጭቃው ጠፈፍ እስኪል ድረስ ለተወሰነ ጊዜ ማቆየት
5. ውሃውን እንዲመጥና እንዲለሰልስ በስፖንጅ ማሸት
6. የፌስታሉን ጫፍ በመያዝ ከሳህኑ ማውጣት
7. በመጨረሻም በእሳት መጥበስ። ይህም ሸክላው በደንብ እንዲደርቅና እንዳይሰነጠቅ ይረዳል።



ሥዕል 2.26 ከሸክላ አፈር ውስጡ ክፍት የሆነ ዕቃ አሠራር

የጀበናና የገንቦ ሞዴል አሠራር

ተግባር 2.4.8 ☛ የቡድን ሥራ

ዓላማ- የጀበናና የገንቦ አሠራርን መለማመድ

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት የጀበናና የገንቦ አሠራር ሁኔታን በሚገልጸው ቅደም ተከተል መሠረት ጀበናና ገንቦ መሰል ቅርጽ ሠርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

1. በአሮጌ ጨርቅ ወይንም ጆንያ የጀበና ወይንም የገንቦ ቅርጽ እንዲኖረው አሸዋ ወይንም አፈር በመሙላት ማዘጋጀት
2. የጀበናው ወይንም የገንቦው ጆሮዎች እንዲሁም የጀበናው ጡት በቅርጽ ውስጥ አይገቡም።
3. የተዘጋጀውን ቅርጽ በተድቦለቦለው የሸክላ ጭቃ ላይ ማስቀመጥ
4. የሸክላ ጭቃውን በተሠራው ቅርጽ ላይ እየጠፈጠፉ ቅርጹን እንዲጠብቅ ማድረግ
5. የሸክላ ጭቃው የሚፈለጉትን ቅርጾች ሲይዝ ቀስ አድርጎ ማንሣት ከዚያም አሸዋውን ወይንም አፈሩን በመዘቅዘቅ መድፋት

የጀበናና የገንቦ መያዣዎች መሥራት

1. የተድቦለቦለ የሸክላ ጭቃ እንደደጋን ቅርጽ እያጠፉ መያዣዎችን መሥራት
2. ቅርጹ በትክክል ከተሠራ በኋላ የተሠሩትን ጆሮች በገንቦውና በጀበናው ትክክለኛ ቦታ ላይ መለጠፍ



ጀበና



ገንቦ

ሥዕል 2.27 ከሸክላ አፈር የተሠሩ ጀበናና ገንቦ

3. ለጀበናው የጡት ቅርጽ ከተሠራ በኋላ በወስፌ የጡት ቀዳዳ መሥራት
4. የተለያዩ ጌጣጌጥ ለመሥራት በቢላዋ ጫፍ ትንሽ ጫን ብሎ ቅርጹን መሥራት
5. ጆሮውና ጡቱ የተገናኙበት ቦታ ከለሰለሰ በኋላ የተዘጋጁትን ጀበናና ገንቦ በእሳት ማቃጠል።

መልመጃ 2.4

ሀ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

1. ከሸክላ የተለያዩ ቁሳቁሶችንና መሣሪያዎችን መሥራት ይቻላል።
2. የሸክላ ሥራ በሀገራችን ምንም ዓይነት አስተዋጽኦ የለውም።
3. በጂሶ የሚሠሩ ቁሳቁሶች ቅድመ ዝግጅት ብዙ ጊዜ አይወስዱም።
4. ከሸክላ አፈር የሚሠሩ እቃዎች የአሠራር ቅደም ተከተል ተመሳሳይ ነው።
5. የሸክላ ሥራ ለገቢ ምንጭነት ያገለግላል።

ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ።

1. ለሸክላ ሥራ የማይጠቅሙ መሣሪያዎችን ስብስብ የያዘው የቱ ነው?
   ሀ. ወፍጮ፣ ሙቀጫ፣ ወንፊት፣ የውሃ መያዣ ባልዲ
   ለ. ሙቀጫ፣ ሽቦ፣ የተለያዩ ቅርጽ ያላቸው ቢላዎች
   ሐ. ቅርጽ ማውጫ ፣ ወስፌ፣ የመጠፍጠፊያ እንጨት
   መ. መልሱ አልተሰጠም
2. የተለያዩ የሸክላ ቁሳቁሶችን ለመሥራት የማይጠቅመው የትኛው ነው?
   ሀ. ደቃቅ አፈር ሐ. ተዳምጦ የተለነቀጠ ጭቃ
   ለ. ጠጣር አፈር መ. ቅርጽ ማውጫ

3. የሸክላ እቃዎችን መሥራት ጥቅም ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ገቢ ለማግኘት

   ለ. ባህላዊ የመመገቢያና ማብሰያ እቃዎችን ለመሥራት

   ሐ. የሥራ ዕድል ለመፍጠር

   መ. ሁሉም መልስ ነው።

4. የሸክላ ጭቃን ዝርግ ነገር ላይ በመጠፍጠፍ ሊዘጋጅ የማይችለው ቅርጽ የትኛው ነው?

   ሀ. ምጣድ ሐ. ምድጃ

   ለ. ጀበና መ. ማሀን

5. ከሸክላ ጐድጓዳ ማሀን ለመሥራት የሚያስፈልገው የትኛው ነው?

   ሀ. ጎድጓዳ የፕላስቲክ ማሀን

   ለ. ጋዜጣ ወይንም ስስ ፌስታል

   ሐ. እስፖንጅ ወይንም የተጠፈጠፈ የሸክላ ጭቃ

   መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ

ሐ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::

1. የጀበና፣ የገንቦ መያዣዎችና ጡት ቅርጽ አሠራርን በዝርዝር ግለጹ።
2. ለሸክላ ሥራ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ዘርዝሩ።
3. ወላንዶ ለመሥራት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ዘርዝሩ።
4. የተለያዩ ንድፎችን መሥራት የሚያስገኘውን ጥቅም ግለጹ።

ማጠቃለያ

- የማኅበረሰብ አባላትን ዕድሜን መሠረት በማድረግ ሕጻናት፣ ጎረምሶች፣ ኮረዶች፣ ጎልማሶችና አዛውንቶች በማለት መመደብ ይቻላል።
- ሕፃናት የመማር፣ ከአቅም በላይ የሆነ ሥራ ያለመሥራት፣ ምግብ፣ አልባሳትና የመኖሪያ ቤት የማግኘት፣ ስምና ዜግነት የማግኘት መብቶች አላቸው።
- ሕጻናት ከአቅማቸው በላይ ከሆነና፣ ጉልበታቸውን ከሚያደክም፣ ጤናቸውን ከሚጎዳና ትምህርታቸውን በአግባቡ እንዳይከታተሉ ከሚያደርጉ ሥራዎች መጠበቅ አለባቸው።
- ድብደባ፣ ቁንጥጫ፣ ጭካኔ የተሞላበት ቅጣት በሕጻናት ላይ መፈጸም የለበትም። ሕጻናትን ማንቋሸሽ፣ መስደብ፣ ማመናጨቅና ማዋረድ መብታቸውን መጣስ ነው።
- በዕቅድና በሥርዓት የመኖር ክህሎትን ማዳበር ራስን የመምራት ክህሎት ነው።
- በማኅበረሰብ ውስጥ ከሚካሄዱ ተግባራት መካከል የአካባቢ ጽዳት፣ የችግኝ ተከላ፣ አቅመ ደካሞችን የመደገፍና የመንከባከብ ተግባራት ሊጠቀሱ ይችላሉ።
- ክበባት በተማሪዎች ተሳትፎና ፍላጎት የሚቋቋሙና ለትምህርታቸውም አጋዥ የሆኑ የተማሪዎች ስብስብ ናቸው።
- ጉልበት ሥራን የመሥራት አቅም ነው። ማንኛውንም ሥራ ለመሥራት ጉልበት ያስፈልጋል።
- የጉልበት ምንጮች የቤት ውስጥ የጉልበት ምንጮች፣ ለመጓጓዣና ለተለያዩ ተግባራት የሚውሉ የጉልበት ምንጮችና የተፈጥሮ የጉልበት ምንጮች ተብለው ይከፈላሉ።
- ንድፎችን በመሥራትና ቁሳቁሶችን በማያያዝ ፖስታ፣ የደስታ መግለጫ ካርድ፣ ወላንዶና የመሳሰሉትን መሥራት ይቻላል።
- ከሸክላና ከጀሶ ጌጣጌጦችን፣ ሞዴሎችንና የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን መሥራት ይቻላል።

የማጠቃለያ ጥያቄዎች

ሀ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ“እውነት” ትክክል ካልሆኑ ደግሞ“ሐሰት” በማለት መልሱ።

1. የማኅበረሰብ አባላትን ዕድሜያቸውን መሠረት አድርጎ መመደብ አይቻልም።
2. መብት ከሌሎች ወገኖች ጣልቃ ገብነት ነጻ በመሆን የሚከናወኑ ተግባራትን ይገልጻል።
3. የዕለት ተግባራትን ለመፈጸም እቅድ ማዘጋጀት አያስፈልግም።
4. ኤሌክትሪክ በራሱ የጉልበት ምንጭ አይደለም።
5. ንፋስ በጉልበት ምንጭነት ያገለግላል።

ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።

1. የሕጻናት ግዴታ ያልሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. ቤተሰቦቻቸውን ማክበር ሐ. ታላላቆችን ማክበር
   ለ. ለጉልበት ብዝበዛ መዳረግ መ. ሕጻናትን በሚመለከቱ ተግባራት ላይ መሳተፍ
2. የሕጻናት መብት የሆነውን ምረጡ።
   ሀ. መጠሪያ ስም ማግኘት ሐ. ለጦርነት መሰለፍ
   ለ. በከባድ ሥራ ላይ መሠማራት መ. መጠለያ መገንባት
3. ለሕጻናት ዕድገት አስፈላጊ ያልሆነው
   ሀ. ድብደባ ሐ. አልባሳት
   ለ. ምግብ መ መጠለያ
4. ራስን የመምራት ክህሎትን የማያሳየው የትኛው ነው?
   ሀ. በዕቅድና በሥርዓት መመራት
   ለ. ተግባርን በጊዜ መሠረት ማከናወን
   ሐ. ስነ-ሥርዓት አለማክበር
   መ. በክበባት ውስጥ መሳተፍ
5. በማኅበረሰብ ውስጥ ከሚካሄዱ ተግባራት መካከል የማይካተተው የትኛው ነው?
   ሀ. የአካባቢ ጽዳት ሐ. የችግኝ ተከላ
   ለ. የቡድን ጸብ መ. አቅመ ደካሞችን መደገፍና መንከባከብ

6. ከጉልበት ምንጮች መካከል ሊመደብ የሚችለው የትኛው ነው?

ሀ. ማገዶ ሐ. የፀሐይ ብርሃን

ለ. ነዳጅ መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ

7. ከማገዶ ዓይነቶች ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?

ሀ. ከሰል ሐ. ኩበት

ለ. ነፋስ መ. ገለባ

8. የነዳጅ ዘይት ከሚባሉት መካከል የማይመደበው የቱ ነው?

ሀ. የፀሐይ ብርሃን ሐ. ኬሮሲን

ለ. ነጭ ጋዝ መ. ቤንዚን

9. በፀሐይ ጉልበት ሊከናወን የሚችለው የትኛው ነው?

ሀ. ውሃ እንዲተንና ተመልሶ በዝናብ መልክ ወደ መሬት መዝነብ

ለ. ጥራጥሬዎችን፣ እንጨትን፣ ቅጠላቅጠሎችን ማድረቅ

ሐ. የአካባቢ አየርን ማሞቅ

መ. ሁሉም መልስ ይሆናል።

ሐ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::

1. የሕጻናት መብቶች እንዴት መጠበቅ እንደሚገባቸው አብራሩ።
2. ሕጻናትን ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ የአደጋ ዓይነቶች ምን ምንድን ናቸው?
3. ራስን የመምራት ክህሎት ምንድን ነው?
4. በሕጻናት ላይ የሚደርሰውን አደጋ ለመከላከል መወሰድ ያለበትን እርምጃ ዘርዝሩ።

ፍተሻ

የምታውቋቸውን ክንውኖች በመለየት በእያንዳንዱ ሳጥን ውስጥ ይህንን (✓) ምልክት አኑሩ።

1. የማኅበረሰባችንን አባላት በዕድሜያቸው መሠረት እመድባለሁ።
2. በማኅበረሰባችን የዕድሜ ምድብ መሠረት የራሴን የዕድሜ ምድብ እለያለሁ።
3. አንዳንድ የሕጻናት መብቶችንና የመብቶች ጥሰት የሚገልጹ ምሳሌዎችን እሰጣለሁ።
4. የሕጻናት መብቶች እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው ሐሳብ አቀርባለሁ።
5. የየዕለት እንቅስቃሴዬን ማቀድን እለማመዳለሁ።
6. ራስን በራስ የመምራት ተግባርን አሳያለሁ።
7. ዕድሜዬ በሚፈቅደው መሠረት በአንዳንድ የማኅበረሰብ እንቅስቃሴ ውስጥ ለመሳተፍ ያለኝን ፍላጎት በተግባር አሳያለሁ።
8. ጉልበት ለማኅበረሰባችን ያለውን ጠቀሜታ እገልጻለሁ።
9. የጉልበት ምንጮችን እዘረዝራለሁ።
10. ንድፎችን መሥራትና ቁሳቁሶችን ማያያዝን (ማገናኘት) እችላለሁ።
11. ጌጣጌጦችንና ቅርጻቅርጾችን ከወረቀትና ከሸክላ እሠራለሁ።
12. ሳይንሳዊ የምርምር ክህሎቶችን ማለትም፦ መመልከትን፣ መጠየቅን፣ መመደብን፣ መለካትን፣ መግባባትን፣ መሳይ ቅርጾችን መስራትንና ተባብሮ መሥራትን በተግባር አሳያለሁ።

ምዕራፍ ሦስት

የተፈጥሮ አካባቢያችን

ከምዕራፉ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፦

- አንዳንድ የተፈጥሮ ክስተቶች ተፈጥሯዊ ዑደቶች መሆናቸውን ትናገራላችሁ፡፡
- አንዳንድ የተፈጥሮ ክስተቶች አልፎ አልፎ የሚከሰቱ መሆናቸውን ትናገራላችሁ::
- የመለኪያ አሐዶችን በመለየት ባህላዊና ዘመናዊ በማለት ትመድባላችሁ፡፡
- ቁሳቁሶችን (ዕቃዎችን) የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ በማለት ትመድባላችሁ፡፡
- ቁሳቁሶችን (ዕቃዎችን) በዓይነታቸውና በክብደታቸው መሠረት ትመድባላችሁ፡፡
- የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የተፈጥሮ ሀብቶች የሚሰጡትን ጠቀሜታ ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የተፈጥሮ ሀብቶች ከጥፋት የሚጠበቁባቸውን ዘዴዎች ታስረዳላችሀ፡፡
- የተክል ክፍሎችን ታሳያላችሁ፡፡
- እያንዳንዱን የተክል ክፍል ናሙናዎች ትሰበስባላችሁ፡፡
- ስለ እያንዳንዱ የተክል ክፍል ሥራ ገለጻ ትሰጣላችሁ፡፡
- ተክሎች ለመብቀል የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች ትዘረዝራላችሁ፡፡
- ተክሎችን ለማብቀል የሚረዱ ዕቃዎችንና ቁሳቁሶችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- እንስሳትን በእርባታ ሂደታቸው መሠረት ትመድባላችሁ
- እንስሳትን በእንቅስቃሴያቸው መሠረት ትመድባላችሁ፡፡
- እንስሳትን በአመጋገባቸው መሠረት ትመድባላችሁ፡፡
- እንስሳትን በመኖሪያ ቦታቸውና በሰውነት ሽፋናቸው መሠረት ትመድባላችሁ::
- ከእንስሳት ውጤቶች የሚገኙ ምርቶችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- ለእርሻ እንስሳት እንክብካቤና አጠባበቅ የሚጠቅሙ ዕቃዎችንና ቁሳቁሶችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የሳይንሳዊ ምርምር ክህሎቶችን ማለትም መመልከትን፣ መጠየቅን፣ መመደብን፣ መለካትን፣ መመዝገብን፣ መግባባትን፣ መሳይ ቅርፆችን (ሞዴሎችን) ማዘጋጀትንና ተባብሮ መሥራትን በተግባር ታሳያላችሁ፡፡

3.1 የተፈጥሮ ክስተቶች

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦

- ወቅቶችን በተፈጥሯዊ ዑደታቸው ትመረምራላችሁ።
- ቀንና ሌሊትን በተፈጥሯዊ ዑደትነታቸው ትመረምራላችሁ።
- የሕይወት ሂደቶችን በተፈጥሮአዊ ዑደታቸው ትመረምራላችሁ።
- ቀስተ ደመናና ጕርፍ አልፎ አልፎ የሚከሰቱ የተፈጥሮ ክስተቶች መሆናቸውን ታብራራላችሁ።
- የርዝመት፣ የክብደትና የጊዜ ልኬት አሐዶችን ትለያላችሁ።
- የመለኪያ አሐዶችን ባህላዊና ዘመናዊ በማለት ትመድባላችሁ።
- ዕቃዎችን (ቁሳቁሶችን) የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ በማለት ትመድባላችሁ።
- ዕቃዎችን (ቁሳቁሶችን) በክብደታቸውና በዓይነታቸው መሠረት ትመድባላችሁ።

ቁልፍ ቃላት

- የተፈጥሮ ክስተት
- ቀንና ሌሊት
- ወቅት
- ድርቅ
- ጕርፍ

1. የተፈጥሮ ክስተቶችን ማስተዋል

የተፈጥሮ ክስተት ማለት ምን ማለት ነው?

የተፈጥሮ ክስተት ማለት ከሰዎች ቁጥጥር ውጭ የሆነና በተፈጥሮ በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈጠር ክስተት ነው።

ተግባር 3.1.1 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- የተፈጥሮ ክስተቶች ምን ምን እንደሆኑ መለየት

መመሪያ- ከ4 -6 ተማሪዎች በቡድን በመሆን ከዚህ በታች በቀረበው የመወያያ ጥያቄ ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን ለመምህራችሁ ንገሩ።

የመወያያ ጥያቄ

- የተፈጥሮ ክስተቶች ምን ምን ናቸው?

ከተፈጥሮ ክስተቶች ጥቂቶቹ ቀንና ሌሊት፣ ክረምትና በጋ፣ ቀስተ ደመና፣ ድርቅ፣ ጕርፍ፣ የመሳሰሉት ናቸው።

ሀ. ቀንና ሌሊት

ቀንና ሌሊት ተፈጥሯዊ ዑደትን የሚያሳይ የተፈጥሮ ክስተት ነው።

ተማሪዎች! ከክፍላችሁ ወጣ በማለት አካባቢያችሁን ተመልከቱ። ምን ምን አያችሁ? ያያችኋቸውን ነገሮች በዝርዝር ለመምህራችሁ ተናገሩ። በአካባቢያችሁ ያሉ ነገሮችን እንድታዩ ያስቻላችሁ ምንድ ነው? እነዚህን የተመለከታችኋቸውን ቁሳቁሶች ብርሃን በማይኖርበት ጊዜ መመልከት ትችላላችሁ?

በአካባቢያችሁ ያሉትን ነገሮች ለማየት ያስቻላችሁ ብርሐን ነው። ብርሐን በአካባቢያችን የሚገኙ ነገሮችን እንድንመለከት ይረዳናል። በጨለማ ብርሐን ስለማይኖር አካባቢያችንን ማየት አንችልም።

ተግባር 3.1.2 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- ስለቀንና ሌሊት ልዩነት ማስረዳት

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በመወያያ ጥያቄዎቹ ላይ ተወያይታችሁ መልሳቸውን በደብተራችሁ ላይ ጻፉ።

የመወያያ ነጥቦች

- በቀንና በሌሊት መካከል ምን ልዩነት አለ?
- በቀንና በሌሊት የምታከናውኗቸው ተግባራት ምን ምን እንደሆኑ ለይታችሁ በመዘርዘር በደብተራችሁ ላይ ጻፉ።

ቀደም ሲል እንደተገለፀው ቀንና ሌሊት አንዱ የተፈጥሮ ገፅታ ነው።

አንድ ሙሉ ቀን 24 ሰዓታት አሉት። ከእነዚህ ውስጥ የፀሀይ ብርሃን ያለበት ጊዜ ቀን በመባል ይታወቃል። ቀሪው የፀሃይ ብርሃን የሌለበት ጊዜ ደግሞ ሌሊት ይባላል።

ቀን የምንለው የተፈጥሮ ክስተት

- ብርሐናማ
- ሞቃታማና
- በጫጫታ የተሞላ ነው።

ሌሊት የምንለው የተፈጥሮ ክስተት ደግሞ

- ጨለማ
- ቀዝቃዛና
- ጸጥ (ረጭ) ያለ ነው።



ሀ. ቀን



ለ. ሌሊት

ሥዕል 3.1 ቀንና ሌሊት

ለ. ወቅቶች

ተግባር 3.1.3 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- ስለወቅቶች ምንነት መግለፅ

መመሪያ- ከ4-6 ተማሪዎች በቡድን በመሆን ከዚህ በታች በቀረቡ የመወያያ ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ ዋና ዋና ሃሳቦችን በጽሑፍ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

የመወያያ ጥያቄዎች

- በአካባቢያችሁ ከፍተኛ የዝናብ መጠን የሚኖርበት ጊዜ መቼ ነው?
- በአካባቢያችሁ የሙቀት መጠን የሚጨምረው በምን ጊዜ ነው?
- በአካባቢያችሁ አረንጓዴ ዕፅዋት በብዛት በቅለው የሚታዩበት ጊዜ መቼ ነው?


በሀገራችን ሁለት ዋና ዋና ወቅቶች አሉ። እነርሱም የዝናብ ወቅትና ደረቅ ወቅት ናቸው። እነዚህ ወቅቶች አልፎ አልፎ የሚከሰቱ ሳይሆን ሁሌም ጊዜያቸውን ጠብቀው የሚከሰቱ ናቸው።

ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን ሰንጠረዥ በመመልከት የዝናብ ወቅትንና የደረቅ ወቅትን ልዩነቶች ተረዱ።

ሠንጠረዥ 3.1 የዝናብ ወቅትና ደረቅ ወቅት

የዝናብ ወቅት	ደረቅ ወቅት
• ዝናብ ይዘንባል • አየሩ ቀዝቃዛ ነው • ዕፅዋት ይለመልማሉ • ወንዞች ይሞላሉ	• ዝናብ አይዘንብም • አየሩ ሞቃት ነው • የዕፅዋት ቅጠሎች ይረግፋሉ • ወንዞች ይጐድላሉ፤ አንዳንድ ወንዞች ደግሞ ይደርቃሉ





- ይህ የምን ሥዕል ነው?
- በምን ጊዜ የሚከሰት ይመስላችኋል?

ተግባር 3.1.4 ☛ የቡድን ሥራ

ዓላማ- የቀስተ ደመናን ቀለማት መዘርዘር

መመሪያ- የቀስተ ደመና ሥዕል ሥላችሁ የቀለማቱን ዓይነትና ቅደም ተከተላቸውን ጻፉ።

ቀስተ ደመና አልፎ አልፎ የሚከሰት የተፈጥሮ ክስተት ነው። የሚፈጠረውም የፀሐይ ብርሐን በዝናብ ጠብታዎች ውስጥ ሲያልፍ ነው። ቀስተ ደመና የተለያዩ ቀለማት አሉት። በሥዕሉ እንደተመለከታችሁት የቀለማቱም ቅደም ተከተል ቀይ፣ ብርቱካንማ፣ ቢጫ፣ አረንጓዴ፣ ሰማያዊ፣ ሃምራዊና ወይን ጠጅ ነው።

መ. ድርቅና ጎርፍ

ተግባር 3.1.5 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- ድርቅና ጎርፍ እንዴት እንደሚከሰቱና የሚያስከትሏቸውን ችግሮች መለየት

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን መሥርታችሁ ከዚህ በታች በቀረቡ የመወያያ ጥያቄዎች ላይ በመወያየት ዋና ዋና ሐሳቦችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

የመወያያ ጥያቄዎች

- ድርቅና ጎርፍ በምን ምክንያት ይከሰታሉ?
- በድርቅና ጎርፍ ምክንያት የሚከሰቱ ችግሮች ምን ምንድን ናቸው?

ድርቅና ጎርፍ ከተፈጥሮአዊና ሰው ሠራሽ ችግሮች የተነሣ አልፎ አልፎ ሊከሰቱ የሚችሉ የተፈጥሮ ክስተቶች ናቸው።

ድርቅ የሚከሰተው አብዛኛውን ጊዜ ወቅቱን ጠብቆ መዝነብ የነበረበት ዝናብ በበቂ መጠን ወይም ጨርሶ ሳይዘንብ ሲቀር ነው።

ድርቅ በደኖች መቆረጥ ወይም መጨፍጨፍ ምክንያት ሊከሰት ይችላል። ድርቅ በእንስሳትና በዕፅዋት ላይ ጉዳት ያደርሳል። በእንስሳትና ዕፅዋት ላይ የሚደርሰው ጉዳት ደግሞ በሰው ልጆች ኑሮና ጤና ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል።

ጉርፍ የሚከሰተው ከመጠን በላይ የሆነ ዝናብ በተከታታይ በአንድ አካባቢ ሲዘንብ ነው። ጉርፍ በእንስሳት፣ በዕፅዋት፣ በሰዎችና በንብረት ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ከፍተኛ ነው።



ሥዕል 3.2 በድርቅና በጉርፍ የተጐዱ አካባቢዎች

ተግባር 3.1.6 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- ድርቅንና ጎርፍን ለመከላከል የሚያስችሉ ዘዴዎችን ማስረዳት

መመሪያ- በቡድን በመሆን በቀረበው የመወያያ ጥያቄ ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ።

የመወያያ ጥያቄ


- ድርቅና ጉርፍን ለመከላከል የሚያስችሉ ዘዴዎች ምን ምን ናቸው?

2. የሕይወት ደረጃዎች (መወለድ፣ ማደግ፣ መሞት)


ከዚህ በታች የቀረቡትን ሥዕሎች በመመልከት የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ።

✓ ከዚህ ሥዕል ምን ትረዳላችሁ?

✓ ይህ ሥዕል ምንን ያሳያል



ሀ) የዶሮ የሕይወት ደረጃዎች



ለ) የተክል የሕይወት ደረጃዎች

ሥዕል 3.3 የሕይወት ደረጃዎች

ሕይወት ያላቸው ነገሮች፡-

- ይወለዳሉ
- ያድጋሉ
- ይሞታሉ።


ለምሳሌ በሥዕል 3.3 እንደተመለከታችሁት ዶሮ ዕንቁላል ትጥላለች፣ ዕንቁላሉ ወደ ጫጩትነት ይለወጣል። በመቀጠልም ጫጩቷ አድጋ ዶሮ ትሆናለች። ዶሮዋ የተወሰነ ጊዜ ከኖረች በኋላ ትሞታለች። በተመሳሳይ ሁኔታ የተክል ዘር ከተዘራ ወይም ከተተከለ በኋላ በቅሎ ከዚያም አድጎ በመጨረሻም አርጅቶ ይሞታል።

3. ልኬት



✓ ልጁ የቆመው ምን ላይ ነው?

✓ ምንስ እያደረገ ነው?



✓ ከዚህ ሥዕል ምን ትረዳላችሁ?

ሥዕል 3.4 መጠነ ቁስና (mass) ቁመት ሲለኩ

ተግባር 3.1.7 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- የመጠነ ቁስንና የርዝመትን የልኬት አሐዶች መዘርዘር

መመሪያ- በቡድን በመሆን በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ።

የመወያያ ጥያቄዎች

- የሰው መጠነ ቁስ በምን ይለካል? ቁመቱስ (ርዝመቱ)?
- የመጠነ ቁስና የርዝመት የልኬት አሐዶች ምን ምንድን ናቸው?

የሰው መጠነቁስ መለኪያ መሣሪያ ሚዛን ሲሆን የርዝመት (የቁመት) ደግሞ ረዥም ማስመሪያ ወይም ሜትር ቴፕ ነው። ጊዜ በሰዓት ይለካል። የታወቁት የመጠነ ቁስ፣ የርዝመትና የጊዜ ልኬት አሐዶች የሚከተለት ናቸው።

- **መጠነቁስ**፡- ኪሎ ግራም፣ ግራም
- **ርዝመት**፡- ሜትር፣ ሴንቲ ሜትር
- **ጊዜ**፡- ሰዓት፣ ደቂቃ፣ ሰኮንድ

ተግባር 3.1.8 ☛ ተግባራዊ ክንውን

ዓላማ- መጠነ ቁስንና ቁመትን መለካት


መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን መሥርቱ። ለዚህ ተግባር ክንውን መምህራችሁ ሚዛን፣ ሜትር ቴፕ ወይም ረዥም ማስመሪያ ያቅርቡላችኋል።

- ሚዛን በመጠቀም የእያንዳንዳችሁን መጠነ ቁስ መዝኑ።
- በሜትር ቴፕ ወይም በረዥም ማስመሪያ አማካኝነት የእያንዳንዳችሁን ቁመት ለኩ።
- ቀጥሎ የቀረበውን ሰንጠረዥ በደብተራችሁ ላይ በመገልበጥ የለካችኋቸውን የመጠነቁስና የቁመት መጠን ሙሉ።

ተ.ቁ	የተማሪው ስም	መጠነ ቁስ	ቁመት

- የእያንዳንዱን ተማሪ የመጠነ ቁስና የቁመት መጠን ከሰንጠረዡ በማየት ተመሳሳይነት ያላቸውን ለዩ።

✓ ቀጥሎ የቀረቡትን ሥዕሎች በደንብ ተመልከቱ።



ይህ የምን ሥዕል ነው?
ምንን ለመለካት ያገለግላል?




ሥዕሉ ምንን ያሳያል?
ለምን ተግባር ይውላል?



ይህ የምን ሥዕል ነው?
ለምን ይጠቅማል?



ሥዕሉ ምንን ያሳያል?
የምን መለኪያ ነው?



ሥዕሉ የሚያሳየው ምንን ነው?
የምን መለኪያ ነው?

ሥዕል 3.5 የርዝመት፣ የመጠነቁስና የጊዜ መለኪያዎች

ተግባር 3.1.9 ☛ የቡድን ሥራ

ዓላማ- ባህላዊና ዘመናዊ የመለኪያ መሣሪያዎችን መለየት

መመሪያ- በስዕል 3.5 የቀረቡትን የመለኪያ መሣሪያዎች ባህላዊና ዘመናዊ በማለት መድቡ::

የመለኪያ መሣሪያዎች ባህላዊና ዘመናዊ በመባል ይመደባሉ::

ዘመናዊ የመለኪያ መሣሪያዎች አብዛኛው የዓለማችን ሕዝቦች የሚጠቀሙባቸው ናቸው:: ሰዓት፣ ማስመሪያ፣ ሚዛን፣ ሜትር ቴፕ ዘመናዊ የመለኪያ መሣሪያዎች ናቸው::

ባህላዊ የመለኪያ መሣሪያዎች በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሕዝቦች ለልኬት የሚጠቀሙባቸው የመለኪያ መሣሪያዎች ናቸው:: ስንዝር፣ ክንድ፣ ፈረሱላ፣ ቁና፣ ጋሻና የመሳሰሉት በሀገራችን የሚገኙ ባህላዊ የመለኪያ መሣሪያዎች ናቸው::

4. ቁሳቁሶችን (ዕቃዎችን)መመደብ

✓ ተማሪዎች በአካባቢያችሁ ምን ምን ቁሳቁሶች ይገኛሉ?

ተግባር 3.1.10 ☛ የቡድን ሥራ

ዓላማ- የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ቁሳቁሶችን መለየት

መመሪያ- በሥዕል 3.7 የቀረቡትን ቁሳቁሶች የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ቁሳቁሶች በማለት መድባችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ::


ሀ.


ለ.


ሐ.


መ.


ሠ.

ሥዕል 3.6 የተለያዩ ቁሳቁሶች

ቁሳቁሶች በሁለት ይመደባሉ:: እነሱም:-

ሀ. የተፈጥሮ ቁሳቁሶችና

ለ. ሰው ሠራሽ ቁሳቁሶች ናቸው::

የተፈጥሮ ቁሳቁሶች የሚባሉት በተፈጥሮ የሚገኙ የቁሳቁስ ዓይነቶች ናቸው።

ምሳሌ፡- ድንጋይ፣ እንጨት፣ ጥጥ፣ ገለባ፣ ሱፍና የመሳሰሉት

ሰው ሠራሽ ቁሳቁሶች:- ለተለያዩ ተግባራት የሚውሉና በተፈጥሮ ከሚገኙ ነገሮች የሚሠሩ ናቸው። ለምሳሌ የመኪና ጐማ፣ ፕላስቲክ፣ ብርጭቆና የመሳሰሉት ሰው ሠራሽ ቁሳቁሶች ናቸው።

ቁሳቁሶች በክብደታቸው፣ በዓይነታቸውና በይዘታቸው የተለያዩ ናቸው።

ተግባር 3.1.11 ☛ ተግባራዊ ክንውን

ዓላማ- ቁሳቁሶችን በክብደታቸው፣ በይዘታቸውና በዓይነታቸው መለየት

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን መሥርቱ።

- የሚከተለውን ሰንጠረዥ በደብተራችሁ ገልብጡ።
- መምህራችሁ የሚያቀርቡላችሁን የተለያዩ ቁሳቁሶች በሰንጠረዥ ውስጥ በቀረበው መሠረት በመለየት ሙሉ። ለምሳሌ ያህል አንዱ ተሠርቶላችኋል።

ተ.ቁ	የቁሱ(የዕቃው) ስም	ከባድ	ቀላል	ጠንካራ	ለስላሳ	ሻካራ	ልሙጥ
1	ጥጥ		✓		✓		
2							
3							
4							
5							

መልመጃ 3.1

ሀ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

1. ሌሊት ጨለማ ያለበት ቀዝቃዛና ጸጥ (ረጭ) ያለ የተፈጥሮ ክስተት ነው።
2. በክረምት ወቅት ከሚከሰተው ሀይለኛ ሙቀት የተነሣ የዕፅዋት ቅጠሎች ይረግፋሉ።
3. ድርቅና ጐርፍ በአየር መዛባት ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ የተፈጥሮ ክስተቶች ናቸው።
4. ርዝመት በኪሎ ግራምና በግራም ይለካል።

ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ።

1. ከሚከተሉት ውስጥ ዘመናዊ የመለኪያ መሣሪያ ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ግራም ሐ. ሜትር

ለ. ሥንዝር መ. ሰዓት

2. የፀሀይ ብርሐን በውሃ ጠብታዎች ውስጥ ሲያልፍ የሚፈጠረው የተፈጥሮ ክስተት ምን ይባላል?

ሀ. ድርቅ ሐ. ጎርፍ

ለ. ቀንና ሌሊት መ. ቀስተ ደመና

3. ከሚከተሉት ውስጥ የጊዜ ልኬት አሐድ ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ሴንቲ ሜትር ሐ. ሰዓት

ለ. ሰኮንድ መ. ደቂቃ

ሐ. በ'ሀ' ሥር የቀረቡትን የልኬት ዓይነቶች በ'ለ' ሥር ከቀረቡት የመለኪያ አሐዶች ጋር አዛምዱ::

'ሀ'	'ለ'
1. መጠነ ቁስ	ሀ. ሜትር
2. ርዝመት	ለ. ሰዓት
3. ጊዜ	ሐ. ግራም

መ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::

1. ድርቅ በምን ምክንያት ይከሰታል?
2. የተፈጥሮ ቁሳቁሶች ምንድናቸው?

3.2 የተፈጥሮ ሀብቶች

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት

ተማሪዎች! ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦

- የአካባቢያችሁን የተፈጥሮ ሀብቶች ትዘረዝራላችሁ::
- የተፈጥሮ ሀብቶችን ጥቅሞች ታስረዳላችሁ::
- የተፈጥሮ ሀብቶችን ለመጠበቅ(ለመንከባከብ) የሚረዱ አጠቃላይ ዘዴዎችን ታስረዳላችሁ::
- አካባቢን ለመጠበቅ የታለመውን የአካባቢ ማኅበረሰብ የሥራ ዕቅዶችን ትጠቅሳላችሁ::

ቁልፍ ቃላት

- የተፈጥሮ ሀብት
- የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ/እንክብካቤ
- የተፈጥሮ ሀብት ጠቀሜታ

ሀ. የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶች

- ✓ ተማሪዎች! የተፈጥሮ ሀብትን ምንነት በአንደኛ ክፍል ትምህርታችሁ ተምራችኋል። ታስታውሳላችሁ?
- ✓ የተፈጥሮ ሀብቶች ማለት በተፈጥሮ የሚገኙና ሰዎች ጥቅም ላይ የሚያውሏቸው ሀብቶች ማለት ነው።

ተግባር 3.2.1 ☛ የቡድን ሥራ

ዓላማ- የተፈጥሮ ሀብቶችን መለየት

መመሪያ- በቡድን በመሆን በአካባቢያችሁ የሚገኙትን የተፈጥሮ ሀብቶች በመለየት ዝርዝራቸውን ጻፉ።



ሀ. ሥዕሉ ምንን ያሳያል?



ለ. በሥዕሉ የሚታየው ምንድነው?



ሐ. ይህ የምን ሥዕል ነው?



መ. ከሥዕሉ ምን ትረዳላችሁ?



ሠ. ሥዕሉ ምን ያሳያል?

ሥዕል 3.7 የተፈጥሮ ሀብቶች

የተፈጥሮ ሀብቶች የሚባሉት፡-

- ውሃ
- አፈር
- ዕፅዋት
- ማዕድናት
- አየር
- የቤት እንስሳት
- የዱር እንስሳትና የመሳሰሉት ናቸው።

ሰ. የተፈጥሮ ሀብት ጥቅሞች

ተግባር 3.2.2 ☛ **የቡድን ሥራ**

ዓላማ- የተፈጥሮ ሀብቶችን ጥቅም መዘርዘር።

መመሪያ- በአካባቢያችሁ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች ለምን ለምን ጥቅም እንደሚውሉ ወላጆቻችሁን በመጠየቅ መረጃ ሰብስቡ። በመቀጠልም በቡድን በመሆን በሰበሰባችሁት መረጃ ላይ ተወያዩ።

የተፈጥሮ ሀብቶች ለሰው ልጆች የተለያዩ ጥቅሞችን ይሰጣሉ። ምግብ፣ ልብስና መጠለያ የሚገኙት ከተፈጥሮ ሀብቶች ነው።

ተማሪዎች! ከዚህ በመቀጠል የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብቶች የሚሰጧቸውን ጥቅሞች በዝርዝር ትማራላችሁ።

አፈር

ተግባር 3.2.3 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- ስለ አፈር ጠቀሜታ ማስረዳት

መመሪያ- በቡድን በመሆን በቀረቡት የመወያያ ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ።

የመወያያ ጥያቄዎች

- አፈር ምንድን ነው?
- አፈር ከሌለ ተክሎች ማደግ ይችላሉ? ለምን?

አፈር ማለት በመሬት ገጽ ላይ የሚታይ ከጥቃቅን የድንጋይ ፍርስራሽ፣ ከዕፅዋትና እንስሳት ብስባሽ የሚፈጠር የተፈጥሮ ሀብት ነው። ተክሎች፣ እንስሳትና ሰዎች ያለአፈር መኖር አይችሉም። ተክሎች መብቀልና ማደግ የሚችሉት በአፈር ላይ ነው። እንስሳት በአፈር ላይ የሚበቅሉትን ተክሎች ይመገባሉ። ሰዎች ደግሞ እፅዋትንና እንስሳትን ይመገባሉ። ሰዎች የሚመገቧቸው የተለያዩ ሰብሎች የሚበቅሉትና የሚያድጉት በአፈር ላይ ነው።

ተክሎች፡-

- ለአልባሳት መሥሪያነት ምሳሌ፡- ጥጥ
- መጠለያዎችን ለመገንባት ምሳሌ፡- እንጨት፣ ሣር
- አፈር እንዳይሸረሸር
- ለእንስሳት መጠለያነት
- መድኃኒት ለመሥራትና ለመሳሰሉት ይጠቅማሉ።

ማዕድናት

ተግባር 3.2.4 ☛ **የቡድን ሥራ**

ዓላማ- የማዕድናትን ዓይነትና ጠቀሜታ መግለጽ

መመሪያ- በቡድን በመሆን የተለያዩ የማዕድናት ዓይነቶችንና ጥቅማቸውን ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

ማዕድናት በተፈጥሮ የሚገኙ ሀብቶች ናቸው።

ምሳሌ፡- ወርቅ፣ነዳጅ፣ ጨውና የመሳሰሉት የማዕድን ዓይነቶች ናቸው።

ማዕድናት፡-

- በሀይል ምንጭነት ያገለግላሉ።
  ምሳሌ፡- ነዳጅ
- ለመድኃኒት መሥሪያነት ይውላሉ።
- ለቤት ግንባታ ይጠቅማሉ።
- ለምግብ ዝግጅት ጨው ያገለግላሉ።
  ምሳሌ፡- ጨው
- ተሸጠው ለሀገር ኢኮኖሚ ገንዘብ ያስገኛሉ።

ተፈጥሯዊ የቱሪስት መስህቦች

- ✓ የቱሪስት መስህብ ማለት ምን ማለት ነው?
- ✓ የቱሪስት መስህቦች ማራኪና ልዩ ገጽታ ያላቸው የአንድ አካባቢ የተፈጥሮ ሀብቶች ናቸው።



ሀ. ይህ የምን ሥዕል ነው?



ለ. ሥዕሉ ምንን ያሳያል?



ሐ. በሥዕሉ የሚታዩት ምንድን ናቸው?



መ. ሥዕሉ የሚያሳየው ምንን ነው?

ሥዕል 3.8

ተግባር 3.2.5 ☛ የቡድን ሥራ

ዓላማ- ተፈጥሯዊ የቱሪስት መስህቦችን መዘርዘር

መመሪያ- በቡድን በመሆን በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን በደብተራችሁ ላይ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ።


- በሀገራችን የሚታወቁት ተፈጥሯዊ የቱሪስት መስህቦች እነማን ናቸው?
- በጋራ በመወያየት በሀገራችን ብቻ የሚገኙ ብርቅዬ እንሳስትን ስም ለመምህራችሁ ንገሩ።

ተፈጥሯዊ የቱሪስት መስህቦች ከሚባሉት ውስጥ ጥቂቶቹ፡-

- የውሃ ፏፏቴ
- ልዩ የሆነ የመሬት አቀማመጥ
- ብርቅዬ እንስሳት

ምሳሌ፡- ቀይ ቀበሮ፣ ኒያላ፣ ዋልያ፣ ጭላዳ ዝንጀሮ

- ሐይቆች
- ፍልውሃዎችና የመሳሰሉት ናቸው።






ፏፏቴ ሐይቅ ፍልውሃ ልዩ የመሬት አቀመማመጥ

ሥዕል 3.9

ሐ. የተፈጥሮ ሀብቶችን መጠበቅ(መንከባከብ)

ተግባር 3.2.6 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- የአካባቢ አጠባበቅ ዘዴዎችን ማብራራት

መመሪያ- ከ5-6 ተማሪዎች በቡድን በመሆን በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ ዋና ዋና ሐሳቦችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በዝርዝር ተናገሩ::

የመወያያ ጥያቄዎች

- በአካባቢያችን እየደረሱ ያሉ የተፈጥሮ ሀብት ጉዳቶች ምን ምን ናቸው?
- የተፈጥሮ ሀብት ጉዳቶችን እንዴት መቀነስ ይቻላል? ተወያይታችሁ መልሱን ለመምህራችሁ ንገሩ::

በአካባቢ ላይ እየደረሱ ያሉ ዋና ዋና የተፈጥሮ ሀብት ጉዳቶች:-

- የአየር ብክለት
- የውሃ ብክለት
- የደን መጨፍጨፍ
- የአፈር መሸርሸርና የመሳሰሉት ናቸው::

የአፈር አጠባበቅ ዘዴዎች

አፈር ከተፈጥሮ ሀብቶቻችን አንዱ ነው:: ሕይወት ላላቸው ነገሮች አስፈላጊ መሆኑንም ቀደም ባለው የትምህርት ክፍል ተመልክተናል:: አፈር ከሌለ ተክሎች፣ እንስሳትና ሰዎች መኖር እንደማይችሉ ተምራችኋል:: አስታወሳችሁ?

በአሁኑ ወቅት በሀገራችን በተለያዩ ሥፍራዎች የሚገኘው አፈር በከፍተኛ ሁኔታ ጉዳት እየደረሰበት ይገኛል:: የአፈር መሸርሸር (መከላት) መንሥኤዎች ብዙ ዓይነት ናቸው:: ዋና ዋናዎቹ መንሥዔዎች ጎርፍ፣ ንፋስና የደን መጨፍጨፍ ናቸው::

አፈር እንዳይሸረሸር የሚረዱ የመከላከያ ዘዴዎች፡-

- ችግኞችን መትከል
- የደን መቃጠልን መከላከል
- የደን መጨፍጨፍን መከላከል
- በተዳፋት (ቁልቁለት) ቦታ ላይ እርከን መሥራትና የመሳሰሉት ናቸው።



ሀ) በደን ያልተሸፈነ መሬት



ለ) በደን የተሸፈነ መሬት

ሥዕል 3.10 በደን የተሸፈነና ያልተሸፈነ መሬት

ደኖች በሥሮቻቸው አፈርን አቅፈው በመያዝ አፈርን ከመሸርሸር ይከላከላሉ። ስለዚህም ተማሪዎች! በደን የተሸፈነ መሬት አፈር እንዳይሸረሸር እንደሚረዳ ተገንዘባችሁ?

እርከን መሥራት አፈር እንዳይሸረሸር ከሚረዱ ተግባራት አንዱ ነው። በተዳፋት (ቁልቁለት) ቦታ ላይ እርከን መሥራት አፈር በጎርፍ ታጥቦ እንዳይወሰድ ይጠቅማል።

የደን አጠባበቅ ዘዴዎች

ተግባር 3.2.7 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- የደን አጠባበቅ ዘዴዎችን ማብራራት

መመሪያ- በቡድን ሆናችሁ በቀረቡት የመወያያ ጥያቄዎች ላይ ከተወያያችሁ በኋላ ደብተራችሁ ላይ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ።

የመወያያ ጥያቄዎች

- የደን መጨፍጨፍ ምን ምን ችግሮችን ያስከትላል?
- የደንን መጨፍጨፍ እንዴት መከላከል ይቻላል?

የደን ጥበቃ ማለት ዛፎችን ያለበቂ ምክንያት አለመቁረጥ፣ አለመጨፍጨፍና አለማቃጠል ማለት ነው።
ሰዎች ደንን ለምን ይጨፈጭፋሉ?

ሰዎች ደንን የሚጨፈጭፉት፡-

- ለማገዶ
- የእርሻ ቦታ ለማግኘት
- የግጦሽ ቦታ ፍለጋና ለመሳሰሉት ተግባራት ነው፡፡



ሀ. ደን ሲጨፈጨፍ



ለ. ደን ሲቃጠል

ሥዕል 3.11 የደን ውድመት

የደን መጨፍጨፍ የሚከተሉትን ችግሮች ያስከትላል፡፡

- አፈርን ለመሸርሸር ያጋልጣል፡፡
- የዱር እንስሳትን ለስደት ይዳርጋል፡፡
- ለድርቅና ለጎርፍ እንዲሁም ለመሳሰሉት ችግሮች ያጋልጣል፡፡

የደን ውድመት የሚያስከትላቸውን ችግሮች ከተረዳን ደን እንዳይጨፈጨፍ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል፡፡ የደን ውድመትን ለመከላከል መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ማንኛውንም ዛፍ ያለበቂ ምክንያት አለመቁረጥ
- ደን እንዳይቃጠል ጥንቃቄ ማድረግ
- ለአገልግሎት በተቆረጡ ዛፎች ምትክ ብዙ የዛፍ ችግኞችን መትከልና መንከባከብ



ሥዕል 3.12 ተማሪዎች ችግኞችን ሲንከባከቡ



ሥዕል 3.13 ልጆች ችግኝ ሲተክሉ

ተግባር 3.2.8 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- የችግኞችን ተከላ አስፈላጊነት መግለፅ

መመሪያ- በቡድን ሆናችሁ በቀረቡት የመወያያ ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን ወረቀት ላይ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ::

የመወያያ ጥያቄዎች

- ከሥዕል 3.13 ምን ተገነዘባችሁ?
- ልጆቹ ጥሩ ተግባር እየፈጸሙ ነው? ለምን?
- እናንተስ በትምህርት ቤታችሁ በችግኝ ተከላ ሥራ ላይ ትሳተፋላችሁ? ከዚህ አኳያ ለወደፊት ምን ለማድረግ ታስባላችሁ?

ተማሪዎች በሥዕሉ እንደተመለከታችሁት በተቆረጡ ዛፎች ምትክ ችግኝ መትከልና ለእርሻ ባልዋሉ ተራራማ ቦታዎች የዛፍ ችግኝ መትከል የደን ሀብት እንዳይመናመን የሚረዳ ተግባር ነው:: ስለዚህ በትምህርት ቤታችሁ ወይም በመኖሪያ ቤታችሁ አካባቢ የአትክልት ቦታን በማዘጋጀት የአፈር መሸርሸርን መከላከል ትችላላችሁ:: በአትክልት ቦታዎች ላይ ችግኞችን በማብቀል ወደ ተራቆቱ መሬቶች ወስዶ በመትከልና በሥሮቻቸው አፈርን አቅፈው እንዲይዙ በማድረግ የአፈር መሸርሸርን መከላከል ይቻላል::

የውሃ ብክለትን ለመከላከል የሚረዱ ዘዴዎች

ተግባር 3.2.9 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- የውሃ ብክለት መከላከያ ዘዴዎችን ማስረዳት

መመሪያ- ከ4 -6 ተማሪዎች በቡድን በመሆን በቀረቡት የመወያያ ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሶቻችሁን በዝርዝር ለመምህራችሁ አቅርቡ።

የመወያያ ጥያቄዎች

- ውሃን ለብክለት የሚዳርጉ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?
- የተበከለ ውሃን መጠቀም ምን ጉዳት ያስከትላል?
- ውሃን እንዴት በንጽሕና መጠበቅ ይቻላል?


ውሃን በተፈጥሮ ከምንጭ፣ ከወንዝ፣ ከሐይቅና ከዝናብ እናገኛለን። እነዚህ የውሃ መገኛዎች በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ ደረጃ እየተበከሉ ናቸው። የውሃ ብክለት መንሥዔዎች ብዙ ዓይነት ቢሆኑም ዋነኛው የአካባቢ ቆሻሻ ነው።

የአካባቢ ቆሻሻ፡-

- የቤት ጥራጊና የእቃ እጣቢዎችን
- በየቦታውና በየወንዙ መፀዳዳት የሚያስከትለው ቆሻሻ
- ከፋብሪካ የሚወገዱ ቆሻሻዎችንና የመሳሰሉትን ያካትታል።

የውሃን ብክለት፡-

- የቤት ጥራጊንና የእቃ እጣቢዎችን በአግባቡ በማስወገድ
- በመጸዳጃ ቤት ብቻ በመጸዳዳት
- ከፋብሪካ የሚወጡ ውኃጆችን በተገቢው መንገድ በማስወገድ መከላከል ይቻላል።



ሥዕል 3.14 ቆሻሻ በአግባቡ ሲወገድ

ውሃ ከፋብሪካዎች በሚወጡ ልዩ ልዩ መርዛማ ፈሳሾች ሊመረዝ ይችላል። ለምሳሌ የአቃቂ ወንዝ ከፋብሪካዎች በሚወጣ ፈሳሽ ይበከላል። ይህም ለሰው ጤና ጠንቅ ይሆናል።

ተግባር 3.2.10 ☛ በግል የሚከናወን ተግባር

ዓላማ- የፋብሪካ ቆሻሻዎች የአወጋገድ ዘዴዎችን መግለጽ

መመሪያ- ከፋብሪካ የሚወጡ ውጋጆች ወደ ወንዝ ከመለቀቃቸው በፊት ምን መደረግ እንዳለበት ወላጆቻችሁንና ታላላቆቻችሁን ጠይቃችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

የአየር ብክለትን ለመቀነስ የሚረዱ ዘዴዎች

ተግባር 3.2.11 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- የአየር ብክለት ምንጮች መለየት

መመሪያ- ከ4 - 6 ተማሪዎች በቡድን በመሆን በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ።

የመወያያ ጥያቄዎች-

- ተማሪዎች አካባቢያችሁ በጭስ ቢታፈን ምን ችግር ይገጥማችኋል?
- አየር በምን በምን ሊበከል ይችላል?

የሚከተሉትን ሥዕሎች በጥንቃቄ ተመልከቱ።



ሀ. የፋብሪካ ጭስ



ለ. የመኪና ጭስ



ሐ. የከሰል ጭስ

ሥዕል 3.15 የአየር ብክለት ምንጮች

በሥዕል 3.15 ላይ የምታዩአቸው ሥዕሎች ምንን ያሳያሉ? ምን ችግር ያስከትላሉ?

አየር ሕይወት ላላቸው ነገሮች ሁሉ አስፈላጊ ነው። አየር ከተበከለ በሰው፣ በእንስሳትና በዕፅዋት ላይ ጉዳት ይደርሳል። ብክለቱ የሚከሰተው በአብዛኛው ጎጂ የሆነ ጭስ ወደ አየር ሲገባ ነው።

ከፋብሪካ፣ ከተለያዩ ተሽከርካሪዎችና ከሰል በሚቀጣጠልበት ጊዜ የሚወጣው ጭስ አየርን ይበክላል። በጠባብ ክፍል ውስጥ በደንብ ያልተቀጣጠለ ከሰል በማንደጃ አድርጎ በርና መስኮቶችን ዘግቶ መቆየት ለሕይወት አደገኛ ነው። ይህን ወደ አካባቢ የሚለቀቅ ጎጂ ጭስ በመቀነስ የአየር ብክለትን መከላከል ይቻላል። ይኸውም ጭስ አልባ የኃይል ምንጮችን በመጠቀም ወይም አነስተኛ ጭስ ሊለቁ የሚችሉ ተሽከርካሪዎችንና ፋብሪካዎችን ጥቅም ላይ በማዋል ነው።

መልመጃ 3.2

ሀ. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

1. ሰዎችና እንስሳት ያለ አፈር መኖር አይችሉም።
2. የቱሪስት መስህቦች ለአንድ ሀገር የኢኮኖሚ እድገት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።
3. ጎርፍና ንፋስ ለአፈር መሸርሸር መንሥዔ ሊሆኑ አይችሉም።
4. ለእርሻ ባልዋሉ ተራራማ ቦታዎች የዛፍ ችግኝ መትከል የደን ሀብት እንዳይመናመን ይረዳል።
5. በጠባብ ክፍል ውስጥ በደንብ ያልተቀጣጠለ ከሰል በማንደጃ አድርጎ በር ዘግቶ መቆየት ለሕይወት አደገኛ ነው።

ለ. ለየሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ።

1. ተፈጥሯዊ የቱሪስት መስህብ ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ፍል ውሀ ሐ. ሐይቅ
   ለ. ሐውልት መ. የመሬት አቀማመጥ
2. ከሚከተለት ውስጥ የአፈርን መሸርሸር ለመከላከል የሚያስችለው የትኛው ነው?
   ሀ. ችግኞችን መትከል ሐ. ደንን መጨፍጨፍ
   ለ. ቁልቁል ማረስ መ. ደንን ማቃጠል
3. የደን መጨፍጨፍ ምን ያስከትላል?
   ሀ. የአፈር መሸርሸር ሐ. ድርቅና ጎርፍ
   ለ. የዱር እንስሳት ስደት መ. ሁሉም መልስ ናቸው።
4. የውሃ ብክለት መንሥዔ ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. የቤት ጥራጊና የፅቃ እጣቢ ሐ. በየቦታውና በየወንዙ መጸዳዳት
   ለ. ከተሽከርካሪዎች የሚወጣ ጭስ መ. የፋብሪካዎች ውጋጅ

5. የተፈጥሮ ሀብት ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ውሃ ሐ. ማዕድን

ለ. አየር መ. መልሱ አልተሰጠም

ሐ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. የተፈጥሮ ሀብት ማለት ምን ማለት ነው?
2. ደንን መንከባከብ የምንችለው ምን ምን በማድረግ ነው?

3.3 በዙሪያችን የሚገኙ ተክሎች

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት

ተማሪዎች! ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- የተክል ክፍሎችን ስሞች እየጠቀሳችሁ ታሳያላችሁ።
- የተክል ክፍሎችን ተግባራት ትናገራላችሁ።
- የተክል ክፍሎችን በመሰብሰብ ትለያላችሁ።
- ተክሎች ለዕድገት ምን እንደሚያስፈልጋቸው ታመለክታላችሁ።
- ሰብሎችን ለማብቀል የሚረዱ ዕቃዎችንና መሣሪያዎችን ታመለክታላችሁ።

ቁልፍ ቃላት

- የተክል ክፍል
- ሰብል
- ብቅለት

የተክል ክፍሎች

ሀ. የተክል ክፍሎችና ተግባራቸው

ተግባር 3.3.1 ☛ የቡድን ሥራ


ዓላማ- የተክል ክፍሎችን መለየት

መመሪያ- በቡድን በመሆን ከክፍላችሁ ወጣ ብላችሁ በአካባቢያችሁ ያሉ ተክሎችን ተመልከቱ።

- ከተመለከታችኋቸው ተክሎች አንዱን መርጣችሁ በመሣል የተለያዩ ክፍሎችን በሥዕሉ ላይ በማመልከት ለመምህራችሁ አሳዩ።

ተክሎች ሕይወት ካላቸው ነገሮች ውስጥ ይመደባሉ። በሥዕሉ ላይ እንደተመለከታችሁት ተክሎች የተለያዩ ክፍሎች አሏቸው። እነርሱም፡-

- ግንድ
- ቅጠል
- አበባና
- ሥር ናቸው።



ሥዕል 3.16 የተክል ክፍሎች



ሥዕል 3.17 የተለያዩ ተክሎች

ከሥዕል 3.17 እንደምትረዱ ተክሎች በመጠናቸውና በቅጠላቸው እንዲሁም በተፈጥሮአዊ ሁኔታዎች የተለያዩ ናቸው። የአካል ክፍሎቻቸውም በቅርጻቸውና በመጠናቸው ይለያያሉ።

የተክሎች ምደባ

ተግባር 3.3.2 ☛ የቡድን ሥራ

ዓላማ-ተክሎችን መመደብ

መመሪያ- በቡድን በመሆን ከዚህ በታች የቀረቡትን ተግባራት በማከናወን ለመምህራችሁ አሳዩ።

- በትምህርት ቤታችሁ ዙሪያ ያሉ ተክሎችን በመመልከት በቁመታቸው፣ በቅጠላቸው ስፋትና ጥበት እንዲሁም ሌሎች መመዘኛዎችን በመጠቀም መድቧቸው።
- በመቀጠልም ለእያንዳንዱ ምድብ ቁጥር በመስጠት በደብተራችሁ ላይ ልዩነቶቹን በመጻፍ የቡድናችሁን ሥራ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

ተክሎችን በመጠናቸው መሠረት ትላልቅ፣ መካከለኛና ትናንሽ ብለን እንመድባቸዋለን፡፡




ሥዕል 3.18 ትላልቅ ዛፎች

ከላይ በሥዕል 3.18 የምትመለከቷቸው ተክሎች ትላልቅ ዛፎች ናቸው፡፡ በጣም ትላልቅና በጣም ረዥም፣ አንዳንዶቹ ቅጠሎች ሰፋፊ ሌሎቹ ደግሞ መርፌ መሰል ቀጫጭን ቅጠሎች አሏቸው፡፡



ሥዕል 3.19 መካከለኛ መጠን ያላቸው ዛፎች

ከላይ በሥዕሉ ላይ የምትመለከቷቸው መካከለኛ መጠን ያላቸው ተክሎች ናቸው፡፡





ሥዕል 3.20 ትናንሽ ተክሎች

ተግባር 3.3.3 ☛ **የቡድን ሥራ**

ዓላማ- የቅጠል ሕትመት ማዘጋጀት

መመሪያ- በትምህርት ቤታችሁ አካባቢ በመዘዋወር የተለያዩ ቅጠሎችን ሰብስቡ።

- ከሰበሰባችኋቸው ቅጠሎች አንዳንዶቹን በመጣል ቀላል የቅጠል ሕትመት ሥራ ሠርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

ተግባር 3.3.4 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- የተክል ክፍሎችን ተግባራት ማስረዳት

መመሪያ- በቡድን በመሆን ተወያይታችሁ መልሳችሁን ለመምህራችሁ ንገሩ።

የመወያያ ጥያቄ

የተክል ክፍሎች ተግባራት ምን ምን ናቸው?

በተክሎች ውስጥ የሚገኙ ተመሳሳይ የአካል ክፍሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ያከናውናሉ። በአካባቢያችሁ ተዘዋውራችሁ እንደተመለከታችሁት ተክሎች ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች አሏቸው። እነርሱም:-

1. ከመሬት በላይ የሚገኙት የተክል ክፍሎች
   - ግንድ
   - ቅጠልና
   - አበባ ሲሆኑ
2. ከመሬት በታች የሚገኘው የተክል ክፍል ደግሞ ሥር ነው።

ተማሪዎች! ከዚህ በመቀጠል የተክል ክፍሎች የሚያከናውኗቸውን ዋና ዋና ተግባራት ትማራላችሁ።

ግንድ



ተክሎች የተለያየ ዓይነት ግንድ ሊኖራቸው ይችላል። ይሁን እንጂ ማንኛውም ዓይነት ግንድ ለተክሉ የሚሰጠው ጥቅም ተመሳሳይ ነው። ይኸውም:-

- የተክሎችን ቅጠሎችና ቅርንጫፎች ይሸከማል።
- ውሃንና ማዕድናትን ወደ ቅጠሎችና ቅርንጫፎች ያደርሳል።
- የተዘጋጀ ምግብን ከቅጠሎች ወደ ሌሎች የተክል ክፍሎች እንዲሰራጭ ያደርጋል።
- የአንዳንድ ተክሎች ግንዶች ለምግብ ማከማቻነት ያገለግላሉ።

ቅጠል



ሥዕል 3.21 የተለያዩ ቅጠሎች

ከስዕሉ እንደምትመለከቱት ቅጠሎች በመጠናቸው፣ በቅርጻቸውና በጠርዞቻቸው ይለያያሉ። የቅጠል ዋና ተግባር ለተክሉ ምግብ ማዘጋጀት ነው።

አበባ



ሥዕል 3.22 የተለያዩ ቅርጽ፣ መጠንና ቀለም ያሳችው አበቦች

አበቦች በቅርጻቸው፣ በመጠናቸው፣ በቀለማቸውና በሽታቸው ይለያያሉ።

አበቦች፡-

- የመራቢያ ክፍሎች ስለሆኑ ተክሎች እንዲራቡ ያደርጋሉ።
- ዘርና ፍሬ የሚፈጠሩባቸው የተክል ክፍሎች ናቸው።

ሥር





ተክሎች የተለያየ ዓይነት ሥር ቢኖራቸውም የሚያከናውኗቸው ተግባራት ግን ተመሳሳይ ናቸው።

ሥር፡-

- ተክሎች ቀጥ ብለው እንዲቆሙ ከመሬት ጋር አጣብቆ ይይዛል፡፡
- ውሃና ሌሎች ሟሟ ማዕድናትን ወደ ግንድ ያስተላልፋል፡፡
- ለአንዳንድ ተክሎች በምግብ ማከማቻነት ያገለግላል፡፡

ስ. ተክሎችን ማብቀል

ተግባር 3.3.5 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- ለተክሎች እድገት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን መለየት

መመሪያ- በቡድን በመሆን በቀረበው መወያያ ጥያቄ ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን በደብተራችሁ ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

የመወያያ ጥያቄ

- ለተክሎች ዕድገት ምን ምን ያስፈልጋል?

ለተክሎች ዕድገት አስፈላጊ ነገሮች፡-

- አየር
- ውሃ
- የፀሐይ ብርሐንና
- አፈር ናቸው፡፡

ከእነዚህ አስፈላጊ ነገሮች አንዱ እንኳን ቢጎድል ተክሎች ማደግ አይችሉም፡፡ ይህንን ሁኔታ በሙከራ ማረጋገጥ ትችላላችሁ፡፡

ተማሪዎች! ሙከራውን ከማከናወናችሁ በፊት የአየርን፣ የውሃን፣ የፀሐይ ብርሐንንና የአፈርን ጥቅም አንድ በአንድ እንመልከት::

አየር

ተክሎች ምግባቸውን ለማዘጋጀት አየር ያስፈልጋቸዋል፡፡ ተክሎችም ጉልበትን ከምግብ ለማመንጨት አየር ይጠቀማሉ፡፡

አፈር

- ተክሎች ምግባቸውን ለማዘጋጀትና ለማደግ የሚረዳቸውን ውሃ እንዲሁም አልሚ ምግብ የሚያገኙት ከአፈር ነው፡፡
- አፈር የተክሎችን ስሮች አቅፎ በመያዝ ቀጥ ብለው እንዲያድጉ ያደርጋል፡፡

ብርሃን

- ተክሎች ምግባቸውን ለማዘጋጀት የጉልበት ምንጭ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ይህም የጉልበት ምንጭ የፀሐይ ብርሐን ነው፡፡

ውሃ

- በቅጠል ውስጥ ምግብ እንዲዘጋጅ ይረዳል።
- ምግብ በተክል ውስጥ እንዲዘዋወር ያደርጋል።
- ለተክል ዕድገት አስፈላጊ የሆኑትን አልሚ ምግቦችን ያሟሟል።
- ተክሎች ያላቸውን ቅርጽ ይዘው ቀጥ ብለው ሳይጠወልጉ እንዲቆዩ ያደርጋል።

ተማሪዎች! ቀጥሎ ውሃ፣ አየር፣ አፈርና የፀሐይ ብርሐን ለተክሎች አስፈላጊ መሆናቸውን በሙከራ ታረጋግጣላችሁ። የቀረበውን ሙከራ በተሰጠው መመሪያ መሠረት በጥንቃቄ አከናውኑ። የሙከራውን ውጤትም በደብተራችሁ ጻፉ።

ተግባር 3.3.6 ☛ ተግባራዊ ክንውን

ዓላማ- አየር፣ ውሃና የፀሐይ ብርሐን ለዕፅዋት እድገት እንደሚያስፈልጉ በሙከራ ማረጋገጥ

መመሪያ- በቡድን በቡድን በመሆን ከዚህ በታች የቀረበውን ሙከራ አከናውኑ

ለሙከራው የሚያስፈልጉ ቁሣቁሶች

- አራት በዕቃ ላይ የበቀሉ ችግኞች
- ላስቲክ
- ውሃ
- ቁም ሳጥን

የሙከራው አሠራር

- የመጀመሪያውን ችግኝ ውሃ፣ አየርና የፀሐይ ብርሐን በሚያገኝበት ሥፍራ አስቀምጡ።
- ሁለተኛውን ችግኝ አየርና የፀሐይ ብርሐን ብቻ እንዲያገኝ አድርጉ።
- ሦስተኛውን ችግኝ በላስቲክ በመሸፈን ውሃና የፀሐይ ብርሐን ብቻ እንዲያገኝ አድርጉ።
- አራተኛውን ችግኝ ውሃና አየር እንዲያገኝ አድርጋችሁ ቁም ሳጥን ውስጥ አስቀምጡ።

ተማሪዎች! ከአንድ ሳምንት በኋላ ችግኞቹን በመመልከት ያሉበትን ሁኔታ በሥዕል ግለጹ።

- ሙከራውን ካከናወናችሁ በኋላ ባገኛችሁት ውጤት ላይ በመመርኮዝ ተወያዩ። በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ ዝርዝሩን ለመምህራችሁ አቅርቡ።

ተክሎችን ለማብቀል የሚረዱ ቁሳቁሶች

ተግባር 3.3.7 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- የተክል ማብቀያ ቁሳቁሶችን መለየት

መመሪያ- አምስት አባላት ያለት ቡድን በመመሥረት በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አሳዩ::

- ተክሎችን ለማብቀል ምን ምን ቁሳቁሶች ያስፈልጋሉ?
- የዘረዘራችኋቸው ቁሳቁሶች ለምን ለምን ይጠቅማሉ?

ተክልን ለማብቀል የሚረዱ ዋና ዋና መሣሪያዎች:-

- መቆፈሪያ
- አካፋ
- መኮትኮቻ
- ውሃ ማጠጫ
- መስመር ማውጫ
- ማንገዋለያና መቧጠጫ
- ጋሪ ናቸው::

✓ የሚከተሉትን ሥዕሎች በጥንቃቄ ተመልከቱ::



ይህ የምን ሥዕል ነው?
ለምን ይጠቅማል?



በሥዕሉ የምታዩት ምንድነው?
ለምን አገልግሎት ይውላል?



ይህ የምን ሥዕል ነው?
ለምን ይጠቅማል?



ይህ የምን ሥዕል ነው?
ለምን የሚያገለግል ይመስላችኋል?



ሥዕሉ ምንን ያሳያል?
ጥቅሙ ምንድነው?

ሥዕል 3.23 ተክልን ለማብቀል የሚረዱ ዋና ዋና መሣሪያዎች

ደማ

ደማ ዘር ከመዘራቱ ወይም ችግኝ ከመተከሉ በፊት መሬትን ቆፍሮ ለማለስለስ የሚረዳ መሣሪያ ነው።

አካፋ

አካፋ አፈር ለመዛቅና ለማንሳት የሚጠቅም መሣሪያ ነው።

ውሃ ማጠጫ

ከፕላስቲክ ወይም ከቆርቆሮ የተሰራ ወንፊት ያለው አትክልቶችን ውሃ ለማጠጣት የሚጠቅም መሣሪያ ነው።

መስመር ማውጫ

መስመር ማውጫ ብዙ ጣቶች ያሉት ከብረት ወይም ከእንጨት የተሠራ ሆኖ በሰብል ማብቀያው መደብ ላይ ቀጥ ያሉ መስመሮችን ለማውጣት የሚጠቅም ነው። መስመሮቹን ተከትሎ ዘር ለመዝራት ወይም ችግኝ ለመትከል ያገለግላል።

ጋሪ

ማጓጓዣ ወይም ጋሪ ፍግና (ማዳበሪያ) ችግኞችን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለማጓጓዝ የሚረዳ መሣሪያ ነው።

መልመጃ 3.3

ሀ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

1. ጥድ ባሕር ዛፍና ዋንዛ በትላልቅ ተክሎች ውስጥ ይመደባሉ።
2. የቅጠል ዋና ተግባር ለተክሉ ምግብ ማዘጋጀት ነው።
3. አካፋ አፈር ለመዛቅና ለማንሳት የሚጠቅም መሣሪያ ነው።
4. አየር ተክሎች ምግባቸውን እንዲያዘጋጁና ጉልበት ማመንጨት እንዲችሉ ይረዳቸዋል።

ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ።

1. ከመሬት በላይ በሚገኙት የተክል ክፍሎች ውስጥ የማይካተተው የትኛው ነው?

   ሀ. ቅጠል ለ. ሥር ሐ. ግንድ መ. አበባ

2. ከሚከተሉት የአበባ ጥቅም የሆነው የትኛው ነው?

   ሀ. የተዘጋጀን ምግብ ከቅጠል ወደ ሌሎች የተክል ክፍሎች ማድረስ

   ለ. ለተክሉ ምግብ ማዘጋጀት

   ሐ. ተክሉ እንዲራባ ማድረግ

   መ. የተክሉን ቅጠሎችና ቅርንጫፎች መሸከም

ሐ. ባዶ ቦታዎችን በተስማሚ ቃል ወይም ቃላት ሙሉ::

1. ለተክሎች ዕድገት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች _____ _____ _____ ና _____ናቸው::
2. ውሃንና ሚሚ ማዕድናትን ወደ ግንድ የሚያስተላልፈው የተክል ክፍል _____ ነው
3. ተክሎችን ለማብቀል ከምንጠቀምባቸው መሣሪያዎች ውስጥ መሬትን ለመቆፈርና ለማለስለስ የሚያገለግለው_____ ነው::

3.4 በዙሪያችን የሚገኙ እንስሳት

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- እንስሳትን በአረባባቸው መሠረት ትመድባላችሁ::
- እንስሳትን በአመጋገባቸው መሠረት ትመድባላችሁ::
- እንስሳትን በእንቅስቃሴያቸው መሠረት ትመድባላችሁ::
- እንስሳትን በመኖሪያ ሥፍራቸው መሠረት ትመድባላችሁ::
- እንስሳትን በሰውነት ሽፋናቸው መሠረት ትመድባላችሁ::
- ከእንስሳት ውጤቶች የሚሠሩ ነገሮችን ትለያላችሁ::
- ለእርሻ እንስሳት እንክብካቤ (አያያዝ) የሚረዱ ቁሳቁሶችን ትዘረዝራላችሁ::
- ለእንስሳት እንክብካቤ የሚረዱ ቁሳቁሶችን ተግባራት ታሳያላችሁ::

ቁልፍ ቃላት

- እንስሳት
- የእንስሳት ውጤቶች
- የእንስሳት እንክብካቤ

ሀ. እንስሳትን መመደብ

ተግባር 3.4.1 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- በአካባቢ የሚገኙ እንስሳትን መመደብ

መመሪያ- በቡድን በመሆን በቀረቡት የመወያያ ነጥቦች መሠረት ተወያይታችሁ መልሳችሁን በደብተራችሁ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ::

የመወያያ ነጥቦች

- በአካባቢያችሁ የሚገኙ እንስሳትን ስም ዘርዝሩ::
- እንስሳት በምን በምን ባህርያት ሊመደቡ እንደሚችሉ በዝርዝር ጻፉ::

በአካባቢያችሁ የሚገኙ እንስሳት

- በአረባባቸው
- በእንቅስቃሴያቸው
- በአመጋገባቸው
- በመኖሪያ ሥፍራቸው
- በሰውነት ሽፋናቸው መሠረት ሊመደቡ ይችላሉ።

እንስሳትን በአረባባቸው መሠረት መመደብ

ተግባር 3.4.2 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- እንስሳትን በአረባባቸው መሠረት መመደብ

መመሪያ- በቡድን በመሆን በተግባር 3.4.1 የዘረዘራችኋቸውን እንስሳት እንቁላል የሚጥሉና የሚወልዱ በማለት መድቧቸው።

- የመደባችኋቸውን እንስሳት ሥዕሎች በመሳል በእያንዳንዱ ሥዕል ሥር የእንስሳውን ስም ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

እንስሳት በአረባባቸው መሠረት በሁለት ይመደባሉ። እነርሱም፦

ልጅ የሚወልዱ እንስሳት እና እንቁላል የሚጥሉ ናቸው።

ልጅ የሚወልዱ እንስሳት፦ እነዚህ አምሳያቸውን በመውለድ የሚተኩ የእንስሳት ዓይነት ናቸው። አምሳያቸውን የሚወልዱ እንስሳት እስኪወልዱ ድረስ ልጆቻቸውን በማኅፀናቸው በመያዝ እንዲያድጉ ያደርጋሉ። ከወለዱም በኋላ ራሳቸውን እስከሚችሉ ድረስ ጡት እያጠቡ ያሳድጓቸዋል።

ምሳሌ፦ ላም፣ አንበሳ፣ ድመት፣ ጅብና የመሳሰሉት

እንቁላል የሚጥሉ እንስሳት፦የእነዚህ እንስሳት ልጆች ተፈልፍለው እስከሚወጡ ድረስ የሚፈጠሩትና የሚያድጉት በእንስሳቱ እንቁላሎች ውስጥ ነው።

ምሳሌ፦ ዶሮ፣ ወፍ፣ እባብ፣ እንቁራሪትና የመሳሰሉት

እንስሳትን በእንቅስቃሴያቸው መሠረት መመደብ

ተግባር 3.4.3 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- እንስሳትን በእንቅስቃሴያቸው መሠረት መመደብ

መመሪያ-

- በአካባቢያችሁ የሚገኙትን እንስሳት ስም ዘርዝሩ፡፡ እንስሳቱን በሰማይ ላይ የሚበሩ፣ በመሬት ላይ የሚሳቡ፣ በእግራቸው የሚራመዱና በውሃ ውስጥ የሚዋኙ በማለት ለይታችሁ መድቧቸው፡፡
- የሚከተለውን ሰንጠረዥ በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ በተራ ቁጥር አንድ በተሰጣችሁ ምሳሌ መሠረት ሰንጠረዡን ሙሉ፡፡

ተ.ቁ	በሰማይ ላይ የሚበረ	በመሬት ላይ የሚሳቡ	በእግራቸው የሚራመዱ	በውሃ ውስጥ የሚዋኙ
1	ወፍ	እባብ	ሰው	አሳ
2				
3				
4				
5				

እንስሳትን በአመጋገባቸው መሠረት መመደብ

ተግባር 3.4.4 ☛ **የቡድን ሥራ**

ዓላማ- እንስሳትን በአመጋገባቸው መሠረት መመደብ

መመሪያ- በቡድን በመሆን በተግባር 3.4.3 ውስጥ የተጠቀሱትን እንስሳት ዕፅዋት በል፣ ሥጋ በልና ዕፅዋትና ሥጋ በል በማለት መድቧቸው፡፡

- ከእያንዳንዱ ምድብ አንድ እንስሳ በመምረጥ ሥዕሉን ስላችሁ ለመምራችሁ አሳዩ፡፡

እንስሳት በአመጋገባቸው መሠረት በሦስት ይመደባሉ፡፡

- **ሥጋ በል እንስሳት:-** የሌሎች እንስሳትን ሥጋ በጥርሳቸው በመዘንጠል፣በማኘክና አጥንታቸውን በመቆረጣጠም ይመገባሉ፡፡
  ምሳሌ:- አንበሳ፣ ውሻ፣ ነብርና የመሳሰሉት
- **ዕፅዋት በል እንስሳት:-** ሳርን በመንጨትና ቅጠላ ቅጠልን በመቀንጠስ በጥርሳቸው አኝከው ይመገባሉ፡፡
  ምሳሌ:- ላም፣ ፍየል፣ ግመል፣ ቀጭኔና የመሳሰሉት
- **ሥጋና ዕፅዋት በል እንስሳት:-** ሁለቱንም ዓይነት የሚመገቡ ናቸው::
  ምሳሌ:- ሰው፣ አይጥ ፣ ዝንጀሮ የመሳሰሉት

እንስሳትን በመኖሪያ ሥፍራቸው መመደብ

ተግባር 3.4.5 ☛ የቡድን ሥራ

ዓላማ- እንስሳትን በመኖሪያ ሥፍራቸው መሠረት መመደብ

መመሪያ- በተግባር 3.4.3 ውስጥ የተዘረዘሩትን እንስሳት በመሬት ላይ የሚኖሩ፣ በውሃ ውስጥ የሚኖሩና በመሬትም በውሃም ውስጥ የሚኖሩ ብላችሁ በመለየት በሚከተለው ሰንጠረዥ ሙሉ። ከእያንዳንዱ ምድብ አንዳንድ የእንስሳ ሥዕል በመሣል ለመምህራችሁ አሳዩ።

ተ.ቁ	በመሬት ላይ የሚኖሩ	በውሃ ውስጥ የሚኖሩ	በመሬትም በውሃም ውስጥ የሚኖሩ
1	አንበሳ	ዓሳ	ጉርጥ
2			
3			
4			
5			

እንስሳትን በሰውነት ሽፋናቸው መሠረት መመደብ

ተግባር 3.4.6 ☛ የቡድን ሥራ

ዓላማ- እንስሳትን በሰውነት ሽፋናቸው መሠረት መመደብ

መመሪያ- በተግባር 3.4.3 ውስጥ የተዘረዘሩትን እንስሳት በላባ የተሸፈኑ፣ በቅርፊት የተሸፈኑና በፀጉር የተሸፈኑ በማለት ሰንጠረዥ አዘጋጅታችሁ መድቧቸው።

- ከእያንዳንዱ ምድብ አንድ እንስሳ በመምረጥ ስዕሉን ስላችሁ ለመምራችሁ አሳዩ።

.

እንስሳት በሰውነት ሽፋናቸው መሠረት በሦስት ይመደባሉ። እነርሱም፦

- በላባ የተሸፈኑ

  ምሳሌ፦ ዶሮ፣ ወፍ፣ ቆቅ፣ አሞራ የመሳሰሉት
- በፀጉር የተሸፈኑ

  ምሳሌ፦ ላም፣ ውሻ፣ ዝሆን፣ አይጥ የመሳሰሉት
- በቅርፊት የተሸፈኑ

  ምሳሌ፦ እባብ፣ እንሽላሊት፣ አዞ፣ አሳና የመሳሰሉት ናቸው።





ሥዕል 3.24 የተለያየ የሰውነት ሽፋን ያላቸው እንስሳት

ለ. ከእንስሳት ውጤቶች የሚሠሩ ነገሮች

ተግባር 3.4.7 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- የእንስሳትን ጥቅም መዘርዘር

መመሪያ- በቡድን በመሆን ተወያይታችሁ መልሳችሁን ለመምህራችሁ ንገሩ።

የመወያያ ጥያቄዎች

- እንስሳት ለምን ለምን ይጠቅማሉ?
- የእንስሳት ውጤቶች የምንላቸው ምን ምን ናቸው?
- ከእንስሳት ውጤቶች ምን ምን ይሠራል?

እንስሳት የተለያዩ ጥቅሞች አሏቸው። ከሚሰጧቸው ጥቅሞች ዋና ዋናዎቹ፦

- ለምግብነት
- ልብሶችን ለመሥራት
- ለጉልበት ሥራ (ለእርሻ)
- ለጥበቃ
- ለመዝናኛነት
- በመጓጓዣነት
- በገቢ ምንጭነት ናቸው።

ተግባር 3.4.8 ☛ **የቡድን ሥራ**

ዓላማ- ከእንስሳት ውጤቶች የሚሠሩ ነገሮችን መለየት

መመሪያ- በአካባቢያችሁ የሚገኙትን የእንስሳት ውጤቶች በቡድን በመሆን የቆዳ ውጤቶች፣ የወተት ውጤቶችና የፀጉር(የሱፍ) ውጤቶች በማለት መድባችሁ በሚከተለው ሠንጠረዥ መሰረት ሙሉ። የተዘጋጀውን ሰንጠረዥ ለመምህራችሁ አሳዩ።

ተ.ቁ	የወተት ውጤቶች	የቆዳ ውጤቶች	የሱፍ (የፀጉር) ውጤቶች
1	ቅቤ	ቀበቶ	ብርድ ልብስ
2			
3			
4			
5			

ሐ. ለእርሻ እንስሳት እንክብካቤ የሚጠቅሙ ቁሳቁሶች

ተግባር 3.4.9 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- የእርሻ እንስሳትን መንከባከብ

መመሪያ- በቡድን በመሆን በመወያያ ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሱን በጽሑፍ ለመምህራችሁ አሳዩ።

የመወያያ ጥያቄዎች

- የእርሻ እንስሳትን መንከባከብ ለምን ያስፈልጋል?
- የእርሻ እንስሳትን እንዴት መንከባከብ አለብን?
- የእርሻ እንስሳትን ለመንከባከብ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ምን ምንድናቸው?

እንስሳትን መንከባከብ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም እንስሳት ለሰው ልጆች ተገቢውን አገልግሎት መስጠት የሚያስችላቸው ሆነው እንዲገኙ ነው።

የእርሻ እንስሳትን የምንከባከበው፡-

- ጥሩ መኖ (ምግብ) በመመገብ
- ምቹ መጠለያ በማዘጋጀት
- ንጽሕናቸውን በመጠበቅ
- ርህራሄ በማሳየት ነው።

የእርሻ እንስሳትን ለመንከባከብ ከሚያስፈልጉ ቁሣቁሶች ዋና ዋናዎቹ፡-

- **ብሩሾች፡-** እንስሳቱን ለማጽዳት (ለማጠብ)
- **የውሃ ገንዳ ወይም ባልዲ፡-** ለውሃ መያዣነት
- **የመመገቢያ ገንዳ፡-** ለእንስሳት ምግብ ማቅረቢያነት
- **ሣር ወይም መኖ፡-** የእንስሳት ምግብ ናቸው።

ተግባር 3.4.10 ☛ የቡድን ሥራ

ዓላማ- ለእርሻ እንስሳት እንክብካቤ የሚጠቅሙ ቁሳቁሶችን በተግባር ማሳየት

መመሪያ- በቡድን ሆናችሁ ከመምህራችሁ ጋር በአቅራቢያችሁ ወደሚገኝ የእርሻ እንስሳት ድርጅት በመሄድ በጥንቃቄ የቁሳቁሶችን አጠቃቀም በተግባር አሳዩ።

መልመጃ 3.4

ሀ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

1. አይጥ እንቁላል በመጣል ትራባለች።
2. ቁራ የተባለው የአሞራ ዝርያ መብረር ይችላል።
3. ሰጐን ክንፍ ስላላት መብረር ትችላለች።
4. ጉርጥና እንቁራሪት በውሃ ውስጥ ብቻ የሚኖሩ እንስሳት ናቸው።
5. ውሻ ከዕፅዋት በል እንስሳት ይመደባል።

ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ መርጣችሁ ጻፉ።

1. ከሚከተሉት ውስጥ በቅርፊት የተሸፈነ እንስሳ የትኛው ነው?

   ሀ. ውሻ ሐ. እባብ

   ለ. ዶሮ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

2. እንስሳት በምን በምን ይለያያሉ?

   ሀ. በመኖሪያ ሥፍራ ሐ. በአረባብ

   ለ. በአመጋገብ መ.ሁሉም መልስ ናቸው።

3. ከሚከተሉት በውሃ ውስጥ ብቻ መኖር የሚችለው እንስሳ የትኛው ነው?

   ሀ. አዞ ለ. አሳ ሐ. ጉማሬ መ. ጉርጥ

4. ከሚከተሉት ውስጥ ተሳቢ የሆነው እንስሳ የትኛው ነው?

   ሀ. አንበጣ ለ. ዔሊ ሐ. እባብ መ. እንቁራሪት

5. ከሚከተሉት ውስጥ ከእፅዋት በል እንስሳት የሚመደበው የትኛው ነው?

   ሀ. ሰው ለ. ድመት ሐ. ዶሮ መ. ፍየል

ሐ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. የእርሻ እንስሳትን እንዴት መንከባከብ ይኖርብናል?
2. ከእንስሳት ውጤቶች የሚሠሩ ሦስት ነገሮችን ጥቀሱ።
3. አካላቸው በቅርፊት የተሸፈነ የሁለት እንስሳትን ስም ጥቀሱ።
4. በአካባቢያችሁ ያሉ እንስሳት በምን በምን ይለያያሉ?

ማጠቃለያ

- ተፈጥሮአዊ ክስተቶች ከሰው ልጅ ቁጥጥር ውጭ በተፈጥሮ የሚከሰቱ ናቸው። አንዳንድ ተፈጥሮአዊ ክስተቶች ተፈጥሮአዊ ዑደቶች ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ አልፎ አልፎ የሚከሰቱ ናቸው። ቀንና ሌሊት እንዲሁም ክረምትና በጋ የመሳሰሉት ተፈጥሯአዊ ዑደቶች ሲሆኑ እንደ ቀስተደመና፣ ጮርፍና ድርቅ የመሳሰሉት ደግሞ አልፎ አልፎ የሚከሰቱ የተፈጥሮ ክስተቶች ናቸው።
- የመለኪያ መሣሪያዎችን በመጠቀም ርዝመትን፣ መጠነቁስና ጊዜን መለካት ይቻላል። ሜትርና ሴንቲ ሜትር የርዝመት፣ ኪሎ ግራምና ግራም የመጠነ ቁስ፤ ሰዓት፣ ደቂቃና ሰኮንድ ደግሞ የጊዜ መልኪያ አሐዶች ናቸው።
- የመለኪያ መሣሪያዎች ዘመናዊና ባህላዊ ተብለው ይመደባሉ። ሜትር ቴፕ፣ ሚዛንና ሰዓት ዘመናዊ የመለኪያ መሣሪያዎች ናቸው። ስንዝር፣ ፈረስላ፣ ቁና፣ ጋሻና የመሳሰሉት ደግሞ ባህላዊ የመለኪያ መሣሪያዎች ናቸው።
- ቁሳቁሶች ከባድ ወይም ቀላል በማለት ሊመደቡ ይችላሉ:: ጠንካራ፣ ለስላሳ፣ ሸካራና ልሙጥ ተብለውም ይመደባሉ።
- የተፈጥሮ ሀብቶች በተፈጥሮ የሚገኙና ለሰው ልጆች ጥቅም የሚሰጡ ናቸው። የተፈጥሮ ሀብቶች ውሃን፣ አፈርን፣ ዕፅዋትን፣ ማዕድናትን፣ አየርንና እንስሳትን ያካትታሉ። ሰው መሠረታዊ ፍላጐቶቹን የሚያሟላው የተፈጥሮ ሀብቶችን በመጠቀም ነው። ስለዚህ የተፈጥሮ ሀብቶቻችንን መጠበቅና መንከባከብ ይገባናል።
- ተክሎች ሕይወት ያላቸው ነገሮች ናቸው። ተክሎች የተለያዩ ክፍሎች አሏቸው። እነርሱም ቅጠል፣ ግንድ፣ ሥርና አበባ ናቸው። እነዚህ የተክል ክፍሎች የተለያዩ ተግባራትን ያከናውናሉ። ተክሎች ለዕድገት የተለያዩ ነገሮች ያስፈልጓቸዋል:: እነርሱም አፈር፣ አየር፣ ውሃና የፀሐይ ብርሐን ናቸው። ተክሎችን ለማብቀል እንደ ዶማ፣ አካፋ፣ ውሃ ማጠጫ፣ ጋሪና የመሳሰሉ መሣሪያዎች ያስፈልጋሉ።
- በአካባቢያችን የተለያዩ ዓይነት እንስሳት ይገኛሉ። እነዚህን እንስሳት በአረባባቸው፣ በእንቅስቃሴያቸው፣ በአመጋገባቸው፣ በመኖሪያ ሥፍራቸውና በሰውነት ሽፋናቸው በመለየት መመደብ እንችላለን። እንስሳት ለሰው ልጅ የተለያዩ ጥቅሞችን ይሰጣሉ። **ለምሳሌ** ለምግብነት፣ ልብሶችን ለመሥራትና ለጉልበት መሣሪያነት ያገለግላሉ። እንስሳትን በእንክብካቤ መያዝ ይገባናል። ምክንያቱም እንክብካቤ ሲደረግላቸው እንስሳቱ ደስተኛና ጠንካራ በመሆን የበለጠ ምርታማ ሆነው ስለሚገኙ ነው።

የማጠቃለያ ጥያቄዎች

ሀ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ::

1. የፀሐይ ብርሐን በውሃ ጠብታዎች ውስጥ ሲያልፍ ቀስተደመና ይፈጠራል::
2. መጠነቁስን በኪሎ ግራምና በግራም መለካት እንችላለን ::
3. የሰው ልጅ ምግብ፣ ልብስና መጠለያን ከተፈጥሮ ሀብቶች ያገኛል::
4. ችግኞችን መትከል ለአፈር መሸርሸር ያጋልጣል::
5. የአካባቢ ቆሻሻ ለውሃ ብክለት መንሥዔ ሊሆን አይችልም::

ለ. በ"ሀ" ሥር የተዘረዘሩትን የተክል ክፍሎች በ"ለ" ሥር ከተዘረዘሩት ጥቅሞቻቸው ጋር አዛምዱ::

"ሀ"	"ለ"
1. አበባ	ሀ. ተክሎች እንዳይወድቁ ከመሬት ጋር አጣብቆ ይይዛል
2. ሥር	ለ. ለተክሎች ምግብ ያዘጋጃል
3. ግንድ	ሐ. ለተክሎች የመራቢያ አካል ሆኖ ያገለግላል
4. ቅጠል	መ. ውሃና ማዕድናትን ወደ ቅጠሎችና ቅርንጫፍች ይወስዳል

ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ አክብቡ::

1. ከሚከተሉት ውስጥ የተፈጥሮ ክስተት የሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. ቀንና ሌሊት ሐ. ድርቅና ጎርፍ
   ለ. ክረምትና በጋ መ. ሁሉም መልስ ናቸው
2. የርዝመት የልኬት አሐድ የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ሴንቲ ሜትር ለ. ግራም ሐ. ሰኮንድ መ. ኪሎግራም
3. የተፈጥሮ ቁሳቁስ የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ጉማ ለ. ድስት ሐ. ጥጥ መ. ብርጭቆ
4. የደን ጥቅም የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. መጠለያ ለመገንባት ሐ. መድኃኒት ለመሥራት
   ለ. አፈር እንዳይሸረሸር መከላከል መ.ሁሉም መልስ ይሆናሉ

5. ለተክሎች ዕድገት አስፈላጊ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. አየር ሐ. የፀሐይ ብርሐን

ለ. ውሃ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

6. ከሚከተሉት ውስጥ እንቁላል በመጣል የሚራባው እንስሳ የትኛው ነው?

ሀ. ጅብ ለ. በግ ሐ.ዶሮ መ. ላም

7. ከሚከተሉት እንስሳት በሰማይ ላይ የሚበረው የትኛው ነው?

ሀ. ቀንድ አውጣ ለ. አንበጣ ሐ. ዔሊ መ. አዞ

8. ሥጋ በል ያልሆነው እንስሳ የቱ ነው?

ሀ. ቀጭኔ ለ. ውሻ ሐ. ነብር መ. አንበሳ

9. ከሚከተሉት ውስጥ የእንስሳት ጥቅም የሆነው የቱ ነው ?

ሀ. ለምግብነት ሐ. ለመዝናኛነት

ለ. ለጥበቃ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

10. ብርድ ልብስን ለመሥራት የሚያገለግለው የእንስሳት ውጤት የቱ ነው?

ሀ. የወተት ውጤቶች ሐ. ቆዳ

ለ. ሱፍ መ.ሁሉም መልስ ይሆናሉ

መ. በክፍት ቦታ ላይ ትክክለኛውን መልስ ሙሉ።

1. የእባብና የአሳ አካላት በ _____ የተሸፈኑ ናቸው።
2. የእንቁላል ጣይ እንስሳት ልጆች የሚያድጉት በ _____ ውስጥ ነው።
3. ተክሎች ምግባቸውን ለማዘጋጀትና ለማደግ የሚረዳቸውን ውሃና ማዕድናት የሚያገኙት ከ _____ ነው።
4. ከሰዎች ቁጥጥር ውጭ የሆነ በተፈጥሮ በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈጠር ክስተት _____ ይባላል።
5. በሀገራችን የሚገኙ ዋና ዋና ወቅቶች _____ እና _____ ናቸው።

ሠ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. የአየር ብክለት ሊፈጠር የሚችለው በምን ምክንያት ነው?
2. ውሃ ለሰው ልጆች ምን ምን ጥቅም ይሰጣል?
3. ዕፅዋትና ሥጋ በል የሆኑ የሦስት እንስሳትን ስም ዘርዝሩ።

ፍተሻ

የምታውቋቸውን ክንውኖች በመለየት በእያንዳንዱ ሳጥን ውስጥ ይህንን (✓) ምልክት አኑሩ።

1. አንዳንድ የተፈጥሮ ክስተቶች ተፈጥሯዊ ዑደቶች መሆናቸውን እናገራለሁ።
2. አንዳንድ የተፈጥሮ ክስተቶች አልፎ አልፎ የሚከሰቱ መሆናቸውን እናገራለሁ::
3. የመለኪያ አሐዶችን በመለየት ባህላዊና ዘመናዊ በማለት እመድባለሁ።
4. ቁሳቁሶችን (ዕቃዎችን) የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ በማለት እመድባለሁ።
5. ቁሳቁሶችን (ዕቃዎችን) በዓይነታቸውና በክብደታቸው መሠረት እመድባለሁ።
6. የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶችን እዘረዝራለሁ።
7. የተፈጥሮ ሀብቶች የሚሰጡትን ጠቀሜታ እዘረዝራለሁ።
8. የተፈጥሮ ሀብቶች ከጥፋት የሚጠበቁባቸውን ዘዴዎች አስረዳለሁ።
9. የተክል ክፍሎችን አሳያለሁ።
10. እያንዳንዱን የተክል ክፍል ናሙናዎች እሰበስባለሁ።
11. ስለ እያንዳንዱ የተክል ክፍል ሥራ ገለጻ እሰጣለሁ።
12. ተክሎች ለመብቀል የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች እዘረዝራለሁ።
13. ተክሎችን ለማብቀል የሚረዱ ዕቃዎችን (ቁሳቁሶችን) እዘረዝራለሁ።
14. እንስሳትን በእርባታ ሂደታቸው መሠረት እመድባለሁ።
15. እንስሳትን በእንቅስቃሴያቸው መሠረት እመድባለሁ።
16. እንስሳትን በአመጋገባቸው መሠረት እመድባለሁ።
17. እንስሳትን በመኖሪያ ቦታቸውና በሰውነት ሽፋናቸው መሠረት እመድባለሁ::
18. ከእንስሳት ውጤቶች የሚገኙ ምርቶችን እዘረዝራለሁ።
19. ለእርሻ እንስሳት እንክብካቤና አጠባበቅ የሚጠቅሙ ዕቃዎችን (ቁሳቁሶችን) እዘረዝራለሁ።

ምዕራፍ አራት

ክፍለ ከተማችን

ከምዕራፉ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ይህን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፦

- ከአራቱ አቅጣጫዎች አንጻር በክፍለ ከተማችሁ ውስጥ የሚገኙትን ጠቃሚ ቦታዎች ታመለክታላችሁ።
- የመሬትን አቀማመጥና ገጽታ ትለያላችሁ።
- በክፍለ ከተማችሁ የሚገኙትን ትላልቅ ተቋማት በመዘርዘር የተቋማቱን ሥራ ድርሻ ትተነትናላችሁ።
- በክፍለ ከተማችሁ ውስጥ የሚከናወኑትን ዋና ዋና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ትለያላችሁ።
- በአካባቢያችሁ ባሉ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ጥቅም ላይ የዋሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በምሳሌ ታስረዳላችሁ።
- ለክፍለ ከተማችሁ እድገት ሥራ አስፈላጊ መሆኑን ትገልጻላችሁ።
- ለክፍለ ከተማችሁ ዕድገት በዕድሜአችሁ ደረጃ ለሥራ ያላችሁን ቁርጠኝነት በተግባር ትገልጻላችሁ።
- ሳይንሳዊ የምርምር ክህሎትን ማለትም መመልከትን፣ መመዝገብን፣ መመደብን፣ መጠየቅን፣ መለካትን፣ መግባባትን፣ መሳይ ቅርጾችን ማዘጋጀትና በንብረት መሥራትን በተግባር ታሳያላችሁ።

4.1. የክፍለ ከተማችን መገኛ


ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ትምህርት ከተማራችሁ በኋላ፦

- አራቱን አቅጣጫዎች ታመለክታላችሁ።
- ከአራቱ አቅጣጫዎች አንጻር በክፍለ ከተማችሁ ውስጥ የሚገኙትን ጠቃሚ ቦታዎች ታመለክታላችሁ።
- በክፍለ ከተማችሁ ውስጥ የሚገኙ ጠቃሚና ታሪካዊ ቦታዎችን ትለያላችሁ።

ቁልፍ ቃላት

- ክፍለ ከተማ
- አንጻራዊ መገኛ
- ታሪካዊ ቦታዎች



ስዕል 4.1 መሠረታዊ አቅጣጫዎች

ተግባር 4.1.1 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- መሠረታዊ አቅጣጫዎችን መለየት


መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለመምህራችሁ በጽሑፍ አቅርቡ።

- መሠረታዊ አቅጣጫዎች ምንድን ናቸው?
- የምንኖርበትን አካባቢ መገኛ ከሌሎች አካባቢዎች እንዴት ለይቶ ማወቅ ይቻላል?

ሀ. አራቱ መሠረታዊ አቅጣጫዎች

የምንኖርበትን አካባቢ ከሌሎች አካባቢዎች ለይተን ለማወቅ በአንጻራዊ መገኛ ማመልከት ይቻላል። አንጻራዊ መገኛ አንድ ነገር የሚገኝበትን ቦታ ለማወቅ የምንጠቀምበት ዘዴ ነው። ለምሳሌ በስተግራ፣ በስተቀኝ፣ ከበስተጏላ፣ ከበስተፊት፣ ከላይና ከታች በማለት መግለጽ ይቻላል። በተጨማሪም የአንድን ነገር አንጻራዊ መገኛ ከአንድ ቋሚ አካባቢ አንጻር ተነሥተን በአራቱ መሠረታዊ አቅጣጫዎች ማመልከት ይቻላል። አራቱ መሠረታዊ አቅጣጫዎች የሚባሉት ሰሜንና ደቡብ፣ ምሥራቅና ምዕራብ ናቸው።

ለ. የክፍለ ከተማችን መገኛ ከሌሎች ክፍለ ከተሞች አንጻር



ሥዕል 4.2 የአዲስ አበባ ክፍለ ከተሞች ንድፍ ካርታ

ተግባር 4.1.2 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- የክፍለ ከተማችንን አቅጣጫ መለየት

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት ክፍለ ከተማችሁ የሚገኝበትን አቅጣጫ በተመለከተ ተወያዩ።

- ትምህርት ቤታችሁ በየትኛው ክፍለ ከተማ እንደሚገኝ ለመምህራችሁ ተናገሩ።
- ትምህርት ቤታችሁ የሚገኝበትን ክፍለ ከተማ በስተግራ በኩል የሚያዋስነው ክፍለ ከተማ ማን ይባላል? በስተቀኝ በኩል የሚገኘው ክፍለ ከተማስ ማን ይባላል?
- ከትምህርት ቤታችሁ አንጻር የቤታችሁን መገኛ አቅጣጫ አመልክቱ።

ክፍለ ከተማ የተለያዩ ብዙ ወረዳዎችን የያዘ የአስተዳደር እርከን ነው። በአዲስ አበባ ውስጥ አሥር ክፍለ ከተሞች አሉ። እነርሱም ቦሌ ክፍለ ከተማ፣ አራዳ ክፍለ ከተማ፣ ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ፣ ልደታ ክፍለ ከተማ፣ የካ ክፍለ ከተማ፣ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ፣ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ፣ አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ፣ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ እና ጉለሌ ክፍለ ከተማ ናቸው።

ተግባር 4.1.3 ☛ የግል ሥራ

ዓላማ- የክፍለ ከተማችሁን አንጻራዊ መገኛ ማመልከት

መመሪያ-

- በአዲስ አበባ የሚገኙ ክፍለ ከተሞችን ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምሥራቅና ምዕራብ በማለት መድቡ።
- በመሐል አዲስ አበባ የሚገኙ ክፍለ ከተሞች የትኞቹ እንደሆኑ ተናገሩ።
- እያንዳንዳችሁ የምትኖሩበትን ክፍለ ከተማ ስምና አንጻራዊ መገኛ በአዲስ አበባ ካርታ ላይ አመልክቱ።

በሥዕል 4.2 የአዲስ አበባን ክፍለ ከተሞች መገኛን የሚያሳየውን ካርታ ንድፍ በመመልከት የእያንዳንዱን ክፍለ ከተማ መገኛዎች ከአራቱ መሠረታዊ አቅጣጫዎች አንጻር መግለጽ ይቻላል። በዚህም መሠረት

- ቦሌ ክፍለ ከተማ የአዲስ አበባ ምሥራቃዊ ክፍል ነው።
- አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የአዲስ አበባ ደቡባዊ ምሥራቅ ክፍል ነው።
- ኮልፌ ቀራንዮና ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተሞች የከተማው ምዕራባዊ ክፍሎች ናቸው።

- ጉለሌና የካ ክፍለ ከተማ የከተማው ሰሜናዊ ክፍሎች ናቸው።
- አዲስ ከተማ፣ አራዳ፣ ልደታና ቂርቆስ ክፍለ ከተሞች ደግሞ በመሐል አዲስ አበባ ይገኛሉ።

ተግባር 4.1.4 ☛ **የቡድን ሥራ**

ዓላማ- በክፍለ ከተማችሁ የሚገኙ የተለያዩ ቦታዎችን አንጻራዊ መገኛ ማመልከት

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት የትምህርት ቤታችሁን መገኛ መነሻ በማድረግ በክፍለ ከተማችሁ የሚገኙ ታዋቂ ቦታዎችን አንጻራዊ መገኛ በተመለከተ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በጽሑፍ አቅርቡ።

- በክፍለ ከተማችሁ የሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ አደባባዮችና ሆቴሎች ከትምህርት ቤታችሁ በየትኛው አቅጣጫ እንደሚገኙ በጽሑፍ አመልክቱ።

ሐ. በክፍለ ከተማችን የሚገኙ ታሪካዊ ሥፍራዎች

ተግባር 4.1.5 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- በየክፍለ ከተማው የሚገኙ ታሪካዊና ጠቃሚ ሥራፍዎችን መለየት

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለመምህራችሁ አቅርቡ በጽሑፍ አቅርቡ።

- በክፍለ ከተማችሁ ከሚገኙ ጠቃሚ ቦታዎች መካከል ዋና ዋናዎቹን ዘርዝሩ።
- ታሪካዊ ሥፍራ ምንድን ነው?



ሥዕል 4.3 በተለያዩ ክፍለ ከተሞች የሚገኙ ሐውልቶች

የአንድ አካባቢ ሕዝብ ታሪካዊ ድርጊቶችን የፈጸመባቸው ቦታዎች ታሪካዊ ሥፍራዎች ይባላሉ። ለምሳሌም ጥንታዊ ዋሻዎች፣ ጦር ሜዳዎች፣ አደባባዮች፣ ምሽጎች፣ የታዋቂ ሰዎች መኖሪያ ቤቶችና ፍርስራሾችን መጥቀስ ይቻላል።

ታሪካዊ ሥፍራዎች የሕዝብን ባሕልና ታሪክ ለማጥናት ይጠቅማሉ። ስለዚህ ልንጠብቃቸውና ልንከባከባቸው ይገባል። ከታሪካዊ ሥፍራዎች የሚከተሉትን መመልከት ይቻላል።

ሀ. **ዋሻዎች** ለጥንታዊ ሰዎች በመኖሪያነት ያገለገሉ ቦታዎች ናቸው።

ለ. **አደባባዮች** የአንድ አካባቢ ሕዝብ በዓላትን የሚያከብርበት ሥፍራ ወይንም በማኅበራዊ ኑሮአቸው ያጋጠሟቸውንና የሚያጋጥማቸውን ልዩ ልዩ ጉዳዮች ለመነጋገር የሚገናኙባቸውና የሚሰባሰቡባቸው ሥፍራዎች ናቸው።

ሐ. **ምሽግ** ጥቃትን ለመከላከል ከአፈር፣ ከአሸዋ ወይንም ከድንጋይ የተሠራ መከላከያ ሥፍራ ነው።

መ. **የጦር ሜዳዎች** ጦርነት የተካሄደባቸው ቦታዎች ናቸው።

ተግባር 4.1.6 ☛ ተግባራዊ ክንውን

ዓላማ- በክፍለ ከተማችሁ ያሉ ታሪካዊ ሥፍራዎችን ይዘት መለየት

መመሪያ- ይህ ተግባር የሚከናወነው በቡድን በመሆን ነው።

- ተማሪዎች በክፍለ ከተማችሁ የሚገኝ አንድ ታሪካዊ ሥፍራ በመጎብኘት፣ ጥናት በማድረግና ሥዕሎችን በመሣል ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።
- በምትኖሩበት ክፍለ ከተማ የሚገኙ ታሪካዊ ሥፍራዎች ምን ምን እንደሆኑ ወላጆቻችሁን በመጠየቅ ዝርራቸውን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

በክፍለ ከተማችሁ ከታሪካዊ ሥፍራዎች በተጨማሪ የተለያዩ ተቋማት ይገኛሉ። ለምሳሌ፦

- በቦሌ ክፍለ ከተማ የቦሌ ዓለም አቀፍ የአውሮፕላን ማረፊያ ይገኛል።
- በቂርቆስ ክፍለ ከተማ የአፍሪካ ኀብረት ጽ/ቤት ይገኛል።
- በጉለሌ ክፍለ ከተማ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ዋና ግቢ ይገኛል።

መልመጃ 4.1

ሀ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

1. አንጻራዊ መገኛ የአንድ ቦታን መገኛ ለማወቅ ይጠቅማል።
2. ክፍለ ከተማ ወረዳዎችን የሚመራ የአስተዳደር እርከን ነው።
3. ምሽግ በታሪካዊ ሥፍራነት አይቆጠርም።
4. ታሪካዊ ሥፍራዎች ጠቀሜታ የላቸውም።

ለ. በ"ሀ"ሥር የቀረቡትን ከ"ለ" ሥር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምዱ።

ሀ	ለ
5. ታሪካዊ ሥፍራዎች	ሀ. ምሥራቅ
6. ክፍለ ከተማ	ለ. የአስተዳደር እርከን
7. መሠረታዊ አቅጣጫ	ሐ. ከበስተኋላ
8. አንጻራዊ መገኛ	መ. ዋሻዎች
	ሠ. ወረዳ

ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።

9. የአንጻራዊ መገኛን ሊያሳይ የሚችለው የትኛው ቃል ነው?

ሀ. በስተቀኝ ሐ. ከበስተኋላ

ለ. ወደታች መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ

10. ሕዝብ በዓላት የሚያከብርባቸው ሥፍራዎች _____ይባላሉ።

ሀ. የጦር ሜዳዎች ሐ. ዋሻዎች

ለ. አደባባዮች መ. ምሽጎች

11. በአዲስ አበባ ውስጥ የማይገኘው ክፍለ ከተማ የትኛው ነው?

ሀ. ቦሌ ለ. ኮተቤ ሐ. የካ መ. አራዳ

መ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::

12. መሠረታዊ አቅጣጫዎችን ዘርዝሩ።

13. በክፍለ ከተማችሁ ከሚገኙ ታሪካዊ ሥፍራዎች ውስጥ ሦስቱን ግለጹ።

4.2 የክፍለ ከተማችን የመሬት ገጽታ

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦

- በክፍለ ከተማችሁ ውስጥ የሚገኙትን የመሬት አቀማመጥና ገጽታ ትለያላችሁ።
- የመሬት ገጽታ ባሕርያትን ትገልጻላችሁ።

ቁልፍ ቃላት

- የመሬት አቀማመጥ
- የመሬት ገጽታ

ተግባር 4.2.1 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- የመሬት ገጽታ ባሕርያትን መለየት

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

- የመሬት ገጽታ ምንድን ነው?
- በክፍለ ከተማችሁ ምን ምን ዓይነት የመሬት ገጽታዎች ይገኛሉ?



ሥዕል 4.4 በተለያዩ ክፍለ ከተሞች የሚገኙ የመሬት ገጽታዎች

የመሬት ገጽታ በአንድ አካባቢ የሚገኝ የመሬት ተፈጥሮአዊ አቀማመጥ ነው፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ክፍለ ከተሞች የተለያዩ የተፈጥሮ ገጽታዎች ይገኛሉ፡፡ በከተማው

ሀ. ከፍተኛ የመሬት አካባቢዎች

ለ. ዝቅተኛ የመሬት አካባቢዎችና

ሐ. ሜዳማ የመሬት አካባቢዎች ይገኙበታል፡፡

ሀ. ከፍተኛ የመሬት አካባቢዎች

ከፍተኛ የመሬት አካባቢዎች የሚባሉት ተራራዎችና ኮረብታማ ሥፍራዎች ናቸው፡፡ **ለምሳሌ** ጉለሌ ክፍለ ከተማ ከፍተኛ ቦታዎች ከሚገኙባቸው ክፍለ ከተማዎች አንዱ ነው፡፡ የእንጦጦ ተራራ በጉለሌ ክፍለ ከተማ የሚገኝ ተራራ ነው፡፡



ሥዕል 4.5 የእንጦጦ ከፍተኛ ቦታ

ለ. ዝቅተኛ የመሬት አካባቢዎች

ዝቅተኛ ቦታዎች የሚባሉት በአብዛኛው የወንዝ ሸለቆዎች ናቸው። **ለምሳሌ** ከየካና ከጉለሌ ክፍለ ከተሞች ከሚገኙ ከፍተኛ ሥፍራዎች የሚነሡ ወንዞች ወደ ሜዳማ አካባቢ ሲፈሱ የወንዝ ሸለቆዎችን ይፈጥራሉ።





ሥዕል 4.6 ዝቅተኛ ቦታዎች

ሐ. ሜዳማ የመሬት አካባቢዎች

ሜዳማ የመሬት አካባቢዎች የሚባሉት በአብዛኛው ለጥ ያሉ ሜዳዎች የሚገኙባቸው ናቸው። የቦሌ ክፍለ ከተማ በብዛት በሜዳማ ቦታዎች የተሸፈነ ነው። በሌሎች ክፍለ ከተማዎች ደግሞ ከፍተኛ፣ ሜዳማና ሸለቋማ የመሬት ገጽታዎች ተደባልቀው ይገኛሉ።



ሥዕል 4.7 ሚዳማ አካባቢ

ተግባር 4.2.2 ➨ የቡድን ውይይት

ዓላማ- የመሬት ገጽታዎች በአየር ንብረት ላይ የሚያመጡትን ተጽእኖ መግለጽ

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለመምህራችሁ በጽሑፍ አቅርቡ::

- የመሬት ገጽታዎች በአየር ንብረት ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ ይፈጥራሉ?
- የአየር ንብረት በሰዎች የአኗኗር ልምድ ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ ይፈጥራል?

በተለያዩ የመሬት ገጽታዎች የሚታየው የአየር ንብረት የተለያየ ነው:: **ለምሳሌ** ዝቅተኛ የመሬት ገጽታ ያላቸው ቦታዎች ከፍተኛ ሙቀትና አነስተኛ የዝናብ መጠን ሲኖራቸው ከፍተኛ ቦታዎች ግን የሙቀት መጠናቸው አነስተኛ ነው:: በተጨማሪም ከፍተኛ ቦታዎች ቀዝቃዛና በአብዛኛው ዝናባማ የአየር ንብረት አላቸው::

የአየር ንብረት መለያየት በሰዎች የአኗኗር ልምድ ላይ ተጽእኖ ይኖረዋል:: ለምሳሌ በአለባበስና በመኖሪያ ቤት አሠራር ላይ በግልጽ የሚታይ ልዩነት ይፈጠራል:: ሞቃታማ የአየር ንብረት ባለበት አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ቀለል ያሉ አልባሳትን ይጠቀማሉ:: ቀዝቃዛማ የአየር ንብረት ባለበት አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ደግሞ ቅዝቃዜውን ለመቋቋም ሲሉ ወፈር ያሉ ልብሶችን ይለብሳሉ::

የቤት አሠራራቸውን ስንመለከት ደግሞ ሞቃታማ የአየር ንብረት ባለባቸው አካባቢዎች የሚሠሩ ቤቶች ጣራቸው ከፍተኛ ሲሆን ሙቀቱን ለመቀነስ የሚረዱ ብዛት ያላቸው

መስኮቶች ይኖሯቸዋል። ቀዝቃዛ የአየር ንብረት ባለባቸው አካባቢዎች የሚሠሩ ቤቶች ጣራ ዝቅ ያለና የመስኮቶቻቸው ብዛት አነስተኛ ነው።



ሥዕል 4.8 የአዲስ አበባ ከተማ ከፊል ገጽታ

ተግባር 4.2.3 ☛ የቡድን ሥራ

ዓላማ- የመልክአ ምድር ገጽታዎችን ልዩነት በመሳይ ቅርጽ ሠርቶ ማሳየት

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት ቀጥሎ የቀረበውን ተግባር ታከናውናላችሁ። በመጨረሻም የመልክአ ምድር ገጽታዎችን ልዩነት ለማሳየት የተሠራውን መሳይ ቅርጽ ለክፍል መምህራችሁ አቅርቡ።

- በክፍለ ከተማችሁ የሚገኙ የተለያዩ መልክአ ምድራዊ ገጽታዎችን በመጎብኘት የተለያዩ የመሬት ገጽታዎችን የሚያሳይ መሳይ ቅርጽ ከጀሶ ወይንም ከሸክላ ሥሩ።

መልመጃ 4.2

ሀ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

1. ተራራማ የመሬት ገጽታዎች በስፋት የሚገኙት በቦሌ ክፍለ ከተማ ነው።
2. ዝቅተኛ ሥፍራዎች በጣም ቀዝቃዛ ናቸው።
3. የአንድ አካባቢ መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ የመሬት ገጽታ ይባላል።
4. በአዲስ አበባ ከተማ ከፍተኛ ሥፍራዎች በስፋት ይገኛሉ።
5. የመሬት ገጽታዎች በአየር ንብረት ላይ ተጽእኖ የላቸውም።

ሐ. በ"ሀ"ሥር የቀረቡትን ከ"ለ" ሥር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምዱ።

ሀ	ለ
1. ከፍተኛ ተራራ	ሀ. ቦሌ
2. ዝቅተኛ ሥፍራ	ለ. ከፍተኛ የመሬት ገጽታዎች
3. ሞቃታማ ሥፍራ	ሐ. ሸለቆዎች
	መ. ወንዝ
	ሠ. እንጦጦ

መ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. የክፍለ ከተማችሁን መልክአ ምድራዊ ገጽታ በአጭሩ ግለጹ።
2. የመሬት ገጽታ በአየር ንብረት ላይ ያለው ተጽእኖ ምንድን ነው።

4.3 በክፍለ ከተማችን ውስጥ የሚገኙ ተቋማት

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦

- በክፍለ ከተማችሁ የሚገኙትን ትላልቅ ተቋማት ትዘረዝራላችሁ።
- በክፍለ ከተማችሁ የሚገኙ ተቋማት የሥራ ድርሻ ትተነትናላችሁ።

ቁልፍ ቃላት

- ተቋማት
- የሥራ ድርሻ

ተግባር 4.3.1 ☛ **የቡድን ሥራ**

ዓላማ- የተቋማትን ምንነትና ተግባር መግለጽ

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለመምህራችሁ በጽሑፍ አቅርቡ።

- ተቋም ምንድን ነው?
- በክፍለ ከተማችሁ የሚገኙ ትላልቅ ተቋማትን ዝርዝር አቅርቡ።
- በክፍለ ከተማችሁ የሚገኙ ተቋማት ምን ምን ተግባራትን ያከናውናሉ።





- ✓ በሥዕሉ የሚታየው ተቋም ምንድን ነው? ሥዕሉ ምንን ያሳያል?
- ✓ በተቋሙ የሚከናወነው ተግባር ምንድን ነው? የተቋሙ ተግባር ምንድን ነው

ሥዕል 4.9 በተለያዩ ክፍለ ከተሞች የሚገኙ ተቋማት

ሀ. ተቋማት

በክፍለ ከተማችን ውስጥ ለሕዝብ የተለያዩ ጠቃሚ አገልግሎቶችን በተቀናጀና በተደራጀ መልኩ ለመስጠት በመንግሥት እውቅና አግኝተው የተቋቋሙ ድርጅቶች ተቋማት ይባላሉ። በክፍለ ከተማችን ማኅበራዊ አገልግሎት ለመስጠት እንዲሁም ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴን ለማገዝ የተቋቋሙ በርካታ ተቋማት ይገኛሉ። ለምሳሌም፦

- ፖሊስ ጣቢያ
- ፍርድ ቤት
- ትምህርት ቤቶች
- ሌሎች የመንግሥት ቢሮዎች
- የጤና ተቋማት
- መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች
- የግል ተቋማት ይገኛሉ።

ለ. የተቋማት ተግባራት

በክፍለ ከተማችን የሚገኙ ተቋማት የተለያዩ ተግባራትና ኃላፊነት አላቸው። **ለምሳሌ** የሚከተሉትን ተቋማት ኃላፊነት እንመልከት።

የፖሊስ መምሪያ፦ የፖሊስ መምሪያ የክፍለ ከተማችን ነዋሪዎች ሰላምና ደኅንነት እንዲጠብቅ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው። የኅብረተሰቡን ሰላምና ደኅንነት የሚጠብቁ የፖሊስ አባላት አሉት። በተጨማሪም በክፍለ ከተማችን ወንጀል ሲፈጸም ወይንም የፖሊስ ክትትል የሚያስፈልገው ጉዳይ ሲያጋጥም ሰዎች በአቅራቢያቸው ወደሚገኘው የፖሊስ ጣቢያ በአካል ሄደው ወይንም በሌሎች መንገዶች የተፈጸመውን ወንጀል የሚያመለክቱበት ተቋም ነው። በክፍለ ከተማችን በፖሊስ መምሪያ ሥር በወንጀል የተጠረጠረ ወይንም ወንጀል የፈጸመ ሰው ለጊዜው ጉዳዩ እስኪጣራ ድረስ በጥበቃ የሚቆይበት ፖሊስ ጣቢያ ይገኛል። ስለዚህ ወንጀል ሲፈጸም ካየን ወይንም የፖሊስ ድጋፍ የሚያስፈልገው ነገር ካጋጠመን ለፖሊስ በመጠቆም አገልግሎት ማግኘት እንችላለን።



ሥዕል 4.10 ፖሊስ ጣቢያ

ፍርድ ቤቶች፡- በክፍለ ከተማችን የተለያየ ምድብ ያላቸው ፍርድ ቤቶች ሊገኙ ይችላሉ፡፡ ፍርድ ቤቶች የኅብረተሰብ ሰላም ተጠብቆ የዕለት ተዕለት ተግባራት እንዳይደናቀፉ የሚሠሩ መንግሥታዊ ተቋማት ናቸው፡፡ ፍርድ ቤቶችም ሕግን በመተርጎም ሕገ ወጥ በሆኑ ግለሰቦችና ድርጅቶች ላይ ተገቢ እርምት እንዲወስዱ የተበደሉ ዜጎች መብታቸው እንዲከበርላቸው የሚሠሩ ተቋማት ናቸው፡፡



ሥዕል 4.11 የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሌሎች መንግሥታዊ ተቋማት፡- በክፍለ ከተማችን እንደተቋቋመበት ዓላማ ለኅብረተሰቡ አገልግሎት የሚሰጡ የተለያዩ ተቋማት ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ የኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የመብራት አገልግሎት ይሰጣል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ የውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን በተለያዩ ክፍለ ከተሞች በሚገኙ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶቹ አማካኝነት ለኅብረተሰቡ ንጹሕ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እንዲሁም የፍሳሽ ቆሻሻ የማንሣት አገልግሎት ያቀርባል፡፡ ቴሌኮሙኒኬሽን ደግሞ የመደበኛ ስልክ፣ የተንቀሳቃሽ ስልክና የመረጃ መረብ አገልግሎት ይሰጠናል፡፡



ሥዕል 4.12 በተለያዩ ክፍለ ከተሞች የሚገኙ ተቋማት

በሁሉም ክፍለ ከተሞች የተለያዩ ተግባራትን የሚያከናውኑ ተቋማት ይገኛሉ። **ለምሳሌ፦**

- **የክፍለ ከተማ የትምህርት ጽሕፈት፦** በክፍለ ከተማችን የሚገኙ የትምህርት ተቋማት ለነብረተሰቡ ተገቢውን ትምህርት እንዲሰጡ የማድረግ፣ ድጋፍ የመስጠትና የመከታተል ሥራ ይሠራል።
- **የክፍለ ከተማ የጤና ጽሕፈት፦** የክፍለ ከተማችን ነዋሪዎች የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል።
- ***መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የግል ተቋማት***

መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ለምሳሌ የቀይ መስቀል ማኅበር ማንኛውም ዓይነት አደጋ በደረሰበት ቦታ ቀድሞ በመድረስ የሰዎችን ሕይወት በማዳን በጐ ተግባር ያከናውናል። የግል ተቋማት የምንላቸው በግል ባለሀብቶች የተቋቋሙ ትምህርት ቤቶች፣ የግል ጤና ድርጅቶች፣ ሆቴሎችንና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል። *መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት በተቋቋሙበት ዓላማ መሠረት ለነብረተሰቡ አገልግሎት ይሰጣሉ።*

መልመጃ 4.3

ሀ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

1. ተቋማት የተለያዩ አገልግሎቶችን ለመስጠት የተቋቋሙት ድርጅቶች ናቸው።
2. *ፖ*ሊስ ጣቢያና ፍርድ ቤት *መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ናቸው።*
3. የፍርድ ቤቶች ተግባር ሕግን መተርጎም ነው።
4. *መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ዓላማ የራሳቸውን ጥቅም ማስፈጸም ብቻ ነው።*

ለ. በ“ሀ”ሥር የቀረቡትን ተቋማት ከ“ለ” ሥር ከተዘረዘሩት አገልግሎቶች ጋር አዛምዱ።

ሀ	ለ
1. ፖሊስ ጣቢያ	ሀ. ሕግን መተርጎም
2. ፍርድ ቤት	ለ. ወንጀል መከላከል
3. ቴሌኮሙኒኬሽን	ሐ. በግለሰቦች የሚቋቋሙ
4. የግል ድርጅት	መ. ተንቀሳቃሽ ስልክ
	ሠ. የኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን

ሐ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. የትምህርት ጽሕፈት ቤትን ተግባራት በዝርዝር ግለጹ።
2. በአካባቢያችሁ ወንጀል እንዳይፈጸም ለመከላከል ከእናንተ ምን እንደሚጠበቅ ለመምህራችሁ በጽሑፍ አቅርቡ።

4.4 የክፍለ ከተማችን ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ትምህርት ከተማራችሁ በኋላ፦

- በክፍለ ከተማችሁ ውስጥ የሚከናወኑትን ዋና ዋና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎችን ትለያላችሁ።
- በክፍለ ከተማችሁ የሚታዩ ዋና ዋና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎችን ጠቀሜታ ትገልጻላችሁ።
- በአካባቢያችሁ የሚታዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ምሳሌ በመስጠት ታስረዳላችሁ።
- ለክፍለ ከተማችሁ እድገት የሥራን አስፈላጊነት ትገልጻላችሁ።
- በዕድሜያችሁ ደረጃ ለሥራ ያላችሁን ቁርጠኝነት በተግባር ትገልጻላችሁ።

ቁልፍ ቃላት

- ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች
- የቴክኖሎጂ ውጤቶች

1. ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች

ተግባር 4.4.1 ☛ የቡድን ሥራ

ዓላማ- የምጣኔ ሀብትን ምንነትና ጥቅም መግለጽ

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለመምህራችሁ በጽሑፍ አቅርቡ፡፡

- የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴን ምንነት በተመለከተ የምታውቁትን ተናገሩ፡፡
- በክፍለ ከተማችሁ ምን ምን ዓይነት ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች እንደሚከናወኑ ዘርዝሩ፡፡
- በክፍለ ከተማችሁ የሚታዩት ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ጠቀሜታን በተመለከተ ግለጹ፡፡

በአዲስ አበባ በሚገኙ ክፍለ ከተማዎች የሚኖሩ ሰዎች በተለያዩ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በመሳተፍ ሠርተው ይኖራሉ፡፡ በተለያዩ ክፍለ ከተሞች የከተማ ግብርና፣ የአገልግሎት ሰጪ ዘርፎች፣ የንግድ፣ የመንገዳ፣ የእደ ጥበብና የኢንዱስትሪ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች በስፋት ይታያሉ፡፡

በሁሉም ክፍለ ከተሞች ተመሳሳይ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ላይኖር ይችላል፡፡ ለምሳሌ የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የአዲስ አበባ ከተማ የኢንዱስትሪ ቀጠና በመሆኑ ብዛት ያላቸው ኢንዱስትሪዎች ይገኙበታል፡፡ የአቃቂ ቃሊቲ፣ የጉለሌ፣ የቦሌ፣ የየካ፣ የንፋስ ስልክ ላፍቶና ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ደግሞ የከተማ ግብርና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ በስፋት ይታይባቸዋል፡፡ የአዲስ ከተማ፣ የልደታ የአራዳና የቂርቆስ ክፍለ ከተሞች ደግሞ ሰፊ የንግድ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ይካሄድባቸዋል፡፡

ሀ. ግብርና

ግብርና በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል፡፡ እነርሱም እርሻና ከብት እርባታ ናቸው፡፡ በእርሻ ሥራ የሚተዳደሩ ሰዎች አርሶ አደሮች ወይም ገበሬዎች ይባላሉ፡፡ በከብት እርባታ የሚተዳደሩ ደግሞ አርብቶ አደሮች ይባላሉ፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ በአንዳንድ ክፍለ ከተማዎች የከተማ ግብርና ይካሄዳል፡፡

ተግባር 4.4.2 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- የከተማ ግብርና ምንነትንና ጠቀሜታ መለየት

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለመምህራችሁ በጽሑፍ አቅርቡ።

- የከተማ ግብርና ምንድን ነው?
- በከተማ ግብርና የሚመረቱ ምርቶች ምን ምን ናቸው?
- የከተማ ግብርና ለምን ይጠቅማል?






ሥዕል 4.13 የከተማ ግብርና በከፊል


በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ በወንዞች ዳርቻዎችና በመኖሪያ ግቢ ውስጥም ልዩ ልዩ አትክልትና ፍራፍሬዎች ይመረታሉ። ጤፍ፣ ስንዴና ገብስ የመሳሰሉት የምግብ ሰብሎችም ይመረታሉ። በተጨማሪም የዶሮ እርባታ፣ የወተትና የሥጋ ከብት እርባታ፣ የአሳማ እርባታ፣ የእንጉዳይ ምርት፣ የሐር ትል ምርት፣ የንብ እርባታ፣ የችግኝ ማራቢያና የመሳሰሉት በሰፊው ይከናወናሉ።

የከተማ ግብርና ለነዋሪዎች የምግብ ፍጆታ የሚውሉ ምርቶችን በማቅረብ፣ የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ የተፈጥሮ ሀብትን በአግባቡ በመጠቀም አካባቢን ለመንከባከብ የሚያስችል ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ አለው።



ሥዕል 4.14 የከተማ ግብርና እንቅስቃሴ በከፊል

ለ. ንግድ



ሥዕል 4.15 የንግድ ዓይነቶች በከፊል

ተግባር 4.4.3 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- የንግድ ምንነትና ጠቀሜታ መለየት

መመሪያ- ከ4-6 ተማሪዎች በቡድን በመሆን ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

- ንግድ ምንድን ነው?
- በአካባቢያችሁ ምን ምን ዓይነት የንግድ እንቅስቃሴዎች ይካሄዳሉ?
- በክፍለ ከተማችሁ የሚገኙ የተለያዩ የንግድ እንቅስቃሴዎች ጠቀሜታ ምንድን ነው?

ንግድ የግብርናና የኢንዱስትሪ ውጤቶችን በሚሸጡና በሚገዙ ሰዎች መካከል የሚደረግ ልውውጥ ነው፡፡ ንግድ አምራቹም ምርቱን ለመሸጥ ተጠቃሚውም ገዝቶ እንዲጠቀም የሚረዳ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ነው፡፡ ንግድ ለመንግሥት ግብር በመክፈል ለሕዝብና ለሀገር ዕድገት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡

በተለያዩ ክፍለ ከተሞች የችርቻሮ የጅምላ ንግድ ይካሄዳል፡፡ በንግድ እንቅስቃሴ የግብርና፣ የኢንዱስትሪ፣ የቴክኖሎጂ፣ የሆቴል አገልግሎትና ሌሎች በርካታ አገልግሎቶች ለተጠቃሚዎች ይቀርባሉ፡፡ በንግድ ልውውጥ የምርት፣ የአገልግሎትና የገንዘብ ዝውውር ይካሄዳል፡፡ በክፍለ ከተማችሁ በሚገኙ ትላልቅ የንግድ ተቋማት፣ መደብሮች፣ የገበያ ቦታዎችና በአገልግሎት መስጫዎች በርካታ ዜጐች ተቀጥረው በመሥራት ሕይወታቸውን ይመራሉ፡፡

ሐ. መጓጓዣ



ሥዕል 4.16 የየብስ መጓጓዣ ዓይነቶች

ተግባር 4.4.4 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- የመጓጓዣ ዓይነቶችና ጥቅሞችን መለየት

መመሪያ- ከ4-6 ተማሪዎች በቡድን በመሆን ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን ለመምህራችሁ በጽሑፍ አቅርቡ፡፡

- መጓጓዣ ምንድን ነው?
- የመጓጓዣ ጥቅሞች ምንድን ናቸው?
- በአካባቢያችሁ በስፋት የሚታዩ የመጓጓዣ ዓይነቶችን ዘርዝሩ፡፡

የመጓጓዣ ዓይነቶች ባህላዊና ዘመናዊ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡ በአንዳንድ ከመሐል ከተማ ርቀው በሚገኙ አካባቢዎች ሰዎች ባህላዊ መጓጓዣዎችን ይጠቀማሉ፡፡ በአንዳንድ ቦታዎች ደግሞ ባለሦስት ጎማ ተሽከርካሪዎች፣ የከተማ አውቶብሶች፣ ታክሲዎችና የቤት መኪናዎች አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡

የተለያዩ ዘመናዊና ባህላዊ መጓጓዣዎች ለነብረተሰቡ በርካታ ጥቅሞችን ይሰጣሉ፡፡ ለምሳሌ፡

- ሰዎችን ወደ ሥራ ቦታ ማድረስና መመለስ
- ለምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ
- እቃዎችን ለማጓጓዝ
- ምርት ለሸማቾች ለማድረስ ይጠቅማል፡፡

መ. እደጥበብ

ተግባር 4.4.5 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- የእደ ጥበብ ዓይነቶችንና ጠቀሜታን መለየት

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለመምህራችሁ በጽሑፍ አቅርቡ፡፡

- በእጅ የሚሠሩ የባህል ልብሶችን በስማቸው ግለጹ፡፡
- በአካባቢያችሁ ምን ምን ዓይነት የእደጥበብ ውጤቶች ይሠራሉ?
- የእደጥበብ ውጤት ጠቀሜታዎች ምንድን ነው?

			
✓ በሥዕሉ የሚታየው ምንድን ነው? የምን ውጤት ነው?	✓ በሥዕሉ የሚታየው ምንድን ነው? የምን ውጤት ነው?	✓ ሥዕሉ የሚያሳየው ምንድን ነው? የምን ውጤት ነው?	✓ ሥዕሉ የሚያሳየው ምንድን ነው? የምን ውጤት ነው?
			
✓ ሥዕሉ ምንን ያሳያል? የምን ውጤት ነው?	✓ ሥዕሉ ምንን ያሳያል? የምን ውጤት ነው?	✓ በሥዕሉ የሚታየው ምንድን ነው? የሚሠራው እንዴት ነው?	

ሥዕል 4.17 ልዩ ልዩ የእደጥበብ ውጤቶች

የእደ ጥበብ ውጤቶች በተለያየ ዘዴ ሊሠሩ ወይንም ሊመረቱ ይችላሉ። ለምሳሌ ሰዎች በእጃቸው ወይንም ትንንሽ የማምረቻ መሣሪያዎችን በመጠቀም እቃዎችን ያመርታሉ። የሀገር ባህል ልብሶች፣ የሽክላ ምጣድ፣ ጀበና፣ የአበባ ማስቀመጫ የመሳሰሉት እቃዎችን በእጅ ይሠራሉ። በተለያዩ የከተማችን አካባቢዎች በርካታ የእደ ጥበብ ውጤቶች ይመረታሉ። በጉለሌ ክፍለ ከተማ በሚገኙ በሸሮ ሜዳና በቀጨኔ አካባቢዎች የሸማ ልብስ በስፋት ይመረታል። የሽክላ ውጤቶች ደግሞ በቀጨኔ አካባቢ ይመረታሉ።

በተለያዩ ክፍለ ከተማዎች ከእንጨት፣ ከብረታ ብረት፣ ከፕላስቲክ፣ ከኖራ፣ ከአፈርና ከሌሎች ነገሮች ጠቃሚ ምርቶች ይመረታሉ። በጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ተቋማት የሚሠሩ ዜጎች ከውጪ ሀገር የሚገቡ የተለያዩ ምርቶችን የሚተኩ፣ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርቡ የአካባቢያቸውን ጥሬ ዕቃ የሚጠቀሙ የእደ ጥበብ ውጤቶችን በማምረት ምጣኔ ሀብታዊ ጥቅሞች ይሰጣሉ። በተጨማሪም ለዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠርና የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ ለኢንዱስትሪ ዕድገት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።

ተግባር 4.4.6 ☛ የቡድን ሥራ

ዓላማ- የኢንዱስትሪ ምጣኔ ሀብት ምንነትንና ጥቅምን መግለጽ

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

- ኢንዱስትሪ ምንድን ነው?
- በክፍለ ከተማችሁ የሚገኙ ትላልቅ ኢንዱስትሪዎችን ዘርዝሩ፡፡
- በክፍለ ከተማችሁ በሚገኙ ኢንዱስትሪዎች የሚመረቱ ምርቶች የሚሰጡት ጥቅም ምንድን ነው?

በክፍለ ከተማችሁ ልዩ ልዩ የግብርና ውጤቶችን በስፋት በመጠቀም የታሸጉ ምግቦችን፣ አልባሳትን፣ የተለያዩ መገልገያ ዕቃዎችንና ለስላሳ መጠጦችን የሚያመርት ድርጅት ኢንዱስትሪ ይባላል፡፡ በተለያዩ ክፍለ ከተማዎች የሚገኙ ኢንዱስትሪዎች መሠረታዊ ፍላጎታችንን ለማሟላት የሚያስችሉ ሸቀጦችን በማምረት፣ ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ ሀገራችን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እንድታገኝ በማድረግና በመሳሰሉት ሁኔታዎች ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣሉ፡፡

የግብርና ምጣኔ ሀብት ምርቶች ለአነስተኛና ጥቃቅን ንግዶች እንዲሁም ለአነስተኛ ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት መሠረት ናቸው፡፡ ኢንዱስትሪና ግብርና የተዛመዱ ናቸው፡፡ የግብርና ምጣኔ ሀብት ለኢንዱስትሪ ምጣኔ ሀብት መሠረትና መጋቢ ነው፡፡

2. ጠቃሚ የቴክኖሎጂ ውጤቶችና አገልግሎታቸው

የቴክኖሎጂ ውጤት የሰው ልጆች ሥልጣኔ በጥበብና በዕውቀት እያዳበረ ሲመጣ በዕለት ተዕለት ኑሮአቸው የሚያጋጥማቸውን ችግሮች ለመፍታት የሚፈጥሩት ግኝት ነው::

ተግባር 4.4.7 ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ-የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ምንነትና ጥቅምን መለየት

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በቀረበው ጥያቄ ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

- በአካባቢያችሁ ጥቅም ላይ የቴክሎጂ ውጤቶችን ዘርዝሩ፡፡
- በአካባቢያችሁ የሚገኙ የቴክኖሎጂ ውጤቶች የሚሰጡትን ጥቅም ግለጹ፡፡

የሚከተሉትን ሥዕሎች በመመልከት ለጥያቄዎቹ መልስ ስጡ::

		
✓ ይህ ሥዕል ምንን ያሳያል? አገልግሎቱስ ምንድን ነው?	✓ በሥዕሉ ሚታየው ምንድን ነው? የሚሰጠው ጥቅም ምንድን ነው?	✓በሥዕሉ ሚታየው ምንድን ነው? የሚሰጠው ጥቅም ምንድን ነው?
		
✓ በሥዕሉ የሚታየው ምንድን ነው? ✓ ለምን ይጠቅማል?	✓ ይህ ሥዕል ምንን ያሳያል? ጥቅሙስ ምንድን ነው?	✓በሥዕሉ የሚታየው ምንድን ነው? ✓ምን ዓይነት አገልግሎት ይሰጠናል?

ሥዕል 4.18 የተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች

የቴክኖሎጂ ውጤቶች የተለያዩ ጠቃሚ አገልግሎቶች በመስጠት አኗኗራችን ቀላልና ምቹ እንዲሆን ይረዱናል::

ለምሳሌ:-

- **ሬድዮና ቴሌቪዥን:-** የዓለም ወቅታዊ መረጃዎችን ለማዳመጥና ለመመልከት እንዲሁም ለመዝናኛ አገልግሎት ይጠቅማሉ::
- **የኤሌክትሪክ ምድጃ:-** የኤሌክትሪክ ጉልበትን በመጠቀም የተለያዩ ነገሮችን በፍጥነት ለማብሰል ይጠቅማል::
- **ማቀዝቀዣ:-**አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ ሥጋ ወተት የመሳሰሉ የምግብና የመጠጥ ዓይነቶች ሳይበላሹ እንዲቆዩ ለማድረግና ለማቀዝቀዝ ይጠቅማል::
- **ተንቀሳቃሽ ስልክ:-** በተለያዩ ቦታ የሚገኙ ሰዎች እንዲገናኙና በፍጥነት መረጃ እእንዲለዋወጡ ያስችላል::
- **የኤሌክትሪክ ጉልበት ማመንጫ ሞተር/ጀኔሬተር/:-**የኤሌክትሪክ ጉልበትን ለማመንጨት፣ ለመብራት፣ ማሽኖችን ለማንቀሳቀስ ይጠቅማል::

3. ሥራ ለአካባቢያችን ዕድገት ያለው ጠቀሜታ

ሰዎች በአካባቢያቸው የተለያዩ ሥራዎችን ይሠራሉ። እያንዳንዱ የኅብረተሰብ ክፍል የሚሠራው ሥራ ለቤተሰብ፣ ለአካባቢውና ለሀገር ዕድገት አስተዋጽኦ ያበረክታል። መሠረታዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት የማይችሉ ዜጎች በአካባቢያቸውና በክፍለ ከተማቸው ዕድገት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ይፈጥራሉ። ስለዚህ የግለሰቦች በሥራ መለወጥና በምጣኔ ሀብት ማደግ ለክፍለ ከተማው ልማት፣ ለመኖሪያ አካባቢያቸው ዕድገት መለወጥ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

4. የሥራ አስፈላጊነትና ክቡርነት

ተግባር 4.4.8 ☛ **የቡድን ውይይት**

ዓላማ- በጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች የመደራጀትን ጥቅም መግለጽ

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በቀረበው ጥያቄ ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

- በየአካባቢው በጥቃቅንና አነስተኛ ተደራጅተው የሚሠሩ ወጣቶች ለክፍለ ከተማው ዕድገት የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ ዘርዝሩ።
- እያንዳንዳችሁ ወደፊት በምን ዓይነት ሥራ ላይ መሰማራት እንደምትፈልጉና ለምን ይህንን እንደመረጣችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ።

ሥራ የዕድገት መሠረት በመሆኑ ሰዎች ለመኖር መሥራት ይኖርባቸዋል። ስለዚህም በአካባቢያችሁ የሚኖሩ ሰዎች በተለያዩ የሥራ መስኮች ተሰማርተው ይገኛሉ። **ለምሳሌ** በሕግ ጉዳዮች ማማከር፣ በንግድ፣ በጽዳት ሥራ፣ በሕክምና ሥራ፣ በመምህርነት፣ በፖሊስነት፣ በግንባታ ሥራና በመሳሰሉት ዘርፎች የተሰማሩ ዜጎች ይገኛሉ። ሁሉም የሥራ መስኮች የገቢ ምንጭ ይፈጥራሉ። ለሕዝቡ ጥቅም የሚሰጡና ገቢ የሚያስገኙ ሥራዎች አስፈላጊ በመሆናቸው ሊከበሩ ይገባል። ለሰዎች ኑሮ አስፈላጊና ጠቃሚ ምርቶችንና አገልግሎቶች የሚያበረክቱ ሙያዎች በእኩል ደረጃ ሊታዩ ይገባል። ስለዚህ ሁሉም የሥራ ዘርፎች ተገቢ አክብሮት ሊሰጣቸው ይገባል።

ተግባር 4.4.9 ☛ የቡድን ሥራ

ዓላማ- ወደፊት የሚሰማሩበትን የሥራ መስክ ጠቀሜታ መለየት

መመሪያ- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በቀረበው ጥያቄ ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

- ወደ ፊት ለመሰማራት በፈለጋችሁበት የሥራ መስክ ምን መሥራት ትፈልጋላችሁ?
- መሥራት የፈለጋችሁት ሥራ ለቤተሰባችሁና ለማኅበረሰባችሁን ምን ጥቅም ይሰጣል?

መልመጃ 4.4

ሀ. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

1. በአካባቢያችን የሚኖሩ ሰዎች ተመሳሳይ ምጣኔ ሀብታዊ ተግባራትን ያከናውናሉ።
2. የግብርና ሥራ የሚከናወነው በገጠር ብቻ ነው።
3. ንግድ ምርትን በሚሸጡና በሚገዙ ሰዎች መካከል የሚደረግ ልውውጥ ነው።
4. የኢንዱስትሪና የግብርና ምጣኔ ሀብታዊ ተግባራት ግንኙነት የላቸውም።
5. የግለሰቦች ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት ለአካባቢ ልማት ጠቃሚ ነው።

ለ.በ"ሀ"ሥር የቀረቡትን በ"ለ" ሥር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምዱ።

ሀ	ለ
1. እደ ጥበብ	ሀ. ምርቶች በዘመናዊ ማሽኖች የሚመረቱበት
2. አርብቶ አደር	ለ. በሰፊ ሥፍራ የሚከናወን የእርሻ ሥራ
3. ኢንዱስትሪ	ሐ. ጥሬ እቃዎች
4. የከተማ ግብርና	መ. ምርቶች በእጅ የሚመረቱበት
	ሠ. ከብት በማርባት የሚተዳደሩ
	ረ. በእርሻ ሥራ የሚተዳደር
	ሰ. የፍጆታ ምርቶች የሚመረቱበት

ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።

1. ከሚከተሉት አንዱ ከምጣኔ ሀብታዊ ተግባራት አይካተትም።

ሀ. ንግድ ሐ. ልመና

ለ. መጓጓዣ መ. እደ ጥበብ

2. በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የማይገኘው የትኛው ነው?

ሀ. የምግብ ሰብሎች ምርት ሐ. የዶሮ እርባታ

ለ. የአትክልትና ፍራፍሬ መ. የአዞ እርባታ

3. ከዘመናዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች ውስጥ የማይካተተው የትኛው ነው?

ሀ. አውቶቡስ ሐ. አውሮፕላን

ለ. የፈረስ ጋሪ መ. ባቡር

4. የእደ ጥበብ ውጤት ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. የባህል ልብሶች ሐ. ከእንጨት የሚሠሩ ቅርጻ ቅርጾች

ለ. ከብርና ከወርቅ የተሠሩ ጌጣ ጌጦች መ. ሽቶዎችና ቅባቶች

5. ለንግድ መቅረብ የሚችሉት ምርቶች የትኞቹ ናቸው?

ሀ. የግብርና ሐ. የእደጥበብ

ለ. የኢንዱስትሪ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

መ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. የእደ ጥበብ ውጤቶችን ጠቀሜታ ግለጹ።
2. የግብርናንና የኢንዱስትሪን ዝምድና ምሳሌ በማቅረብ አስረዱ።

ማጠቃለያ

- አንጻራዊ መገኛ የምንኖርበትን አካባቢ መገኛ ከሌሎች ቦታዎች አንጻር ለማሳየት ይጠቅማል።
- በክፍለ ከተማችን የተለያዩ የመሬት ገጽታዎች ይገኛሉ።
- በክፍለ ከተማችን ማኅበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ይገኛሉ።
- በክፍለ ከተማችን የተለያዩ
  - የንግድ፣
  - የከተማ ግብርና፣
  - የኢንዱስትሪና ሌሎች አገልግሎት ሰጪ እንቅስቃሴዎች ይገኛሉ።
- ተንቀሳቃሽ ስልክ፣ ቴሌቭዥን፣ ምድጃ፣ ጄኔሬተር የመሳሰሉት የተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች መጠቀም ኑሮአቸውን በቀላሉ ለመምራት ያስችላሉ።
- ለአካባቢያችንና ለክፍለ ከተማችን ዕድገት ሁሉም የሥራ ዓይነቶች የገቢ ምንጭ አስፈላጊና ጠቃሚ ናቸው። ስለዚህም የሥራ ዓይነቶች እኩል በመሆናቸው። አክብሮት ልንሰጣቸው ይገባል።

የምዕራፉ የማጠቃለያ ጥያቄዎች

ሀ. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

1. አንጻራዊ መገኛ የአንድ ቦታ መገኛን ለማወቅ ይጠቅማል።
2. የቦሌ ክፍለ ከተማ በምዕራባዊ አዲስ አበባ ይገኛል።
3. ማኅበራዊ ተቋማት ለትርፍ ብቻ የተቋቋሙ ድርጅቶች ናቸው።
4. የጉለሌ ክፍለ ከተማ በብዛት በሜዳማ ቦታዎች የተሸፈነ ነው።
5. የቀይ መስቀል ማኅበር መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው።

ለ. በ«ሀ» ስር የተዘረዘሩትን ተቋማት በ«ለ» ስር ከተዘረዘሩት የተቋማት ተግባራት ጋር አዛምዱ።

ሀ	ለ
1. ፖሊስ	ሀ. የፍትሕ አገልሎት መስጠት
2. ትምህርት ጽሕፈት ቤት	ለ. የውሃ አቅርቦት መስጠት
3. ጤና ጽሕፈት ቤት	ሐ. የመብራት አገልግሎት መስጠት
4. ፍርድ ቤት	መ. የኅብረተሰብ ሰላምና ደኅንነት መጠበቅ
5. የመብራት ኃይል ኮርፖሬሽን	ሠ. የትምህርት ዕድልን ማድረስ
	ረ. የኅብረተሰብ ጤና መጠበቅ

ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ።

1. መሐል አዲስ አበባ የሚገኘው ክፍለ ከተማ የቱ ነው?
   ሀ. ጉለሌ ለ. ቂርቆስ ሐ. ቦሌ መ. ንፋስ ስልክ ላፍቶ
2. እንጦጦ ተራራ በየትኛው ክፍለ ከተማ ይገኛል?
   ሀ. አራዳ ለ. ቦሌ ሐ. ልደታ መ. ጉለሌ
3. በከብት እርባታ የሚተዳደሩ ሰዎች ምን ይባላሉ?
   ሀ. አርሶ አደር ሐ. አርብቶ አደር
   ለ. ገበሬ መ. ወዝ አደር
4. የእደ ጥበብ ውጤት ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. የሀገር ባህል ልብሶች ሐ. ጀበና
   ለ. የሸክላ ምጣድ መ. ተንቀሳቃሽ ስልክ
5. ከሚከተሉት የመሬት ገጽታዎች በዝቅተኛ ሥፍራ ውስጥ የማይመደበው የቱ ነው?
   ሀ. ወንዝ ለ. ሸለቆ ሐ. ሜዳ መ. ኮረብታ

መ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. መሠረታዊ አቅጣጫዎችን ዘርዝሩ።
2. በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ክፍለ ከተማዎችን ዘርዝሩ።

ፍተሻ

የምታውቋቸውን ክንውኖች በመለየት በእያንዳንዱ ሳጥን ውስጥ ይህንን (✓) ምልክት አኑሩ።

1. ከአራቱ አቅጣጫዎች አንጻር በክፍለ ከተማችን የሚገኙ ጠቃሚ ቦታዎችን አመለክታለሁ።
2. የመሬትን አቀማመጥና ገጽታ እለያለሁ።
3. በክፍለ ከተማችን የሚገኙትን ትላልቅ ተቋማት በመዘርዘር የተቋማቱን የሥራ ድርሻ እገልጻለሁ።
4. የክፍለ ከተማችን ዋና ዋና የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴዎች እለያለሁ።
5. በአካባቢያችን ባሉ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ጥቅም ላይ የዋሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በምሳሌ አስረዳለሁ።
6. ለክፍለ ከተማችን እድገት ሥራ አስፈላጊ መሆኑን እገልጻለሁ።
7. ለክፍለ ከተማችን እድገት በዕድሜዬ ደረጃ ለሥራ ያለኝን ቁርጠኝነት አሳያለሁ።
8. ሳይንሳዊ የምርምር ክህሎትን ማለትም መመልከትን፣ መመዝገብን፣ መመደብን፣ መጠየቅን፣ መለካትን፣ መሳይ ቅርጾችን ማዘጋጀትና መንብረት መሥራትን በተግባር አሳያለሁ።